


# ትንቅንቅ

ሲድኒ ሼልደን

ትርጉም - ፀጋዬ ሸንብር

## ማውጫ


| | ገፅ |
|---|---|
| ምዕራፍ አንድ:- | 5 |
| ምዕራፍ ሁለት:- | 13 |
| ምዕራፍ ሦስት:- | 20 |
| ምዕራፍ አራት:- . | 26 |
| ምዕራፍ አምስት:- | 37 |
| ምዕራፍ ስድስት:- | 46 |
| ምዕራፍ ሰባት:- | 58 |
| ምዕራፍ ስምንት:- | 63 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ:- | 76 |
| ምዕራፍ አስር:- | 87 |
| ምዕራፍ አስራ አንድ:- | 91 |
| ምዕራፍ አስራ ሁለት- | 108 |
| ምዕራፍ አስራ ሦስት | 114 |
| ምዕራፍ አስራ አራት:- | 117 |
| ምዕራፍ አስራ አምስት:- | 122 |
| ምዕራፍ አስራ ስድስት:- | 132 |
| ምዕራፍ አስራ ሰባት:- | 139 |
| ምዕራፍ አስራ ስምንት:- | 146 |
| ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ:- | 150 |
| ምዕራፍ ሃያ:- | 156 |
| ምዕራፍ ሃያ አንድ:- | 162 |
| ምዕራፍ ሃያ ሁለት- | 170 |
| ምዕራፍ ሃያ ሦስት | 174 |

ትንቅንቅ


ምዕራፍ ሃያ አራት:- ........ 177
ምዕራፍ ሃያ አምስት:- ........ 182
ምዕራፍ ሃያ ስድስት:- ........ 185
ምዕራፍ ሃያ ሰባት:- ........ 195
ምዕራፍ ሃያ ስምንት:- ........ 200
ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ:- ........ 204
ምዕራፍ ሰላሳ- ........ 210
ምዕራፍ ሰላሳ አንድ:- ........ 221
ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት- ........ 226
ምዕራፍ ሰላሳ ሦስት ........ 228
ምዕራፍ ሰላሳ አራት:- ........ 233
ምዕራፍ ሰላሳ አምስት:- ........ 247
ምዕራፍ ሰላሳ ስድስት:- ........ 255
ምዕራፍ ሰላሳ ሰባት:- ........ 270
ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት:- ........ 272
ምዕራፍ ሰላሳ ዘጠኝ:- ........ 279
ምዕራፍ አርባ:- ........ 282
ምዕራፍ አርባ አንድ :- ........ 384
ምዕራፍ አርባ ሁለት- ........ 291
ምዕራፍ አርባ ሦስት ........ 299
ምዕራፍ አርባ አራት:- ........ 300

# ምዕራፍ አንድ
# ፓምፕሎና. ስፔን 1976

እቅዱ ከተሳሳተ ሁላችንም እንሞታለን፡፡ ነገሩን ለመጨረሻ ጊዜ በአእምሮው መልሶ አሰላሰለው፡፡ ጠብ ያለለት ምንም ነገር የለም እቅዱ የተዋጣለት ነው። ነገር ግን ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡ ከተሳካ ደግሞ ድንቅ እና ከኤል ሲድ የበለጠ ዋጋ ይኖረዋል፡፡ ካልተሳካ ደግሞ ...

ደህና የሚያስጨንቀው ጊዜ አልፏል፡፡ ጂሚ ሚሮ አሰበ፡፡ አሁን ጊዜው የተግባር ነው፡፡

ጂሚ ሚሮ ከባስክ ህዝብ ጀግናና አፈ ታሪክ ነው፡፡ ለስፔን መንግሥት ደግሞ ራስ ምታት፡፡ ሰውነቱ ግዙፍ ሲሆን በጡንቻ የፈጠረመ ነው፡፡ ቁመቱ ስድስት ጫማ ይረዝማል፡፡ የአይን አማኞች ሲገልፁት ካለው ቁመት ያረዝሙታል፡፡ መልኩ ጠይምና አስፈሪ መሆኑንም ይናገራሉ፡፡ ግራ የሚያጋባና በእሱ ላይ የሚነዙትን ወሬዎች በሚገባ የሚረዳ ሲሆን ለሚያምንበት ነገር ለመሞት ዝግጁ ነው፡፡

ፓምፕሎና አብዳለች፡፡ የጉሽ ሩጫ የሚደረግበት የመጨረሻው ጠዋት ላይ ትገኛለች፡፡ ፊስታ ዲሳን ፈርሚን የተባለው አመታዊ ፌስቲቫል ከጁላይ 7 እስከ 14 ይከናወናል፡፡ ከመላው አለም ሰላሳ ሺ የሚጠጉ ታዳሚዎች ወደ ከተማው ገብተዋል፡፡ አንዳንዶቹ አደገኛውን ውድድር ለመታደም የመጡ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በአስፈሪዎቹ አውሬዎች ፊት በመሮጥ ወንድነታቸውን ለመፈተሽ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የሆቴል አልጋዎች ቀደም ብለው ሲያዙ ከናቫራ የመጡት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መንገድ ላይ በባንኮች ደጃፍና መኪና ውስጥ አርፈዋል፡፡

ቱሪስቶች ካፌዎችንና ሆቴሎችን አጨናንቀዋል፡፡ በከተማ ውስጥ የማርሽ ባንድ ይደመጣል፡፡ የሰልፉ ተካፋዮች የሚያብለጨልጩ አልባሳትን ተጎናፅፈዋል። በመንገዱ ላይ ሲፈሱ ቀስተ ደመና ያረፈበት ወንዝ ይመስላል፡፡ የእሣት አደጋ መከላከያ መኪናዎችተጨማሪ ጩኸት ፈጥረዋል፡፡

የተጨነቁት ተመልካቾች ጉጉት ምሽት ላይ የሚከናወነውን የጉሽ ፍልሚያ መመልከት ነው፡፡ ብዙ ህዝብ የሚከታተለው ውድድር ኢንሴሪዬ ሲሆን ረፋድ ላይ የሚሮጡት ጉሾች አመሻሹ ላይ ለፍልሚያ ይቀርባሉ፡፡

ብዙ ጊዜ መመርመሪያው በአየር መንገዶች የተለመደ ነው::

‹‹አባቴ አዝናለሁ መመሪያ በመሆኑ ነው...››

‹‹ልክ ነህ ልጄ››

ቄሱ መሣሪያውን አልፈው ሲገቡ ጩኸት አሰማ:: ጥበቃው ጠመንጃውን አጥብቆ ያዘ::

ቄሱ ዞር በማለት ጠባቂውን እያዩ ፈገግ አሉ::

‹‹የእኔ ስህተት ነው›› በማለት መስቀላቸውን ከአንገታቸው ላይ አውልቀው ሰጡት:: በድጋሚ ሲያልፉ መሣሪያው ድምፅ አላሰማም:: ጥበቃው መስቀላቸውን መልሶ ሲያቀብላቸው አንገታቸው ላይ እያጠለቁ ወደ እስር ቤቱ ውስጥ ክፍል ጉዞአቸውን ቀጠሉ::

ማለፊያው ከባድ ጥበቃ ይደረግበታል::

ጠበቃው እየተፈላሰፈ ‹‹ያውቃሉ ጊዜዎትን በከንቱ እያባከኑ ነው:: አባቴ እነዚህ ጨካኞች ለምህረት የሚበቃ ነፍስ የላቸውም::››

‹‹አሁንም መሞከር አለብን ልጄ››

ጥበቃው አንገቱን በመነቅነቅ ‹‹የገሀነም ጠባቂ ሁለቱንም ለመቀበል እየተዘጋጀ መሆኑን ልነግርዎት እወዳለሁ::››

ቄሱ ጥበቃውን በመገረም ተመልከቱት:: ‹‹ሁለቱም አልኸኝ?›› እኔ የተነገረኝ መናዘዝ የሚፈልጉት ሦስት መሆናቸው ነበር::››

ጥበቃው በግዴለሽነት ትከሻውን ነቀነቀ:: ‹‹የእርሶን ጊዜ ቆጥበልንዎታል። ዛምራ ዛሬ ጠዋት በልብ ድካም በድንገት ሞቷል::››

ሁለቱ ሰዎች ራቅ ብሎ የሚገኘው ክፍል አጠገብ ደረሱ::

‹‹ደርሰናል አባቴ››

ጥበቃው የእስር ቤቱን በር በመክፈት ቄሱ ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ራቅ ብሎ ቆመ:: ጥበቃው በድንብርብሩን ቆለፈውና ኮሪደሩ ጥግ ቆመ:: ሁሉንም ነገር በንቃት እየጠበቀ ነው::

ቄሱ አስቀያሚው እስር ቤት ውስጥ ወደ ተጋደመው እስረኛ ተጠጉ::





‹‹ስምህ የእኔ ልጅ?››

‹‹ሪካርዶ ሜላዶ››

ቄሱ ትኩር ብለው ተመለከቱት:: ሰውየው ምን እንደሚመስል ለመናገር ይከብዳል:: ፊቱ ሞጋጋ ነው:: አይኑ ተከድኗል ማለት ይቻላል:: የደረቀ ከንፈሩን እየነቀነቀ ‹‹አባቴ እዚህ በመምጣትዎት ደስ ብሎኛል::››

‹‹ቄሱ የአንተን ኑዛዜ መቀበል የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው ልጄ›› አሉት በምላሻቸው::

‹‹ዛሬ ጠዋት በስቅላት ሊቀጡኝ ነው?››

ቄሱ በዝግታ ትከሻውን መታ አደረጉት:: ‹‹የሞት ፍረዱ የሚፈፀምብህ በመቀላት ነው::››

ሪካርዶ ሜላዶ ትኩር ብሎ እየተመለከታቸው ‹‹አይደለም›› አለ ‹‹አዝናለሁ:: ትዕዛዙ የተሰጠው በጠቅላይ ሚኒስትሩ በራሱ ነው::›› ቄሱ እጃቸውን እስረኛው ግንባር ላይ በመጫን ‹‹እግዚአብሔር ይማርህ::›› አሉት::

ሪካርዶ ሜላዶ ‹‹በቃሌ፣ በሐሣቤና፣ በፍላጐቴ ታላቅ ሐጢያት ሰርቻለሁ:: ሐጢያቴን በጠቅላላ ልቤ ውስጥ ይዤዋለሁ›› አላቸው::

ጥበቃው በር ስር ተለጥፎ ንግግራቸውን እያዳመጠ "ምን አይነት ጊዜ ማጥፋት ነው" በማለት ያጉረመርማል:: እግዚአብሔር ራሱ ፍርዱን ይሰጣል።

ቄሱ ሥራቸውን ጨረሱ:: ‹‹ልጄ ደህና ሁን:: እግዚአብሔር ነፍስህን በሰላም ይቀበሉት::

ቄሱ በሩን ሲያንኳኩ ጥበቃው ከፈተላቸውና ወደሚቀጥለው ክፍል ከፍቶ አስገባቸው::

‹‹እሱም የእርሶ ነው አባቴ›› አላቸው::

ቄሱ ወደ ሁለተኛው የእስር ክፍል ዘለቁ:: በውስጡ ያለው ሰው በተመሳሳይ ክፉኛ ተደብድቧል:: ቄሱ ረዘም ላለ ጊዜ በፅሞና ተመለከቱት:: ‹‹ማነው ስምህ ልጄ?››

‹‹ፊሊክስ ካርፒዬ›› አላቸው ጺማሙ ሰው ፊቱ ላይ አዲስ ጠባሳ ይታያል:: ‹‹ሞትን አልፈራም አባቴ››

# ምዕራፍ ሶስት
# አቪላ

ለስላሳና ስሜት የሚገዛ ነው፡፡ ሴቶች ብቻ

ዝምታው እንደበረደ ጥጥ ለስላሳና ስሜት የሚገዛ ነው፡፡ ሴቶች ብቻ ዝምታው እንደበረደ ጥጥ ከድንጋያማ ከተማዋ አቪላ ወጣ የሚኖሩበት (አድባር) የሲስቴሪዚያን ገዳም ከድንጋያማ ከተማዋ አቪላ ወጣ ብሎ ከትሟል፡፡ ከማድሪድ ሰሜን ምዕራብ 112 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው አቪላ ከስፔን ከተሞች ከፍታ ቦታ ላይ በመከተም ቀዳሚ ነች፡፡ ገዳሙ ለፅሞና ታስቦ የተሰራ ሲሆን አጅግ ጥበቅ የሆነ ዝምታ የነገሰበት ነው፡፡ በ1601 የወጣው ደንብ ለዘመናት ሳይለወጥ ፀንቶ ቆሟል፡፡ ከፀሎት በስተቀር ዘወትር በዝምታ የተዋጠ ነው፡፡

በቤተክርስቲያኑ ስር የታነፀው ገዳም አራት በአራት ሲሆን በጠንካራ ድንጋይ የተከበበ ነው፡፡ መሐሉ ላይ ያለው ቀዳዳ ብርሃን ያስገባል፡፡ አርባ ሴት መነኮሳት (እማሆዮች) በገዳሙ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በአቪላ ያለው ገዳም በስፔን ከቀሩት ሰባት ገደማቶች አንዱ ነው፡፡ በእርስ በርስ ጦርነቱ በመቶ የሚቆጠሩ ገዳማት የወደሙ ሲሆን ፀረ ቤተክርስቲያን አቋም ለዘመናት ያንፀባረቀ ነበር፡፡

የሚደረግበትና ህይወታቸውን

የሲስተር ቴሬዚያን ገዳም ጥብቅ ክትትል የሚደረግበትና ህይወታቸውን ለፀሎት የሚሰጡ የሚኖሩበት ነው፡፡ ጊዜና ወቅት የማይገድበው ቦታ አንዴ ከገቡ ለዘለአለም የማይወጡበት ነው፡፡ የገዳሙ ነዋሪዎች ህይወት በአምነት የተሞላና፣ ፀፀት የወረረው ነው፡፡ የእምነት ቢሮው በየቀኑ ቁጥጥር የሚደረግበት ሲሆን አጥሩ የተሟላና ቋሚ ነው፡፡

የእማሆዮቹ አለባበስ አንድ አይነት ሲሆን ልብሱ የሚሰፋው ገዳሙ ውስጥ ነው፡፡ ለአመታት ይዘቱን ሳይለቅ ቆይቷል፡፡ አኗኗራቸው ቀላልና ማራኪ ነው፡፡ አለባበሳቸውም ገዳማዊነትን የሚያንፀባርቅና ለመቶ አመታት ያልተቀየረ ነው፡፡ የሴት መነኮሳቱ አለባበስ ጥቁር ቆብ መሳይ ነገር በመድፋት ከጉልበታቸው ዝቅ ያለ ጥቁር ቀሚስ ይለብሣሉ፡፡

በገዳሙ ውስጥ ያለው መተላለፊያ ከመመገቢያ ክፍሉ፣ በማኅበራዊ መሰብሰቢያ፣ ከመቅደሱና ማደሪያ ክፍሉ ጋር ያገናኛል፡፡ ሁሉም ቦታ ቀዝቃዛና በንፅህና የተሞላ ነው፡፡ በመጋረጃ በተሸፈነው ክፍል አሻግረው ሲመለከቱ መናፈሻውን ያያሉ፡፡ እያንዳንዱ መስኮት በብረት ፍርግርግ ታጥሯል፡፡ በዚህም የውጪ አለም እይታ አይረብሻቸውም፡፡ በጥንታዊው ሻማ ማብሪያ ላይ





የተተከሉት ሻማዎች የከፍሉን ብርሃን አድምቀውታል፡፡

ላለፉት አራት መቶ አመታት ከሰዎቹ መቀያየር በስተቀር ከገዳሙ ይዞታ የተለወጠች ቅንጣት ነገር የለችም፡፡ እማሆዮቹ የእኔ የሚሉት ንብረት የላቸውም፡፡ ለክርስቶስ ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት በድህነት በመኖራቸው ይደሰታሉ፡፡ ቤተክርስቲያኗ ራሷ ከከበሩ ጌጣጌጦች የራቀች ሲሆን ከብዙ ዘመን በፊት አንድ ግለሰብ የለገሳት ጠንካራ የወርቅ መስቀል ብቻ ነው እስኛ የምትለው ሐብቷ፡፡ ይህ ከትዕዛዝ ውጭ ተቀምጦ የተገኘው ወርቅ መኖሩ የታወቀው ከተሸሸገ ቦታ በመገኘቱ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗ ቅጥር ላይ የተሰቀለው የእንጨት መስቀል ነው፡፡

ሕይወታቸውን ለአምላካቸው የሰጡት ሴቶች በህብረት ይኖራሉ፡፡ በጋራ ይሰራሉ፣ በጋራ ይፀልያሉ፣ በጋራ ይመገባሉ፡፡ ተነካክተውና ተነጋግረው አያውቁም፡፡ መናገር የሚፈቀድላቸው በጋራ ሲያመሰግኑ ወይም ማዘር ፕሪ አሬስ ቤቲና ቢሮአቸው ጠርተው ሲያነጋግሯቸው ብቻ ነው፡፡ አሁንም በገዳሙ ጥንታዊው የምልክት ቋንቋ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የገዳሙ አበአምኔት (ማዘር ፕራ ኣሬስ) በሰባዎቹ ውስጥ የሚገኙና ለብሩህ ፈገግታ የተሞሉ ናቸው፡፡ በገዳሙ ሰላማዊ ህይወት ፍፁም ደስተኛና ህይወታቸውን ለአምላካቸው የሰጡ ናቸው፡፡ በስራቸው ያሉትን መነኮሳት በፅናት የሚጠብቁ ሲሆን ደንብ ለማስከበር እርምጃ ሲወስዱ ውስጣቸው በህመም ይዋጣል፡፡ ህመሙ ከተቀጪዎቹ በላይ ይሰማቸዋል፡፡

መነኮሳቱ በኮሪደሩ በኩል ሲያልፉ አንገታቸውን ደፍተው በዝምታ ተውጠው ነው፡፡ እጃቸውን አነባብረው እርስ በርስ ይተላለፋሉ፡፡ በገዳሙ የሚሰማው ብቸኛ ድምፅ ደወሉ ብቻ ነው፡፡

መነኮሳቱ የመጡት ከተለያዩ አገራትና የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ ቤተሰቦቻቸው ወግ አጥባቂ፣ ገበሬ፣ ወታደር ወዘተ ናቸው፡፡ ሐብታቸውን ጥለው ወይም ከነድህነታቸው ወደ ገዳሙ ገብተዋል፡፡ የተማሩና መሐይሞች የዋህና በምስጢር የተሞሉ ቢሆኑም አሁን በእግዚአብሔር አይን ሁሉም እኩል ናቸው፡፡ ከአምላክ ጋር ዘለአለም ጋብቻ መስረተዋል፡፡

በገዳሙ ያለው የኑሮ ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ በክረምት ብርዱ አጥንት ይሰብራል፡፡ ሲተኙም ልብሣቸውን ሳያወልቁ ነው፡፡ በብርድ ልብሳቸው ተጠቅልለው በጠባቧ ክፍላቸው ሌሊቱን ያሳልፋሉ፡፡ በክፍሉ ጥግ ለመታጠቢያ የሚሆን እቃ ተቀምጦላቸዋል፡፡ የትኛዋም መነኩሴ ሌላዋ ክፍል እንድትገባ

አይፈቀድላትም። ፈቃድ ያላቸው ማዘር ቤቲና ብቻ ናቸው። በግቢው ከስራና ፀሎት በስተቀር ምንም አይነት መዝናኛ ቦታ የለም። ለስራ በተከለለው ቦታ መፅሐፍ መጠረዝ፣ ሽመና ዳቦ ጋገራ ይከናወናል። በየቀኑ ስምንት የፀሎት ሰአት ሲኖር ማቲንስ፣ ላውድስ፣ ፕሪም፣ ቴርሴ፣ ሴክት፣ ኖን፣ ቬስፐርስ እና ኮምፕላይን ይባላሉ። ከዚህ ጐን ለጐን ሌሎች የአምልኮ ተግባራት አሉ።

ራስን መቅጣት በሌሎች ገዳማት የቀረ ቢሆንም እዚህ ግን በቀን አንዴ ወይም በሳምንት አንድ ጊዜ መነኮሳቱ አካላቸውን ስለጥሩ ሥነ ምግባር በማለት ይቀጣሉ። አካልን በሚያሳምመውና ጀርባን በሚልጠው በቀጭን ሽቦ በተያያዘ ወፍራም እንጨት ራሣቸውን ይገርፋሉ። ክርስቶስን ለመምሰል እሱ ላይ የደረሰውን ቅጣት በራሣቸው ላይ ይፈጽማሉ።

እዚህ ያለው ህይወት የትኛውም እስር ቤት ካለው ህይወት የተለየና ጥብቅ ነው። በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ከውጪ አለም ጋር ምንም አይነት ትውውቅ የሌላቸው ናቸው። ከአካላዊ ፍቅር ንብረት ከማፍራትና የፈለጉትን ከመምረጥ የተገለሉ ቢሆንም እነዚህን ነገሮች በመተዋቸው ከስስትና ውድድር ላይ ወጥተዋል። ከጥላቻና በቀል ፀድተዋል። የውጪ አለም ከሚጭንባቸው ጫናም ተገላግለዋል።

በገዳሙ የሞላው ሰላምና ፍቅር ብቻ ነው። ገዳሙ እስር ቤት ቢሆን ኖሮ በአምላክ ገነት ውስጥ የሚገኝ እስር ቤት ሊባል የሚችል ሲሆን ለዘለአለማዊ ደስታ የሚገኝበትና በፍፁም ፍቃደኛነት ለመኖር መርጠው የገቡበት ነው።

ሲስተር ሉቺያ ከእንቅልፋቸው የነቁት ደወሉ ሲጮህ ሰምተው ነው። ከተኙበት ጠባብ ክፍል በፍጥነት ነቅተው ተነሱ። ደወሉ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት መሆኑን አሳወቃቸው። የቪግሊስ ቢሮ ሥራውን ሲጀምር አለም በበኩሏ ገና ከጨለማ አልተላቀቀችም።

ደደብ። ይህ ድግግሞሽ ሊገድለኝ ነው አለች ሲስተር ሉቺያ በሐሳቧ።

ምቾት በሌለው አልጋዋ ላይ ተጋድማ ሲጋራ ጠማት። እያመነታች ከአልጋዋ ውስጥ ወጣች። በምቾት የምታሳልፈው ሌሊት እንደአሸዋ ተጠራርጐ ሔዷል። ቢሮም በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ያላትን ድንቅና በዲዛይነሮች የተሰጠፉ የሌሊት ልብሶቿ ትዝ አሏት።

ከማደሪያ ክፍሏ ውጭ ዝቅ ያለው የመነኮሳቱ እርምጃ ተሰማት። አልጋዋን በግድየለሽነት አለባብሳ ከመነኮሳቱ ጋር ኮሪደሩ ላይ አብራ ተሰለፈች። ሁሉም





አንገታቸውን ደፍተው አይናቸውን ሰብዋል። በዝግታ ወደማምለኪያ ቦታው ጉዞ ጀመሩ።

ሰልፋቸው ያልተዛነፉ መሆኑን ሉቺያ ተገነዘበች። እነዚህ ሴቶች ህይወታቸውን በዚህ መንገድ ለማሳለፍ የወደዱበት መንገድ ግራ አጋብቷታል። ያማሩ ልብሶች፣ ጣፋጭ ምግቦችና የፍቅር ጨዋታን ንቀው እዚህ ተገኝተዋል። እነዚህን ነገሮች ትተው የመኖር ትርጉሙ ምንድን ነው? የማይረቡስ መመሪያዎች!

ሲስተር ሉቺያ ወደፀሎት ቤቱ ስትገባ የመነኮሳቱ አለቃ ‹‹አንገትሽን ደፍተሽ መጓዝ አለብሽ። እጆሽን ደረትሽ ላይ ማነባበሩን አትርሺ። በዝግታ ተራመጂ። ማንንም ቀና ብለሽ እንዳታይ። ማውራት አትችይም። ጆሮሽ መስማት ያለበት የአምላክን ቃል ብቻ ነው›› አሏት።

‹‹እሺ እናቴ›› አለች።

ለሚቀጥለው ወር የሚያገለግውን መመሪያ ሉቺያ ተቀበለች።

‹‹እዚህ የሚመጡት ሰዎች ሌሎችን ለመቀላቀል ሳይሆን የሚመጡት ከአምላክ ጋር ለመቀላቀል ነው። በብቸኝነት የተሞላ መንፈሣዊ ህይወት ከአምላክ ጋር ህብረት ለመፍጠር አስፈላጊ ነው። የዝምታ ደንቡ ደግሞ መተማመኛችን ነው።››

‹‹እሺ እናቴ››

‹‹እዚህ ስትመጪ መማር ያለብሽ ቀዳሚው ነገር ያለፈውን ነገር መርሣት ነው። ልምድሽን የቃላት ውክቢያውን እንዲሁም በውስጥሽ የተቀበሩትን ምስሎች አውጥተሽ ጣይው። ህሊናችን በማንፃት ከራስ ወዳድነትና ምኞት መላቀቅ ይጠበቅብሻል። ባለፉት ጊዜያት ለሰራነው ጥፋት ማዘናችን ወይም መፀፀታችን ብቻውን በቂ አይደለም። የአምላክን ዘለአለማዊነትና ውበት እንዴ ከተረዳነው ለራሣችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ለሰሩት ኃጢት መፀለይ አለብን።››

‹‹እሺ እናቴ››

‹‹ከውስጥ ጉጉትሽ ጋር መታገል አለብሽ››

‹‹እሺ እናቴ››

‹‹እያንዳንዱ መነኩሴ በዝምታ ለብቻዋ ተገልላ ትኖራለች። በዚህም መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳለች።››

አይፈቀድላትም፡፡ ፈቃድ ያላቸው ማዘር ቤቲና ብቻ ናቸው፡፡ በግቢው ከስራና ፀሎት በስተቀር ምንም አይነት መዝናኛ ቦታ የለም፡፡ ለስራ በተከለለው ቦታ መፅሐፍ መጠረዝ፣ ሽመና ዳቦ ጋገራ ይከናወናል፡፡ በየቀኑ ስምንት የፀሎት ሰአት ሲኖር ማቲንስ፣ ላውድስ፣ ፕሪም፣ ቴርሴ፣ ሴክት፣ ኖን፣ ቬስፐርስ እና ኮምፕላይን ይባላሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ሌሎች የአምልኮ ተግባራት አሉ፡፡

ራስን መቅጣት በሌሎች ገዳማት የቀረ ቢሆንም እዚህ ግን በቀን አንዴ ወይም በሳምንት አንድ ጊዜ መነኮሳቱ አካላቸውን ስለጥሩ ሥነ ምግባር በማለት ይቀጣሉ፡፡ አካልን በሚያሳምመውና ጀርባን በሚልጠው በቀጭን ሽቦ በተያያዘ ወፍራም እንጨት ራሣቸውን ይገርፋሉ፡፡ ክርስቶስን ለመምሰል እሱ ላይ የደረሰውን ቅጣት በራሣቸው ላይ ይፈጽማሉ፡፡

እዚህ ያለው ህይወት የትኛውም እስር ቤት ካለው ህይወት የተለየና ጥብቅ ነው፡፡ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ከውጪ አለም ጋር ምንም አይነት ትውውቅ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከአካላዊ ፍቅር ንብረት ከማፍራትና የፈለጉትን ከመምረጥ የተገለሉ ቢሆንም እነዚህን ነገሮች በመተዋቸው ከስስትና ውድድር ላይ ወጥተዋል፡፡ ከጥላቻና በቀል ፀድተዋል፡፡ የውጪ አለም ከሚጭንባቸው ጫናም ተገላግለዋል፡፡

በገዳሙ የሞላው ሰላምና ፍቅር ብቻ ነው፡፡ ገዳሙ እስር ቤት ቢሆን ኖሮ በአምላክ ገነት ውስጥ የሚገኝ እስር ቤት ሊባል የሚችል ሲሆን ለዘለአለማዊ ደስታ የሚገኝበትና በፍፁም ፍቃደኛነት ለመኖር መርጠው የገቡበት ነው፡፡

ሲስተር ሉቺያ ከእንቅልፋቸው የነቁት ደወሉ ሲጮህ ሰምተው ነው፡፡ ከተኙበት ጠባብ ክፍል በፍጥነት ነቅተው ተነሱ፡፡ ደወሉ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት መሆኑን አሳወቃቸው፡፡ የቪግሊስ ቢሮ ሥራውን ሲጀምር አለም በበኩሏ ገና ከጨለማ አልተላቀቀችም፡፡

ደደብ፡፡ ይህ ድግግሞሽ ሊገድለኝ ነው አለች ሲስተር ሉቺያ በሐሳቧ፡፡

ምቾት በሌለው አልጋዋ ላይ ተጋድማ ሲጋራ ጠማት፡፡ እያመነታች ከአልጋዋ ውስጥ ወጣች፡፡ በምቾት የምታሳልፈው ሌሊት እንደአሸዋ ተጠራርጐ ሔዷል፡፡ ቢሮም በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ያላትን ድንቅና በዲዛይነሮች የተሰጠፉ የሌሊት ልብሶቿ ትዝ አሏት፡፡

ከማደሪያ ክፍሏ ውጭ ዝቅ ያለው የመነኮሳቱ እርምጃ ተሰማት፡፡ አልጋዋን በግድየለሽነት አለባብሳ ከመነኮሳቱ ጋር ኮሪደሩ ላይ አብራ ተሰለፈች፡፡ ሁሉም





አንገታቸውን ደፍተው አይናቸውን ሰብረዋል፡፡ በዝግታ ወደማምለኪያ ቦታው ጉዞ ጀመሩ፡፡

ሰልፋቸው ያልተዛነፉ መሆኑን ሉቺያ ተገነዘበች፡፡ እነዚህ ሴቶች ህይወታቸውን በዚህ መንገድ ለማሳለፍ የወደዱበት መንገድ ግራ አጋብቷታል፡፡ ያማሩ ልብሶች፣ ጣፋጭ ምግቦችና የፍቅር ጨዋታን ንቀው እዚህ ተገኝተዋል፡፡ እነዚህን ነገሮች ትተው የመኖር ትርጉሙ ምንድን ነው? የማይረቡስ መመሪያዎች!

ሲስተር ሉቺያ ወደፀሎት ቤቱ ስትገባ የመነኮሳቱ አለቃ ‹‹አንገትሽን ደፍተሽ መጓዝ አለብሽ፡፡ እጅሽን ደረትሽ ላይ ማነባበሩን አትርሺ፡፡ በዝግታ ተራመጂ፡፡ ማንንም ቀና ብለሽ እንዳታይ፡፡ ማውራት አትችይም፡፡ ጆሮሽ መስማት ያለበት የአምላክን ቃል ብቻ ነው›› አሏት፡፡

‹‹እሺ እናቴ›› አለች፡፡

ለሚቀጥለው ወር የሚያገለግውን መመሪያ ሉቺያ ተቀበለች፡፡

‹‹እዚህ የሚመጡት ሰዎች ሌሎችን ለመቀላቀል ሳይሆን የሚመጡት ከአምላክ ጋር ለመቀላቀል ነው፡፡ በብቸኝነት የተሞላ መንፈሣዊ ህይወት ከአምላክ ጋር ህብረት ለመፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ የዝምታ ደንቡ ደግሞ መተማመኛችን ነው፡፡››

‹‹እሺ እናቴ››

‹‹እዚህ ስትመጪ መማር ያለብሽ ቀዳሚው ነገር ያለፈውን ነገር መርሣት ነው፡፡ ልምድሽን የቃላት ውክቢያውን እንዲሁም በውስጥሽ የተቀበሩትን ምስሎች አውጥተሽ ጣይው፡፡ ሀሊናችን በማንፃት ከራስ ወዳድነትና ምኞት መላቀቅ ይጠበቅብሻል፡፡ ባለፉት ጊዜያት ለሰራነው ጥፋት ማዘናችን ወይም መፀፀታችን ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ የአምላክን ዘለአለማዊነትና ውበት አንዴ ከተረዳነው ለራሣችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ለሰሩት ኃጢት መፀለይ አለብን፡፡››

‹‹እሺ እናቴ››

‹‹ከውስጥ ጉጉትሽ ጋር መታገል አለብሽ››

‹‹እሺ እናቴ››

‹‹እያንዳንዱ መነኩሴ በዝምታ ለብቻዋ ተገልላ ትኖራለች፡፡ በዚህም መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳለች፡፡››

# ምዕራፍ አራት

ኮሎኔል ራሞን ኢኮካ የአዳኝ ደመነፍስ አለው፡፡ ግብ ግቡን ይወደዋል፡፡ ጥልቅ እርካታ የሚሰጠው ግን መግደል ነው፡፡ አንድ ጊዜ ለወዳጁ ‹‹ግድያ ሲፈጸም እረካለሁ፡፡ ሰው፣ አጋዘን፣ ጥንቸል ቢሆንም ልዩነት የለውም፡፡ ልብ እንደ አምላክ ህይወት ስቀጥፍ እረካለሁ›› ብሎታል፡፡

ኢኮካ የጦር ሠራዊት የስለላ ባልደረባ የነበረ ሲሆን በአጭር ጊዜ ዝናን ተቀዳጅቷል፡፡ ጨካኝ፣ ደፋርና ብሩህ አዕምሮ የተላበሰ ነው፡፡ ይህ ብቃቱ ከጄኔራል ፍራንኮ ረዳቶች የአንዱን ቀልብ ለመሳብ አግዞታል፡፡

ኢኮካ የፍራንኮን ቢሮ በሴፍተናንት ማዕረግ በመቀላቀል ከሦስት አመት ባነሰ ጊዜ ኮለኔል ለመሆን በቅቷል፡፡ ፍራንኮን የሚቃወሙ ሰዎችን ለማሸበር በማለት ልዩ ሐይሉን እንዲቀላቀል ተደርጓል፡፡

በጦርነቱ ወቅት ነበር በኦፐስ ሙንዶ አባላት ተመልምሎ የተላከው፡፡ የደረሰው መልእክት፡

‹‹አንተን የምናነጋግርህ በጄኔራል ፍራንኮ መልካም ፈቃድ መሆኑን እንድታወቅ እንፈልጋለን››

‹‹እሺ ጌታዬ››

‹‹እየተከታተልንህ ነው ኮለኔል፡፡ ባየነው ነገር ተደስተናል››

‹‹አመሰግናህለሁ ጌታዬ››

‹‹ብዙ ጠላቶች አሉን፡፡ የምንሰራው ሥራ ጠቀሜታ የማይገባቸው ሰዎች አሉ፡፡››

‹‹አናው ጌታዬ››

‹‹አንዳንድ ጊዜ ጣልቃ ይገባሉ፡፡ እኛ ደግሞ ያ እንዲሆን አንፈልግም፡፡››

‹‹አይሆንም ጌታዬ››

‹‹አንተን በመሰሉ ሰዎች ላይ እምነት አለን ኮሎኔል፡፡ እንድታግባባን እስባለሁ››





‹‹አዎ ጌታዬ፡፡ እናንተን በማገልገሌ ክብር ይሰማኛል፡፡››

‹‹በጦር ውስጥ እንድትቆይ እንፈልጋለን፡፡ መቆየትህ ለእኛ ከፍተኛ ዋጋ አለው፡፡ ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ አንተን እነዚህን በመሰሉ ልዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ እንድትካፈል እንፈልጋለን፡፡››

‹‹አመሰግናለሁ ጌታዬ››

‹‹ስለዚህ ነገር ለማንም እንዳታወራ››

‹‹አላደርገውም ጌታዬ››

ከጠረጴዛው ጀርባ ያለው ሰውዬ ኢኮካን አሸበረው፡፡ እንድትፈራው የሚያደርግ ያልተገደበ ኃይል እንዳለው ያስታውቃል፡፡

በጊዜ ሒደት ኮለኔል ኢኮካ ከኦፐስ ሙንዶ የተለያዩ ተልእኮዎችን ተቀብሎ እውን አድርጓል፡፡ የሚሰጠው ተልእኮ በሙሉ አደጋ የተሞላበት ነው፡፡ እንዲሁም ፍፁም ምስጢራዊ፡፡

በአንዱ ተልእኮው ከደህና ቤተሰብ የተገኘች ቆንጆ ሴት ለመተዋወቅ በቅቷል፡፡እስከዚህ ድረስ የሴት ወዳጆቹ በጠቅላላ ሴተኛ አዳሪዎች ነበሩ፡፡ በካምፕ የተዋወቃቸውን ሴቶች ጨምሮ ሁሉም የሚያስተናግዳቸው በጭካኔ ነው፡፡

ነገር ግን ሱዛን ሴዲላ ወደተለየ አለም ከተተችው፡፡ አባቷ በማድሪድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሲሆን እናቷ ደግሞ ጠበቃ ናቸው፡፡ ሱዛን የአስራ ሰባት አመት ልጃገረድ ስትሆን ውበቷ የአምላክ እናትን ይመስላል፡፡ ራሞን ኢኮካ በህይወቱ ይችን የመሰለች ሴት ተዋውቆ አያውቅም፡፡ ልቡ እስኪጠፋ በፍቅር በነነ፡፡ ኢኮካና ቤተሰቦቿ በማያውቁት ሁኔታ እሷም ከልቧ ወደደችው፡፡

ከጫጉላ ሽርሽራቸው እንስቶ ኢኮካ ሌላ ሴት ጋር አልሔደም፡፡ ፍቅርን ልብ የሚያጠፋ ስሜት ተዋህደው በህይወቱ ያላገኘውን ደስታ ሰጡት፡፡

ከተጋቡ ከሦስት ወራት በኋላ ሱዛን ማርገዟን ነገረችው፡፡ የኢኮካ ደስታ ገደቡን አለፈ፡፡ ደስታቸውን ከፍ ለማድረግ በባስክ ግዛት ወደምትገኘው ትንሿ መንደር ካስቲላ ባንካ ተዛወረ፡፡ በብሔረተኞቹና በሪፐብሊካኖች መካከል አስከፊው ጦርነት የፈነዳው በ1936 ነበር፡፡

በአንድ ድንቅ የእሁድ ጠዋት ኢኮካና ቆንጆዋ ሙሽራ በመንደራቸው

# ምዕራፍ ስድስት
# ላስናቫስ ዴል ማርኩዌዝ
# ስፔን 1950

የአምስት አመት ልጅ ነበረች። የልጅነት ትዝታዋ የተሞላው ወደ እናቷ አልጋ በሚገቡና በሚወጡ ርቃናቸውን የተሞሉ እንግዳ ሰዎች ነው።

እናቷ የምታስረዳት "አጐቶችሽ በመሆናቸው አክብሮት ልትሰጪያቸው ይገባል" በማለት ነው።

ሰዎቹ ጨካኝና ጨፍጋጋ ናቸው። አንድ ምሽት፣ ሳምንት ወይም ወር ቆይተው ይሰወ ራሉ። ዶሎሬስ ፒኔሮ አንዱ እንደ ወጣ በቅፅበት ሌላ ወንድ ትተካለች።

እህቷ ቆንጆ ስትሆን ግራቤላም የእሷን ውበት ወርሳለች። አመታት ሲያልፉ የዶሎሬስፒኔሮ ሰውነት እና ውበት ጠወለገ። የአልጋ አጣማጅም አጣች፤ ፍቅር መስራትን በሚገባ ስለምታው ቅበት በዚሁ በመታገዝ አብሯት የሚዘልቅ አጋር ብትመኝም አልተሳካላትም።

የግራቤላ እናት ዘወትር የሚጐበኛት አንድ ሰው ብቻ ልጇን እንዲቀርብ ፈቅዳለታለች። ያ ሰው የልጇ አባት ነው። አባቷ ወጣት መልከ መልካም መካኒክ ሲሆን ዶሎሮስ እንዲያገባት ብትጠ ይቀውም ፈቃደኛ አልሆነም። ማርገዟን ስትነግረው ላይመለስ ወጥቶ ቀረ።

ዶሎሬስ በቀልን ልጇ ላይ ማሳረፍ ጀመረች። ዘወትር ትገርፋታለች ትጮህባታለች። "እንደ አባትሽ ደደብ ነሽ።" እያለች ሞራሏን ታደቀዋለች። ከመጮህ በስተቀር ከእናቱ የምታመ ልክበት ምንም መንገድ አልነበራትም። ግራቤላ ዘወትር ከአልጋዋ ስትነሣ" አምላኬ እባክህ ዛሬ እናቴ እንዳትመታኝ አድርግ" በማለት ትፀልያለች።

"እባክህ አምላኬ እናቴን ዛሬ ደስተኛ አድርጋት"

"እባክህ አምላኬ እናቴ ዛሬ እወድሻለሁ እንድትለኝ አድርግ"

እናቷ ካልመታቻት ቀኑን ሙሉ ዘግታት ትውላለች። ግራቤላ የራሷን





ምግብ ታዘጋጀለች፤ ልብሶቿንም ታጥባለች። ምሳዋን ይዛ ትምህርት ቤት ስትሔድ ለአስተማሪዎቿ "እናቴ ዛሬ ይህን ምግብ ሰርታልኛለች" ትላቸዋለች። ልብሴን ሰፋችልኝ፣ ነገ ስእል ለማየት እንሔዳለን ስትላቸው የአስተማሪዎቹ ልብ በሐዘን ይደማል።

ላስ ናቫስ ዴል ማርኩዌዝ ከአቪላ አንድ ሰአት ያህልየምትርቅ ትንሽ ከተማ ነች። እያንዳንዱ ሰው በደንብ ይተዋወቃል። የደሌሬስ ፒኔር አኗኗር አሳፋሪ ነበር። ነውብራቁም ግራቤላ ላይ አርፏል። ጐረቤቶቿ ልጆቻቸው ከግራቤላ ጋር እንዲጫወቱ አይፈልጉም። ግራቤላ በትምህርት ቤት ውስጥ ምንም ጓደኛ አልነበራትም። ብሩህ አእምሮ ያላት ተማሪ ብትሆንም ዘወትር ውጤቷ ዝቅተኛ ነበር። ስለሚደክማት ትምህርቱ ላይ ማተኮር አልቻለችም።

አስተማሪዎቿ በጊዜ እንድትኛ ይመክሯታል። ድካሟ አርፍዳ በመተኛቷ ብቻ የመጣ አይደለም። እሷና እናቷ ሁለት ክፍል ባላት ጠባብ ቤት አብረው ይኖራሉ። እሷ የምትተኛበት ክፍል በስስ መጋረጃ የተከፈለ በመሆኑ ሁሉንም ነገር ትመለከታለች። ሌሊት ስለሚያቃትት ድምፅ ለአስተማሪዎቿ ነግራቸዋለች።

ግራቬላ የትምህርት ውጤቱን የያዘውን ሪፖርት ካርድ ለእናቷ ስታሳያት ታምባርቅባታለች። ይህን ውጤት ያገኘሽው ደደብ ስለሆንሽ ነው ትላታለች። እሷም ነገሩን በመረዳት ላለማልቀስ በእጅጉ ትጥራለች።

ግራቬላ ከትምህርት ቤት ስትመለስ በምታየው ነገር ሁሉ ትመሰጣለች። ግራቬላ አጫዋች ጓደኞቿን በአእምሮዋ ስላቸዋለች። ቆንጆ ሴቶችና መልከ መልካም ወጣቶች ሲሆኑ ወደ ተለያዩ ዝግጅቶች ሲጋብዟት ታልማለች። ትሁትና ተወዳጅም ናቸው። አንዳንዴም በሐሳቧ ታናግራቸዋለች።

እሁድ ጠዋት ቀደም ብላ በመነሣት ንፁህ ልብስ ለብሣ እናቷን ላለመቀስቀስ በመጠንቀቅ ወደ ሳን ጁአን ባቲስታ ቤተክርስቲያን ትሔዳለች። አባት ፔሬዝም ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት ይሰብካሉ።

ቄስ ፔሬዝ ማራኪ እና በአርባዎቹ ውስጥ የሚገኙ አባት ናቸው። ሁሉንም ሰው በእኩል አይን ይመለከታሉ። በመንደሯም ምስጢር የሚባል ነገር የለም። ቄስ ፔሬዝ ግራቬላ ዘወትር ወደ ቤተክርስቲያን በመሔዷ ለይተው ያውቋታል። የእናቷንም ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ቤቱ ለታዳጊ ህፃን እንደማይሆን ቢያውቁም ማንም ምንም ሊያደርግ አይችልም። ግራቬላ ቀና እና የተረጋጋች ስትሆን በቤት ውስጥ ስለምታሳልፈው ህይወት አማራ ወይም ለማንም ተናግራ አታውቅም።

አላመነቻትም። እናቷን እየተጠቀመባት እንደሆነ አውቃለች።" ነገር ግን መቃወም አትችልም። የእናቷ ቁጣ ያስፈራታል። አንድ ጊዜ ቢላዋ ይዛ አባራታለች።

አንድ እሁድ ግራቬላ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሔድ እየተዘጋጀች ነው። እናቷ ጉዳይ ገጥሟት በጠዋት ወጥታ ሔዳለች። ልብሷን እየቀየረች ሳለ መርከበኛው እርቃኑን ብቅ አለባት።

"እናትሽ የት ናት? ሲል ጠየቃት

"በጠዋት ነው የሔደችው"

መርከበኛው የግራቬላን እርቃን የሚታይ ገላ እያጠና ነው።

"በእውነት ውብ ነሽ" አላት በዝግታ።

ግራቬላ ፊቷ ቀላ። ምን ማድረግ እንዳለባት ታውቃለች። ልብሷን በፍጥነት ለብሳ ውልቅ ማለት። ነገር ግን ደንዝዛ ቀረች። አይኗ እያየ ብልቱ እየተገተረ መጣ። እናቷ የምታሰማው ድምፅ ጆሮዋ ላይ አቃጨለ።

መርከበኛው ተረጋግቶ "ገና ልጅ ነሽ ልብስሽን ልበሺና ውጪ" አላት።

ግራቬላ ተንቀሳቀሰች። ወደ እሱ ተጠጋች። እጇን ወገቡ ላይ ጠምጥማ ወንድነቱን ከሰውነቷ ጋር አጣበቀችው። አቃሰተች። ምስጢሩ ምን እንደሆነ አወቀች። በደንብ አስደሰታት። ሰዎች በዚህ ነገር ለምን እንደሚደሰቱና የህይወታቸው ጣዕም አድርገው እንደሚወስዱት ገባት።

"ምን እያደረጋችሁ ነው?"

ድምፁ የዶሴሬስ ጩኸት ነበር። ለጊዜው ሁሉም ነገር ጥሪው ብሎ ደረቀ። ደሎሮስ ፒዌሮ አልጋው አጠገብ ደንዝዛ ቆማለች። አይኗን ማመን አቅቷታል።

ግራቬላ እናቷን እያየች መናገር አቃታት። የእናቷ አይን በቁጣ እየነደደ ነው።

"አንቺ ሸርሙጣ" ስትል አንባረቀችባት።

"እማማ . . . እባክሽ"

ዶሴሬስ ግዙፍ የብር መተርኮሻ አንስታ ልጇ አናት ላይ አሳረፈችው።

ግራቬላ የምታስታውሰው የመጨረሻ ነገር ይህ ብቻ ነው።





በሰዎች የተሞላ ሆስፒታል ውስጥ ራሷን አገኘችው። ነርሶች ከወዲያ ወዲህ ታማሚዎችን ለመርዳት ይዋከባሉ።

የግራቬላ ጭንቅላት በህመም ይወቅራታል። በተንቀሳቀሰች ቁጥር ውስጧ ይነዳል። ተኝታ የሌሎችን ጩኸት ታዳምጣለች።

"ደህና" አላት"። "በመጨረሻ ነቃሽ"

"የት ነው ያለሁት?" ስትናገር እየተሰቃየች ነው።

"አቪላ በሚገኝ የበጐ አድራጐት ሆስፒታል ውስጥ ነሽ። ትላንት ነው የመጣሽው። በአስጊ ሁኔታ ውስጥ ነበርሽ። ግንባርሽን መስፋት ነበረብን" ዶክተሩ ቆንጆ በመሆንሽ ጠባሳ እንዲኖርብሽ ስላልፈለገ እራሱ ነው የሰፋሽ።

ተሳስቷል ስትል ግራቬላ አሰበች። ህይወቴን ሙሉ አብሮኝ የሚኖር ጠባሳ ይገኛለሁ።

በሁለተኛው ቀን ቄስ ፔሬዝ ሊመለከቷት መጡ። ውቧ ወጣት ተጋድማ ሲመለከቷት ቁሱ ልባቸው ቀለጠ። በእሷ ላይ የደረሰው ገጠመኝ የላስ ናቫስ ዴል ማርኩዌዝ ቅሬት ነው ሲሉ አሰቡ። ነገር ግን ማንም ምንም ሊያደርግ አይችልም። እናቷ ልጇ የተጐዳችው ወድቃ መሆኑን ለፖሊሶች ተናግራለች።

"ደህና ነሽ?" ሲሉ ቄስ ፔሬዝ ጠየቋት። ግራቬላ አንገቷን በመነቅነቅ ምላሽ ስትሰጣቸው ውስጧ በህመም ነደደ።

"ፖሊሶች ሊጠይቁሽ ይችላሉ። ለእነሱ እንድነግራቸው የምትፈልጊው ነገር አለ?"

ዝምታዋ ረዘም ያለ ነበር። በመጨረሻም "አደጋ ደርሶብኝ ነው" አለች።

አይኗ ላይ የሚነበበው መከራ ነው። "ገባኝ" አሏት ሊነግሯት የፈለገው ነገር ከህመም የባሰ ነው። "ግራቬላ ከእናትሽ ጋር ተነጋግሬ ነበር"።

ግራቬላ አውቃው ነበር። "በድጋሚ ወደ ቤት መሔድ አልችልም . . . እችላለሁ እንዴ?

"አትችይም። ስለጉዳዩ ተነጋግረናል" አሏት ቄስ ፔሬዝ የግራቬላን እጅ ይዘው። "ነገ መጥቼ አይሻለሁ።"

"አመሰግናለሁ አባቴ"

ቄስ ፔሬዝ እንደወጡ ግራቤላ በተጋደመችበት ፀሎት አደረሰች "አምላኪ እንድሞት እርዳኝ:: መኖር አልፈልግም"::

አሁን የምትሔድበት ቦታ የላትም:: ቤቷን በፍፁም ደግማ አታየውም:: ትምህርት ቤቷንና አስተማሪዎቿንም በድጋሚ አታያቸውም:: በአለም ላይ የቀራት ምንም ነገር የለም::

ነርሷ አጠገቧ ቆማ "የምትፈልጊው ነገር አለ?" አለቻት ግራቤላ ቀና ብላ አይታት ምን እንደምትናገር ጠፋት::

በሚቀጥለው ቀን ዶክተሩ በድጋሚ መጣ::

"ጥሩ ዜና ይዤልሽ መጥቻለሁ" አላት በደስታ:: "አሁን ጤነኛ በመሆንሽ መውጣት ትችያለሽ::" ነገሩ ውሸት ነው:: የቀረው ንግግሩ ደግሞ እውነት ነው:: "አልጋውን እንፈልገዋለን::"

ለመሔድ ነፃ ነች ግን የት ትሔዳለች?

ከአንድ ሰአት በኋላ ቄስ ፔሬዝ ሲመጡ ሌላ ቄስ አብረዋቸው ነበሩ::

"እኚህ ቄስ ቤሬንዶ ናቸው:: የረጅም ጊዜ ወዳጄ ናቸው::" ግራቤላ ቀና ብላ አይታቸው "አባቴ" አለች::

ትክክል ነው ሲሉ ቄስ ቤሬንዶ አሰቡ:: ቆንጆ ናት::

ቄስ ፔሬዝ በግራቤላ ላይ የደረሰውን በጠቅላላ ነግረዋቸዋል:: "በልጅቷ ገፅታ ላይ የተመሰቃቀለ ህይወቷን የሚያንፀባርቅ ነገር እመለከታለሁ" ብለው ገምተው ነበር:: ነገር ግን በወጣቷ ፊት ላይ የሚነበብ ምንም ነገር የለም::

"መጥፎ ጊዜ በማሳለፍሽ አዝናለሁ" አሏት ቄስ ቤሬንዶ:: ቃላቱ ጥልቅ ትርጉም ነበረው::

ቄስ ፔሬዝ "ግራቤላ ወደ ላስ ናቫስ ዴል ማርኩዌዚ መመለስ አለብኝ:: አንችን ለቄስ ቤሬንዶ አደራ ሰጥቼሻለሁ::"

ግራቤላ በድንገተኛ ጭንቀት ተዋጠች:: ከቤቱ ጋር የምትገናኝበት የመጨረሻው መስመር መበጠሱ ታወቃት:: "አትሒድ" ስትል ተማፀነችው::

ቄስ ፔሬዝ እጇን አጥብቀው ያዟት::" ብቸኝነት እንደሚሰማሽ አውቃለሁ::"





አላት ቀዝቀዝ ብሎ:: "ነገር ግን በቻሽን አይደለሽም:: እመኚኝ ልጄ::"

አንድ ነርስ የተጠቀለለ ነገር ይዛ ግራቤላን ተጠግታ ሰጠቻት:: እነዚህ ያንቺ ልብሶች ናቸው:: አሁኑኑ መልቀቅ እንዳለብሽ የምነግርሽ በማዘን ነው::

ጥልቅ የሆነ ግራ መጋባት ዋጣት:: "አሁን?" ሁለቱ ቄሶች እርስ በእርሳቸው ተያዩ::

"ለምን ልብስሽን ለብሰሽ ከእኔ ጋር አትወጣም?" አሏት ቄስ ቤሬንዶ:: "እንነጋገራለን::"

ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ቄስ ቤሬንዶ እየረዷት ግራቤላ ደማቅ ብርሃን የሞላውን ከተማ ተቀላቀለች::

ቄስ ቤሬንዶ ቢሮአቸው ውስጥ ከግራቤላ ጋር በተቀመጡበት ወቅት "ቄስ ፔሬዝ መሔጃ እንደሌለሽ ነግረውኛል" አላት::

ግራቤላ በአዎንታ ራሷን ነቀነቀች::

"ዘመድ የለሽም?"

"እናቴ በቻ ነች" አለች ለመናገር እየከበዳት::

"አንቺ ዘወትር ቤተክርስቲያን እንደምትሔጂ ቄስ ፔሬዝ ነግረውኛል::"

"አዎ" አለች መንደሯን ደግማ እንደማታይ እያሰበች:: ግራቤላ የእሁድ ፀሎቱ ትዝ አላት::

"ግራቤላ ገዳም መግባትን አስበሽው ታውቂያለሽ?"

"በፍፁም" አለች በሐሳቡ በመገረም::

"እዚህ አቪላ አንድ ገዳም አለ:: የሴቶች ገዳም:: እዛ አንቺን ይንከባከቡሻል።"

"አላውቅም" አለች ሐሳቡ እያስፈራት::

"ለሁሉም ሰው የተፈቀደ አይደለም" አሏት ቄስ ቤሬንዶ:: የማስጠንቅቅሽ ነገር ቢኖር ጥብቅ መሆኑን ነው:: አንዴ በሩን አልፈሽ ከገባሽ ተመልሰሽ እንደማትወጪ ለእየሱስ ቃል ትገቢያለሽ::

ግራቬላ በተመሰቃቀለ ሐሳብ ተውጣ በመስኮት አሻግራ ውጪውን ትመለከታለች። ራሷን ከአለም አግልላ መቀመጡ አስፈሪ ሆነባት። እስር ቤት መግባት መስሎ ታያት። በሌላ በኩል አለም ምን ትሰጣታለች? ስቃይና መገለል። ዘወትር ራሷን ለማጥፋት ታስባለች። እድሉ ከምስጢሯ ያወጣት ይሆናል። ቄስ ፔሬዝ "ጉዳዩን ለእንቺ እተወዋለሁ የእኔ ልጅ። ከወደድሽው ከእናት ፕሪየርስ ጋር አገናኝሻለሁ።"

ግራቬላ አንገቷን በመነቅነቅ። "ደህና" አለች።

ኃላፊዋ መነኩሴዋ የወጣቷን ፊት በጥንቃቄ ተመለከቱት። ትላንት ምሽት ከብዙ አመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን ሰማችው። ወጣት ልጃገረድ ወደ እንቺ ትመጣለች ጠብቂያት።

"የእኔ ውድ ስንት አመትሽ ነው?"

"አስራ አራት"

አድጋለች። በአራተኛው ክፍለ ዘመን ጳጳሱ አስራ ሁለት አመት የሞላት ሴት ገዳም እንድትገባ ደንግገዋል።

"ፈርቻለሁ" አለቻቸው ግራቬላ ለእናት ፕራየርስ። "ፈርቻለሁ። ቃሉ በቴቲና አእምሮ ውስጥ ደወለ። ፈርቻለሁ።

ነገሩ የሆነው ከብዙ አመት በፊት ነው። ለነፍስ አባቷ ስትናገር። "ለዚህ ነገር የተጠራሁ አይመስለኝም አባቴ። ፈርቻለሁ።

"ቤቲና ለመጀመሪያ ጉዜ ከአምላክ ጋር መገናኘት ይረብሻል። እናም ህይወትሽን ለእሱ አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ ነው።"

"ጥሪውን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?" አለች ቤቲና በመገረም። ለሐይማኖት ገድ አለነበራትም። እንደ ወጣት ሴቶች ቤተክርስቲያንና የሰንበት ትምህርት አትከታተልም። ጭፈራ፣ ወንዶችና ቆንጆ ልብስ መልበስ ያስደስታት ነበር። ማድሪድ ካሉ አማኞች መነኩሴ ለመሆን ምርጫ ቢደረግ እንኳ ቤቲና መጨረሻ ከመሆን አታመልጥም ነበር። አስራ ዘጠኝ አመት ሲሞላት ነገሮች መልካቸውን ቀየሩ።

ድምፁ ወደ እሷ ሲመጣ ተኝታ ነበር "ቤቲና ተነሽና ወደ ውጭ ውጪ።"

መብራት እየፈራች ተነስታ ተቀመጠች። አልጋዋ አጠገብ ያለውን





አበራችው። ብቻዋን ነበረች። ያልተለመደ ህልም ነው፡

ነገር ግን ድምፁ እውነተኛ ነበር። ልትተኛ ብትሞክርም ነገሩን መርሣት አልቻለችም።

ብዙ ካመነታች በኋላ ተነስታ ወደታች ወረደች። ሰው ሁሉ ተኝቷል። ሰውነቷን ፍርሀት እንደዋጠው የወጥ ቤቱን በር ከፍታ ገባች። በጨለማው ውስጥ የምትታየው ጨረቃ ብርሃን አሮጌው ፍሪጅ ላይ አርፏል።

ቤቲና በድንገት እዚህ የመጣችው ለምን እንደሆነ ታወሳት። እየመነታች ወደ ፍሪጁ ተጠግታ ከፈተችው። ፍሪጁ ውስጥ የሶስት አመት ወንድሙ ራሱን ስቶ አገኘችው።

ይህ የመጀመሪያው አጋጣሚ ነበር። እየቆየ ሲሄድ ነገሮቹ ለቤቲና የተለመዱ እየሆኑ መጡ። ከወር በኋላ ሌላ ነገር ተከሰተ። በእንቅልፍ ልቧ አንድ ድምፅ "ከእሳቱ ውጪ" አላት።

ልቧ እየደለቀ ነቅታ ተቀመጠች። ሁሉም ነገር ሰላም ነው። የወላጆቿ እና የወንድሟ መኝታ ቤት ሰላም ነው።

ቤቲና ደደብ ነኝ ስትል አሰበች። ነገርየው ህልም ነው፤ ልክ አልጋዋ ላይ እንደወጣች ቤቱ በፍንዳታ ጋየ። እሷና ቤተሰቦቿ ከአደጋው አመለጡ። ምድር ቤት ያለው ማሞቂያ እንደፈነዳ የእሳት አደጋ መከላከያ ሰራተኛው ነገራቸው።

ከሶስት ሳምንት በኋላ ሌላው አጋጣሚ ተከሰተ። አሁን ነገሩ ህልም አይደለም።

ቤቲና መናፈሻ ውስጥ ተቀምጣ መፅሐፍ ስታነብ እንግዳ የሆነ ገፅታ ያለው ሰው አተኩሮ እያያት አለፈ። ገፅታውን ልትረሳው አልቻለችም።

ከሶስት ቀን በኋላ አንድ መስሪያ ቤት ህንፃ ውስጥ ገብታ ሊፍት ስትጠብቅ የተመለከተችው የሊፍቱ ሰራተኛ መናፈሻው ውስጥ ያየችው ነበር። ቤቲና በፍርሀት ወደ ኋላ ተመለሰች። በዛው ቅፅበት የሊፍቱ በር ተዘግቶ ወደላይ ጉዞ ጀመረ። ወዲያውኑ ሊፍቱ ተከስክሶ ውስጡ የነበሩት ሰዎች በጠቅላላ አለቁ፡

በሚቀጥለው እሁድ ቤቲና ወደ ቤተክርስቲያን ሔደች።

"ውድ አምላክ በእኔ ላይ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ አላወኩም። እናም ፈርቻለሁ። እባክህ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ነግረህ ምራኝ"። ብላ ፀለየች።

# ምዕራፍ ሰባት

ሉቺያ ካርማይን ከሜጋንና ቴሬዛ ጋር ሆና በጉዳናው ላይ ስትጓዝ የተሰማት ስሜት ድንቅ ነበር። በድጋሚ የሴት አልባሳት መጐናፀፏ ስሜቷን አሙቆታል። የሰዎችንም ትኩረት አግኝታለች። የለበሰችን አዲስ ልብስ ስላልተላመዱት ሲራመዱ የተራበሹ ይመስላሉ። በራስ መተማመናቸው ገና አልዳበረም። ከሌላ አለም የመጡ መስሉ ተሰምቷቸዋል። ይህ ቦታ ለእኛ አይሆንም ስትል ሉቺያ አሰበች። አለባበሳቸው "ያዙን" የሚል ይመስላል።

ከሴቶቹ መካከል ምቾት ያለተሰማቸው ሲስተር ቴሬዛ ናቸው። በገዳሙ ያሳለፉት ሰላሳ አመት የማያዩትን አለም እውነት እንዳይመስላቸው አድርጓቸዋል። ለእሳቸው ምቹው ቦታ ገዳሙ ብቻ ነው።

በመንገዱ መካከል ሰዎች አተኩረው እንደሚመለከቱት ልብ ያለችው ሜጋን ናት። ይህን አለም ለረጅም ጊዜ ስለዘነጋችው ወንዶችን መመልከት ምን ስሜት እንደሚሰጥ ጠፍቶባታል። አንዱ አይቷት ፈገግታ ሲመግባት ሀፍረት ዋጣት፤ ውስጧ የተቀበረውን ስሜት አጫሩባት። ከአመታት በኋላ ሴትነቷ ትዝ አላት።

ቀደም ብለው ባለፉት የቡና ቤት በራፍ ደግመው ሲያልፉ ሙዚቃው መንገዱን ሞልቶት አደመጡ። ፍራየር ካሪሎ ምን ብሎ ነበር የጠራው? ሮክኤንድ ሮል። በወጣቶች ዘንድ ተወዳጅ ነው። የሆነ ነገር ረበሻት። በድንገት ምን እንደሆነ ተገለፀላት። በሲኒማ ቤቱ በኩል ሲያልፍ ፍራየር "በዚህ ዘመን የሚታዩት ፊልሞች አሳፋሪዎች ናቸው" ነበር ያለው።

የሜጋን ልብ በፍጥነት መደለቅ ጀመረ። ፍራየር ካሪሎ ለሀያ አመት ኑሮው በገዳም ውስጥ ከነበረ እንዴት ስለሮክ ሙዚቃና ሲኒማ ሊያውቅ ቻለ? የሆነ የተሳሳተ ነገር አለ።

በፍጥነት ወደ ሉቺያና ቶሬዛ ዛራ "በፍጥነት ወደ ሱቁ መመለስ አለብን" አለቻቸው።

ሜጋን ፊቷን አዙራ ስትሮጥ ተመልክተው እነሱም ተከተሏት።

ግራሺላ ወለሉ ላይ ተጋድማ ራሷን ነፃ ለማውጣት እየታገለች ነበር። ከካሪሎ ጋር ግብግብ ገጥማለች።





"የማትረቢ አሁን ትታገያለሽ" አላት በብስጭት። ድምፅ ሰምቶ ቀና አለ። በሱቁ ውስጥ ከተደረደሩት የሴት ታኮ ጫማዎች አንዱ ወደ ጭንቅላቱ ሲጠጋ ተመለከተ። የሚያስታውሰው የመጨረሻው ነገር ይህ ነው።

ሜጋን የምትርበተበተውን ግራሼላን ደግፋ አነሳቻት። "ሽሽ! ሁሉም ነገር ደህና ነው። ከአሁን በኋላ አያስቸግርሽም"

ግራሺላ ለመናገር ረጅም ደቂቃ ወሰደባት። "አሁን የተደረገው በእኔ ጥፋት አይደለም" አለች በጥፋተኛ ስሜት።

ሉቺያና ቴሬዛ ወደ ሱቁ ገቡ። ሉቺያ ዙሪያውን ተመልክታ ነገሩ ገባት።

"ዲቃላ"

መሬት ላይ ራሱን ስቶ ግማሽ እርቃኑን የተጋደመውን ሰው ተመለከተችው። ሌሎቹ እየተ መለከቷት ቀበቶ አንስታ እጁን ከብረት ጋር አሰረችው። "እግሩን እሰሪው" አለቻት ሜጋንን።

ሜጋን ስራዋን ጀመረች።

በመጨረሻ ሉቺያ በእርካታ ቆመች። "ይኸው ነው። ረፋድ ላይ ሱቃቸውን ሲከፍቱ እዚህ ምን ይሰራ እንደነበር ማስረዳት ይችላሉ።" አለቻት ግራሼላን አተኩራ እያየቻት። "ደህና ነሽ?" በማለት ጠየቀቻት።

"እኔ . . . አዎ . . ." አለች ፈገግ ለማለት እየሞከረች።

"አሁን ብንወጣ ጥሩ ነው።" አለች ሜጋን። "በፍጥነት ልበሺ" ለመውጣት ሲዘጋጁ ሉቺያ" ትንሽ ጠብቁኝ አለቻቸው ወደ ገንዘብ መቀበያ ሔዳ ቁልፉን ከፈተችው። ጥቂት የመቶ ብር ኖቶች አሉ። ቦርሣ አንስታ ገንዘቡን ከተተችው። በቴሬዛ ፊት ላይ "አይሆንም የሚል ነገር አነበበች።

ሉቺያ "በዚህ መንገድ እይው ሲስተር። እግዚአብሔር ይህንን ገንዘብ እንድንወስድ ባይፈልግ ኖሮ እዚህ አያስቀምጠውም ነበር።"

አንድ ቡና ቤት ውስጥ ተቀምጠው መወያየት ጀመሩ። ሲስተር ቴሬዛ ነበረች ተናጋሪዋ። "በቻልነው ፍጥነት መስቀሉን ሜንዳቪያ ወደሚገኘው ገዳም ማድረስ አለብን"። የሁላችንም ደህንነት የሚጠበቀው እዛ ብቻ ነው።"

ለእኔ ግን አይሆንም ስትል ሉቺያ አሰበች። የእኔ ደህንነት ያለው ስዊስ

ባንክ ነው። ነገር ግን የሚቀድመው ይቀድማል። መስቀሉን እጂ ማስገባት አለብኝ።

"የሚንዳቪ.ያ ገዳም የሚገኘው ከዚህ በሰሜን በኩል ነው አይደለም?"

"አዎ"

"ሰዎቹ በሁሉም ከተማ እኛን መፈለጋቸውን አያቆሙም። ሌሊቱን ተራራው ላይ ማሳለፍ አለብን"

ብትጮህ እንኳን የሚሰማት አልነበረም።

አስተናጋጁ የምግብ ዝርዝር አመጣላቸው። ሲስተሮቹ ግን ግራ በመጋባት እርስ በእርሳቸው ተያዩ። ሉቺያ ነገሩ በድንገት ገባት። ምግብ ከመረጡ አመታት አስቆጥረዋል። የገዳም አመጋገባቸው የተገደበ ነው።

ሲስተር ቱሬዛ ቀደም ብለው "ቡናና ዳቦ እፈልጋለሁ" አሉ ሜጋን "ረጅም መንገድ ስለምንጓዝ እንደ እንቁላል ያለ ጠንካራ ምግብ ያስፈልገናል።" አለች።

ሉቺያ በመገረም ተመለከተቻት። ልትጠነቀቃት ተመለከተቻት። ልትጠነቀቃት የምትገባው እሷን መሆኑ ገባት። ጮክ ብላ" ሲስተር ሜጋን ልክ ነች። እኔ ልዘዝላችሁ" አለች ሉቺያ።

የተቆረጠ ብርቱካን፣ ድንች፣ የተጠቀለለ ስጋና በስኳር በደንብ የበሰለ አትክልት እና ቡና አዘዘችላቸው።

"ቸኩለናል" አለችው አስተናጋጁን።

የቀኑ ፀሎት አስር ተኩል ላይ ስለሚያበቃ ከተማዋ በድንገት ነፍስ ትዘራለች። ያ ነገር ከመፈጠሩ በፊት ከተማዋን ለቀው መውጣት አለባቸው።

ምግቡ ሲቀርብ ሲስተሮቹ እርስ በእርሳቸው ተያዩ።

"እራሳችሁን እርዱ" አለቻቸው ሉቺያ።

መጀመሪያ በማመንታት ቀጥሎ በችኮላ ተመገቡ። የጥፋተኝነት ስሜት ቢይዛቸውም መብላቱን አላቆሙም።

ችግር የገጠማቸው ሲስተር ቴሬዛ ብቻ ናቸው። አንድ ጊዜ ከጐረሱ በኋላ "አልችልም። ይህ እጅ መስጠት ነው" አሉ።





ሜጋን" ሲስተር ወደገዳሙ መመለስ ይፈልጋሉ አይደል? ስለዚህ እንዲጠነክሩ መመገብ አለብዎት።

"እበላለሁ ነገር ግን እንደሚያስደስተኝ ቃል እገባልሻለሁ" አሏት። ሉቺያ አተኩራ እያየቻቸው ጥሩ ነው ብሉ" አለች።

ከጨረሱ በኋላ ሉቺያ ሒሳባቸውን ከፈለችና ወጡ። መንገዱ ህይወት እየዘራ ነው። ሱቆቹም እየተከፈቱ ነው። "አሁን ሚጉዌል ካሪሉን አግኝተውት ይሆናል" ስትል ሉቺያ አሰበች።

ሉቹያ እና ቴሬዛ ከከተማ እስኪወጡ ድረስ ትዕግስት አጥተዋል። ግራቬላና ሜጋን ደግሞ ዝግ ብለው ነው የሚራመዱት። የሚያዩት ነገር በጠቅላላ አስደንቋቸዋል።

ከከተማው ጫፍ ወደ ሚገኘው ሸለቆ ሲደርሱ ሉቺያ እፎይ አለች። የሰሜን አቅጣጫውን ይዘው ጋራውን ተያያዙት። ሲስተር ቴሬዛን ላግዝሽ ልትላት አሰበች እና ተወችው። ይህን ማለቷ በአሮጊቷ ላይ ጥርጣሬ ሊያሳድር ይችላል።

ተራራው አናት ላይ የሚገኝ በዛፍ የተከበበ ገላጣ ቦታ ሲደርሱ ሉቺያ "ምሽቱን እዚህ ማሳለፍ እንችላለን ሲነጋ ሜንዲቪ.ያ ወደ ማገኘው ገዳም እንሔዳለን።

ሌሎቹ አመኔታ ጥለውባት በአዎንታ አንገታቸውን ነቀነቁ። ፀሐይዋ ቀስ በቀስ ጠለቀችና በመጨረሻ ምሽቱ መጣ።

ሴቶቹ አንድ በአንድ ሳሩ ላይ ተጋደሙ።

ሉቺያ በገዘምታ ተጋድማ በቀስታ እየተነፈሰች ታዳምጣለች። እንቅልፍ እስኪወስዳቸው እየጠበቀች ነው። እነሱ ሲተኙ እሷ ጉዞዋን ትጀምራለች።

ሲስተር ቴሬዛ ለመተኛት ተቸግረዋል። በሲስተሮች ተከበውኮከብ እየቆጠሩ መተኛት እንግዳ ሆኖባቸዋል። ስማቸውን ገፅታቸውን ተዋውቀዋል። ይህን የተከለከለ እውቀት በመገበየታቸው "አምላክ ይቀጣኛል" ብለው አሰቡ።

ሲስተር ሜጋንም በተመሳሳይ ለመተኛት ተቸግራለች። የቀኑ ትዕይንት እስካሁን ያስደንቃታል። ፍራየር አጭበርባሪ መሆኑን እንዴት ላውቅ ቻልኩ? በማለት ተገረመች። ሲስተር ግራቬላ ላማዳን ጀግንነቱን ከየት ነው ያገኙሁት? ስትል በፈገግታ አሰበች። ሐጢያት ቢሆንም ነገሩ ገርሟታል።

ግራሺላ የገጠማት ነገር ስላስበረገጋት እንቅልፍ ወስዷታል፡፡ አስፈሪ ህልም ያወራጫታል፡፡

ሉቺያ በበኩሏ ተረጋግታ እየጠበቀች ነው፡፡ ለሁለት ሰዓት ያህል ከጠበቀች በኋላ በዝግታ ወደ ሲስተር ቴሬዛ ተጠጋች፡፡ እቃውን ጠልፋ ለመሰወር አሰባለች፡፡

ጨለማውን ተገን አድርጋ ሲስተር ቴሬዛ አጠገብ ስትደርስ ተንበርክከው ሲፀልዩ አየቻቸው፡፡ በብስጭት ወደ ኋላ ተመለሰች፡፡

ሉቺያ በድጋሚ ተጋድማ ራሷን በትዕግስት እንዲጠብቅ ነገረችው፡፡ ሴሲቱን በሙሉ ስለማይፀልዩ በሆነ ሰዓት ላይ ይተኛሉ፡፡

ሉቺያ እቅድ አወጣች፡፡ ከሱቁ የወሰደችው ገንዘብ ማድሪድ ለመድረስ በቂዋ ነው፡፡ እዛ ከደረሰች በኋላ ደላላ ማግኘት አያቅታትም፡፡ የወርቅ መስቀሉን በቀላሉ መሸጥ ትችላለች፡፡ ደላላው መስረቁን ቢጠረጥር ችግር አይኖረውም፡፡ መግዛት የሚፈልጉ ብዙ ደንበኞች ይኖሩታል፡፡

በሐሳቧ የምትሸጥበትን ገንዘብ አወጣች አወረደች፡፡ ከመሸጧ በፊት ግን ፓስፖርት ለማግኘት የወርቅ መስቀሉን መደራደሪያ ልታደርገው አሰበች፡፡ ድርድሩ ተጠናቀቀ፡፡ አባቷ "በህይወትሽ ካጠፋሽው ገንዘብ አስር እጥፍ የሚበልጥ ገንዘብ እዛ አለ" ያላትን አስታወሰች፡፡ አይኗ መከደን ጀመረ አድካሚ ቀን ነበር፡፡ እያንቀላፋች በአቅራቢያዋ ካለ ቤተ ክርስቲያን የደወል ድምጽ ሰማች፡፡ ውስጧን ትዝታ ሞላው ሌላ ቦታ ሌላ ጊዜ . . . .





# ምዕራፍ ስምንት
# ታርሚና ሲሲሊ 1968

ታርማናን ከከበበው የፔሎታኒ ተራራ አናት የሚገኘው የሳን ድሜኒኮ ቤተ ክርስቲያን ደወል ዘወትር ከእንቅልፏ ይቀሰቅሳታል፡፡ ቀስ እያለች በደስታ ትነሣለች፡፡ አይኗን እየከደነች ድንቅ የነበረውን ነገር አስታወሰች፡፡ አእምሮዋ በደስታ ተሞላ፡፡ እሷ ሉቺያ ማሪያ ከርማን ናት፡፡ የአንጄሎ ካርሚን ልጅ እናም በአለም ላይ ደስተኛ ለመሆን ያ በቂዋ ነው፡፡

የምትኖረው ድንቅ በሆነ ቪላ ውስጥ ሲሆን በአስራ አምስት አመቷ የነበሩትን ሰራተኞች ቆጥራ አትጨርሳቸውም ነበር፡፡ የግል ጠባቂዎች አጅበዋት ትምህርት ቤት አድርሰው ይመልሷታል፡፡ ያማሩ ልብሶችን ትለብሳለች፤ ቢሲሲሊ ያሉ ውድ አሻንጉሊቶች ይገዙላታል፡፡ ይህ ደግሞ የትምህርት ቤት ጓደኞቿ ይቀኑባት ነበር፡፡

የሉቺያ ህይወት የተመሰረተው በአባቷ ዙሪያ ነው፡፡ በእሷ አይን በአለም ላይ ውቡ ሰው እሱ ነው፡፡ አባቷ ሁለት ወንድ ልጆች ሲኖሩት አርናልዶ እና ቪክቶር ይባላሉ፡፡ የሚደሰተው በሴት ልጁ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ሉቺያ ታመልከዋለች፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ቄሱ ስለ አምላክ ሲናገሩ እሷ ስለ አባቷ ታስባለች፡፡

ዘወትር ጠዋት መኝታ ቤቷ በመግባት "ትምህርት ሰዓት ደርሷል" ይላታል፡፡ የሚያቆላምጣት መልአክ የመሰልሽው ልጄ እያለ ነው፡፡

ሉቺያ ቆንጆ እንዳልሆነች ታውቀዋለች፡፡ ነገር ግን ማራኪ ነች፡፡ ሰውነቷ እጅግ የተዋጣለት ነው፡፡ በአስራ አምስት አመቷ ሙሉ የሴት ቁመና ያዘች፡፡

"በቅርቡ እንድርሻለን" እያለ አባቷ ይቀልድባታል፡፡

"አንተን የመሰለ ሰው ነው ማግባት የምፈልገው አባቴ፡፡ ነገር ግን አንተን የሚመስል ማንም የለም፡፡"

ፈገግ አለ፡፡ "አትጨነቂ፡፡ "ልዑል እናመጣልሻለን፡፡ የተወለድሽው በእድለኛዋ ካከብ ስር ነው፡፡ አንድ ቀን የሚወድሽ ሰው ክንድሽን ይዞ ሲጓዝ ምን እንደሚሰማሽ ትደርሺበታለሽ፡፡"

"እሺ አባባ" አለች በደስታ።

እውነት ነው። እስካሁን ከእሷ ጋር ፍቅር የሰራ ሰው የለም። ቤኒቶ ፓታስ ከጠባቂዎቿ አንዱ ሲሆን አባቷ ወደ ከተማ ሲወጣ እግሩን ጠብቆ መኝታ ቤቷ ይገባል። በገዛ አልጋዋ ላይ ፍቅር ይሰራሉ። አባቷ ቢያገኛቸው እንደሚገላቸው ስለምታውቅ በፍርሀት ነበር የሚያደርጉት።

ቤኒቶ እድሜው በሰላሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው። የታላቁ አንጄሎ ካርማይን ልጅ እሱን በመምረጧ በእጅጉ ተደስቷል።

ለመጀመሪያ ጊዜ አብሯት ከተኛ በኋላ "የምትጠብቂው ይህን ነበር?" ሲል ጠየቃት""

"አዎ" አለች ሉቺያ እያለከለከች። "ጥሩ ነበር"

በውስጧ የምታስበው "ከማሪዮ፣ ቶኒ ወይም ኤንሪኮ አይሻልም" እያለች ነበር። አብራቸው የተኛቻቸውን ወንዶች ስም ማስታወስ አቃታት።

በአስራ ሶስት አመቷ ድንግል ሆኖ መቀመጥ ሰለቻት። ፓሎ ኮስቴሎ ለተባለ እድለኛ ወጣት ክብረንፅህናዋን ሰጠችው፣ ልጁ የአባቷ ዶክተር ልጅ ነው። እንዳየችው በፍቅሩ ወድቃ ነበር። እሱ ልጅ አድርጎ ይቆጥራት ነበር። በአንድ ሞቃታማ የነሐሴ ቀን ከዚህ በላይ አልጠብቅም በማለት ደወለችለት።

አባቷ እንደሚፈልገው ነገረችው። ልጁ የሚፈራው የማሪያ አለቃ ከነመኖሩ እንደማያውቀው ቢገምትም ነገሩ አስገረመው።

"ደስ ይለኛል ስንት ሰአት ልምጣ" አላት

"ዘጠኝ ሰአት" አለችው

የፀሎት ሰአት በመሆኑ አለም በጠቅላላ ትተኛለች። ቤቱ ባዶ ይሆናል። አባቷም ከከተማ ውጭ ሔዷል። ማንም አይዛቸውም።

ፓሎ በሰአቱ ደረሰ። መዋኛው አጠገብ ያለው ክፍል ሲደርስ በሩን አንኳኳ። ቆም ብሎ ቢጣራም መልስ አጣ። በሩን ከፍቶ "ሲኖርካርማይን?" በማለት በድጋሚ ተጣራ።

አንድ ነገር ወደ እሱ እየተንቀሳቀሰ "ፓሎ . . ." የሉቺያን ድምፅ አስታወሰው። "ሉቺያ አባትሽን ፈልጌ ነበር። እቤት አለ?





አሁን በጣም ተጠጋችው። እንደአያት ስትቀርበው እርቃኗን መሆኗን ተመለከተ።

"አምላኬ" አለ ፓሎ። "ምንድን . . . ?"

"ከእኔ ጋር ፍቅር እንድትሰራ እፈልጋለሁ።"

"ገና ልጅነሽ። ከዚህ መውጣት አለብኝ" አላት በር በሩን እየተመለከተ።

"ሒድ። ለአባቴ አስገድደህ እንደደፈርከኝ እነግረዋለሁ"

"አታደርጊውም"

"ሒድና ታገኘዋለህ"

ባለበት ቆሞ ሉቺያ የተናገረችውን ከፈፀመችው እድሉ ምን እንደሆነ ያውቀዋል።

ሊያሳምናት ተጠጋት "ሉቺያ . . .የእኔ ውድ"

"ውዴ ስትለኝ ደስ ይለኛል"

"አይደለም . . . ስሚኝ ሉቺያ። ነገሩ አሳሳቢ ነው። ለአባትሽ ደፈረኝ ብለሽ ከነገርሽው ይገለኛል"

"አውቃለሁ።"

ቢያደርገውም ቢተወውም ለውጥ የለም። ትቶ ቢወጣ መሞቱ አይቀርም። እጁን ጐትታ ጭኗ ስር ከተተችው።

ፓሎ ሳይወድ ተገናኛት። "ድንቅ ናት" ሲል አሰበ።

ሉቺያ ገነት የገባች ያህል ተሰማት። ለእዚህ ነገር እንደተወለደች ገመተች። እሱንም እራሷንም እንዴት ማስደሰት እንደምትችል ደመነፍሷ ነግሯታል። ሰውነቷ በጠቅላላ ነደደ። የስሜቷ ጣራ ላይ ስትደርስ በደስታ ጮኸች። በረጅሙ እየተነፈሱ ተጋደሙ።

ሉቺያ በመጨረሻ "ነገ በዚህ ሰዓት" በማለት ተናገረች።

ሉቺያ አስራ ስድስት አመት ሲሞላት አባቷ ከአክስቷ ጋር አለምን ማየት አለባት በማለት ወሰነ። የእረፍት ጊዜዋን ካፕሪ፣ ኢቺያ፣ ቬነስ እና ሮማ

ሉቺያ በድጋሚ "ለጓደኝነታችን" አለች ብርጭቆዋን ከፍ አድርጋ:: ዳኛው ንግግራቸውን አልጨረሱም:: በድንገት ትንፋሽ አጠራቸው:: ልባቸውን ቀሰፍ ያዛቸው:: "እባክሽ ዶክተር ጥሪ ... አምላኬ"

በጉልበታቸው በርከክ ብለው ወለሉ ላይ ተነጠፉ:: ለዘለአለሙ ባሉበት አንቀላፉ::

"ይሄ አንደኛው ነው አባባ" አለች ሉቺያ::

ቤኒቶ ፓታኮ ክፍሉ ውስጥ ሆኖ የግል ካርታ እየተጫወተ ሳለ የእስር ቤት ጠባቂው ጉብኚ እንደሚፈልገው ነገረው::

ቤኒቶ ተጠራጠረ:: መረጃ በማቀበሉ ከተሰጡት እድሎች መካከል በፈለገው ሰአት የሴት ወዳጆቹ እንዲጎበኙት መደረጉ አንዱ ነው:: ብዙ የሴት ጓደኞቹ እየተመለሳለሱ ስለሚጠይቁት ዛሬ የመጣችው "ማን ናት?" ሲል ራሱን ጠየቀ::

ጠባቂው እየመራ ወደ ሌላ ክፍል ወሰደው:: እንግዳ የሚቀበሉበት የግል ክፍል አስገባው:: ክፍሉ ውስጥ ሲገባ ያልጠበቀው ነገር ስለገጠመው ወደ ኋላው አፈገፈገ::

"ሉቺያ" አምላኬ እዚህ ምን ታደርጊያለሽ? እንዴት መግባት ቻልሽ?" ሉቺያ በለስላሳ ድምጿ "ልንተጫጭ መሆኑን ነገርኳቸው ቤኒቶ" አለችው::

ገላዋን የሚያሳይ ቀይ ስስ ቀሚስ አጥልቃለች::

ቢኒቶ ፓታስ ወደ ኋላ አፈገፈገ:: "ከዚህ ውጪ"

"ከፈለክ:: ነገር ግን በቅድሚያ መስማት ያለብህ ነገር አለ:: ምስክርነት ስትሰጥ ስመለከትህ ጠልቼህ ነበር:: ልገልህ ፈልጌ ነበር" አለችው ወደ እሱ እየተጠጋች:: "ግን ቆየት ብዬ ሳስበው የሰራኸው ነገር የጀግና ተግባር ነው:: እውነቱን አውጥተሀል:: ቤተሰቦቼ ሰይጣን ባይሆኑም የሰይጣን ተግባር ሲያከናውኑ ነበር:: ከእነሱ ፊት የቆምከው ደፋሩ ሰው አንተ ብቻ ነህ::"

"እመኚኝ ሉቺያ ፖሊሶች አስገድደውኝ ነው. . ."

"ማብራራት አይጠበቅብህም" አለችው ተረጋግታ::

"ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር የሰራንበትን ቀን አስታውስ? ከዛ ቀን አንስቶ ነው ፍቅር የያዘኝ አሁንም እንደዛው ነኝ::"





"ሉቺያ ያደርኩትን ነገር የማድረግ . . ."

"የተፈጠረውን ነገር መርሳት ይገባናል:: የሆነው ሆኗል:: አሁንም አስፈላጊዎቹ እኔ እና አንተ ነን::

ስትጠጋው ሽቶዋ አወደው:: ግራ በመጋባት ስሜት ተዋጠ:: ምንድን ነው ያልሽው?

"በህይወቴ ከዚህ በላይ የተናገርኩት ነገር የለም:: ዛሬ እዚህ የመጣሁት ለዚህ ነው:: የአንተ መሆኔን ላረጋግጥልህ ነው የመጣሁት:: ከዚህ በኋላ ምንም ቃል እንዳትተነፍስ::"

ቀሚሷን ከገላዋ ላይ አውልቃ ጣለችው:: እርቃኗን ፊቱ ቆመች:: "አሁንስ አመንከኝ?"

አምላኬ በጣም ቆንጆ ነች:: "አዎ አምኜሻለሁ" አሳት ድምፁ እንደተቆራረጠ::

ሉቺያ በገላዋ እያሸች ተጠጋችው:: "ልብስህን አውልቅ" በማለት አንሾካሾከችለት:: "ፍጠን"

ፓታስ ልብሱን ሲያወልቅ ተመለከተችው:: በፍጥነት ክፍሉ ጥግ ወዳለችው አልጋ ወስዷት ማሟሟቂ ሳያስፈልገው እላይዋ ላይ ተከመረባት::

"ልክ እንደ በፊቱ አትረሽኝም አይደለም" ሲል ጠየቃት::

"አዎ አልረሳህም" አለች በዝግታ:: "ግን ለምን እንደማልረሳ ታውቃለህ?"

"አላውቅም የእኔ ፍቅር:: ንገሪኝ::"

"ምክንያቱም ልክ እንደ አባቴ ሲሲሊያዊ ስለሆንክ"

በዛው ፍጥነት ፀጉሯ ውስጥ የሰካችውን ሹል ፀጉር ማስያዣ አወጣችው::

ቤኒቶ ፓታስ ጉሉ በሆነ ነገር ሲወጋ ተሰማው ሊጮህ ሲሞክር ሉቺያ አፉን ግጥም አድርጋ ሳመችው:: እሱ ሲያጣጥር እሷ የእርካታ ጣራ ላይ ደረሰች:: አልጋው ላይ ቀስ ብላ ብርድልብስ አልብሳ አጋደመችው::

ሉቺያ በሩን አንኳኩታ እየወጣች ለጠባቂው "ተኝቷል" አለችው::

ጠባቂው ቆንጆዋን ልጅ እያየ "ዘረርሽው" አላት::

"እባክዎት ፓስፖርት"

ሉቺያ ለስፔን የኢሚግሬሽን ኦፊሰር ፓስፖርቷን ሰጠችው፡፡ አይቶ ሊመልስላት ካለ በኋላ እመነታና ወደኋላ ተመለሰ፡፡ በጥሞና ከተመለከታት በኋላ ሁኔታው ተለዋወጠ፡፡

"እባክዎ ጥቂት ይጠብቁ፡፡ ቢሮ ገብቼ ማህተም አድርጌ ልምጣ"

አውቆኛል ስትል ሉቺያ ተስፋ በመቁረጥ አሰበች፡፡ ወደ ክፍሏ ገብቶ ፓስፖርቱን ለሌላ ኦፊሰር ሲያሳየው አሻግራ ተመለከተችው፡፡ ማምለጥ አለባት፡ ፡ በሩን ከፍታ ከመኪና ወረደች፡፡ በቡድን የመጡ የጀርመን ቱሪስቶች እየጮኹ በአጠገቧ አለፉ፡፡ መኪናቸው ላይ "ማድሪድ" ተብሎ ተለጥፎበታል፡፡

ፓስፖርቱን የተቀበላት ኦፊሰር በስልክ እየጮኸ ሲያወራ ተመለከተችው፡፡

ሉቺያ ደግሞ ማሰብ ሳያስፈልጋት አስጐብኚው ሳይመለከታት ከቱሪስቶች ጋር ተደባለቀች፡፡ መኪናው ውስጥ ገብታ የኋላ ወንበር ላይ አንገቷን አቀርቅራ ተቀመጠች፡፡ ተንቀሳቀስ! ስትል ፀለየች፡፡ አሁኑኑ፡፡

ፀሎቷ የተሰማ ያህል መኪናው ተንቀሣቀሰ፡፡ ሳንሰባስቲያንን ለቆ ወደ ማድሪድ ጉዞውን ጀመረ፡፡ ጠ ባቂዎቹ መኪናውን ትታ መሰወሯን ሲያውቁ ምን ያደርጋሉ? ፈልገው ሲያጧት ለአለቆቻቸው ያሳውቃሉ፡፡ በአካባቢው ብዙ መኪና ስለሚተላለፍ ወዴት እንደተጓዘች ሐሣቡ አይኖራቸውም፡፡

ጐብኚዎች ዘወትር በደስታ የተሞሉ ናቸው፡፡ ለምን አይደሰቱ? አለች ሉቺያ በሐሣቧ ፖሊስ እያሳደዳቸው፡፡ የዳኛ ጆቫኒና ቤኒቶ ምስል አይኗ ላይ ድቅን አለ፡፡ የተናገሩትን ነገር እያስታወሳት ፈገግ አለች፡፡ የክህደታቸውን ዋጋ ሰጥታቸዋለች፡፡ እነሱ ሞተዋል፡፡ ቤተሰቦቿ ግን እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ በእስር ቤት ይማቅቃሉ፡፡

ሉቺያ ለጊዜው ከጐብኚዎቹ ጋር በመሆኗ ደህንነቷ የተጠበቀ መሆኑ ተሰማት፡፡ "ማድሪድ ስደርስ የሚቀጥለውን እርምጃዬን እወስናለሁ" ስትል አሰበች፡፡

ማድሪድን አታውቃትም፡፡

ቡድኑ በያዘው ፕሮግራም መሠረት በድንጋይ የተሠራችው አቪላ ከተማ ሲደርስ ትንሽ እረፍት ይወስዳል፡፡





ጐብኚዎቹ እንዲወርዱ ተነገራቸው፡፡

ሉቺያ ከወንበሯ አልተነቃነቀችም፡፡ ሁሉም ሲወርዱ ተመለከተቻቸው፡፡ "እዚህ መቀመጥ ለደህንነቴ ጥሩ ነው" ስትል አሰበች፡፡ ነገር ግን አስጐብኚው ለይቶ ሊያውቃት ይችላል፡፡

"ውረጂ" አስራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው ያለን"

ሉቺያ እያመነታች ተነስታ ወደ በሩ ሔደች፡፡

አስጐብኚውን አልፋ ልትሔድ ስትል "አንቺ የዚህ ቡድን አባል አይደለሽም?" አላት፡፡

ሉቺያ ሞቅ ያለ ፈገግታ ለገሰችው፡፡ "አይደለሁም" አለችው፡፡ "መኪናዬ ሳንሳባስቲያን ላይ ተበላሸብኝ፡፡ ማድሪድ የምደርስበት አስፈላጊ ጉዳይ አለብኝ፡፡ እናም እኔ ..."

"አይሆንም" አላት እየጮኸ፡፡

"አውቃለሁ" አለችው ሉቺያ፡፡ "ነገር ግን ገባህ እኔ ..."

"አይቻልም ዋናው ቢሮ ማወቅ አለበት"

"አልችልም፡፡ በጣም ቸኩያለሁ እና ..."

"አይሆንም፡፡ ችግር ውስጥ ትከቺኛለሽ፡፡ ከዚህ ውጪ አለበለዚያ ለፖሊስ እደውላለሁ፡፡"

"ግን"

ምንም ብትለው አይቀበላትም፡፡ ከሀያ ደቂቃ በኋላ ጐብኚዎቹ ጥለዋት ወደ ማድሪድ ጉዞአቸውን ጀመሩ፡፡ ፓስፖርት እና ገንዘብ የላትም፡፡ አሁን በብዙ አገራት የሚገኙ በደርዘን የሚቆጠሩ ፖሊሶች በግድያ እየፈለጓት ይሆናል፡፡

ዙሪያዋን ተመልክታ ሌላ አውቶብስ ላገኝ እችላለሁ ስትል አሰበች፡፡ ወደ አውቶብስ ማቆሚያ ጣቢያው ሄደች፡፡ የተለያዩ የጉዞ መስመሮች ምልክት ተለጥፈውበታል፡፡ ምግብ የሚሸጡ ነጋዴዎች ስትመለከት ሆዷ ተላወሰባት፡፡ የአውቶብስ ትኬቱ ስንት እንደሚያወጣ ስታጣራ ምግብ አትገዛም፡፡

ማድሪድ ተብሎ ወደተፃፈው መሣፈሪያ ስትጠጋ ሁለት ፖሊሶች በፍጥነት

ወደጣቢያው ሲገቡ ተመለከተች፡፡ አንዱ ፎቶግራፍ ይዟል፡፡ ከአንዱ መስኮት ወደ አንዱ እየተሽጋገሩ ለተሳፋሪዎች ፎቶውን ያሳያሉ፡፡

እኔን እየፈለጉ ነው፡፡ አስጐብኚው ሳይደውልላቸው አልቀረም፡፡ ሉቺያ በሰዎች ተከልላ ወደ ውጭ ወጣች፡፡

በኮብል ስቶን ያጌጠውን የኢቫላ መንገድ ይዛ በፍጥነት ለመሰወር ስትንደረደር ትኩረት እንዳትስብ ሰጋች፡፡ ጥቂት ከተጓዘች በኂላ አንድ መናፈሻ ውስጥ ተቀምጣ ስለሚቀጥለው ጉዞዋ ማሰላሰል ያዘች፡፡ አሁንም ፖሊስ ያለችበት አካባቢ ደረሰ፡፡ አንዷን ሴት መጠየቅ ሲጀምር የሉቺያ ልብ መደለቅ ጀመረ፡፡

ልቧ እየመታ ተነስታ ቆመች፡፡ ጀርባዋን ለፖሊሱ ሰጥታ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ የሚቀጥለው ጐዳና በማይታመን መልኩ "የህይወትና የሞት ጐዳና" ተብሎ ተፅፎበታል፡፡

ፊት ለፊቷ ግዙፍ ካቴድራል ይታያል፡፡ በሩ ላይ ወጣት ሴት እና ትልቅ አፅም (የራስ ቅል) ተሰቅሏል፡፡ አየሩ በሞት የተሞላ ነው፡፡

ሉቺያ የቤተክርስቲያን ደወል ስትሰማ በከተማዋ መግቢያ በር አሻግራ ተመለከተች፡፡ ራቅ ብሎ ተራራው አናት ላይ የአንድ ገዳይ አጥር አየች፡፡ ያለችበት ቆማ ተመለከተችው፡፡

"የእኔ ልጅ ወደእኛ የመጣችው ለምንድን ነው?" በማለት ሐላፊዋ መነኩሴዋ እማሆይ ቤቲና ለስለስ ብለው ጠየቋት፡፡

"መጠለያ ፈልጌ ነው"

"የአምላክን መጠለያ ፈልገሽ ነው የመጣችው?"

ትክክል፡፡ "አዎ" አለች ሉቺያ በማረጋገጥ፡፡ "የሁልጊዜ ምኞቴ እንደዚህ አይነት ቦታ መኖር ነው፡፡ ... ህይወቴን ለመንፈሣዊ ነገር ማስገዛት፡፡

"ሁላችንም ለነፍሣችን የምንመኘው ይህንኑ ነው፡፡ አይደለም እንዴ ልጄ? እየሱስ ከልቧ እንደምትገዛለት፡፡ ሉቺያ በደስታ አሰበች፡፡

መነኩሴው ተጠግተዋት " የሴቶች ገዳም ህግ ጥብቅ መሆኑን ልትረጂ ይገባውል፡፡ ከውጭው አለም የተገለገልን ነን፡፡ ህጋችንም ከየትኛውም በላይ ጥብቅ ነው፡፡





አነጋገሯ ሉቺያ ጆሮ እንደ ሙዚቃ ነበር፡፡

"ወደዚህ ገዳም የሚገቡ ተመልሰው መውጣት አይችሉም፡፡"

"በፍፁም ከዚህ መውጣት አልፈልግም" በማለት ሉቺያ ለራሷ አረጋገጠች፡፡ ለማንኛውም ለሚቀጥሉት ጥቂት ወራት አላስበውም፡፡

መነኩሴው ተነሱ፡፡ "ጥሩ ውሣኔ ነው፡፡ ከመወሰንሽ በፊት ዳግመኛ አስቢበት፡፡"

የምትሄድበት ቦታ የላትም፡፡ ብቸኛ ተስፋዋ ያለው ከዚህ አጥር ጀርባ ነው፡፡

"በደንብ አስቤበታለሁ" አለች ሉቺያ በፍጥነት፡፡ "እመኑኝ እናቴ ከዚህ ውጭ የማስበው ነገር የለኝም፡፡ አለምን መተው እፈልጋለሁ" አለቻቸው እማሆይን እየተመለከተች፡፡ "በአለም ላይ እዚህ ከመሆን ውጭ የምፈልገው ነገር የለም፡፡"

መነኩሴዋ ግራ ተጋቡ፡፡ እቺ ሴት ትረብሻለች፡፡ ያልተረጋጋ ነገር ይታይባታል ሲሉ አሰቡ፡፡ እዚህ የሚመጡ ሰዎች ጊዜያቸውን በተመስጦ እና በፀሎት ለማሳለፍ የቆረጡ ናቸው፡፡

"ካቶሊክ ነሽ?"

"አዎ"

"ስምሽን ንገሪኝ ልጄ?" አሉ ለመፃፍ እየተዘጋጁ፡

"ሉቺያ ካር ...ሮሜ"

"ቤተሰቦችሽ በህይወት አሉ?"

"አባቴ አለ"

"ምን ይሠራሉ?"

"ነጋዴ ነበር፡፡ አሁን ጡረታ ወጥቷል" አባቷ ትዝ አላት፡፡

"ወንድም ወይም እህት አለሽ?"

"ሁለት ወንድሞች"

"እነሱስ ምን ይሠራሉ?"

ሉቺያ እርዳታ የምታገኝበትን መንገድ አሰበች።

"ቄስ ናቸው"

"ድንቅ ነው"

ጥያቄው ሶስት ሰአት ፈጀ። በመጨረሻ እናት ቤቲና "ዛሬ የምታድርበት አልጋ አገኝልሻለሁ። ሲነጋ መመሪያዎች ይነግሩሻል። ነገሩ ሲያበቃ ስሜትሽ ተመሣሣይ ከሆነ ትዕዛዙን ትቀላቀያለሽ። የመረጥሽው መንገድ አስቸጋሪ መሆኑን ላስጠነቅቅሽ እወዳለሁ።"

"እመኚኝ" አለች ሉቺያ በእርግጠኝነት። "ሌላ አማራጭ የለኝም።"

ምሽቱ ቀዝቃዛ ቢሆንም ሉቺያ ተመችቷት ተኛች። ህልም እየለመደች ነው። "አንድ ሰው ወደክፍሏ ገብቶ እነዚህ እነማን ናቸው? ሲል ጠየቀ። በድንገት መብራት ሲበራባት ከእንቅልፏ ነቃች።

ግማሽ ደርዘን ሰዎች ከበዋቸዋል። መነኩሴዎቹ ደንግጠዋል። ሉቺያ በጨረቃዋ ብርሃን ቅርፃቸውን ብቻ ለመለየት ቻለች።

"እነማን ናችሁ?" በማለት ሰውየው በድጋሚ ጠየቃቸው። ድምፁ መራራና አስፈሪ ነው።

ሉቺያ በደንብ ነቃች። አእምሮዋ ዝግጁ ነበር። ተከባለች። እነዚህ ሰዎች ፖሊስ ቢሆን ኖሮ መነኩሴዎቹን ያውቋቸው ነበር። በዚህ ጨለማ እዚህ ጫካ ውስጥ ምን ያደርጋሉ?"

ሉቺያ እድሏን ተጠቀመችበት። "እኛ አቪላ ከሚገኘው ገዳም የመጣን መነኮሳት ነን።" አለች። "የሆኑ የመንግሥት ሰዎች መጥተው .."

"ስለእሱ ሰምተናል" በማለት ሰውየው አቋረጣት።

ሌሎቹ ሴቶች ነቅተው በፍርሃት ቁጭ ብለዋል።

"ማን .. ማን ናቸው?" ስትል ሜጋን ጠየቀች።

"የእኔ ስም ጂሚ ሚሮ ነው።"





ሰዎቹ ስድስት ሲሆኑ አለባበሳቸው እንደ ነገሩ ነው። የባስክን ባህላዊ ኮፍያ አጥልቀዋል። በከፍተኛ ሁኔታ መሣሪያ ታጥቀዋል። ሁለቱ ሰዎች ክፉኛ ተደብድበዋል።

ጂሚ ሚር ብሎ የተዋወቃቸው ሰው ረጅምና ጉበጥ ያለ ባለ ጥቁር አይን ነው። "እየተከተሉን ይሆናል"

ከአባላቱ ወደ አንዱ ዞሮ "ዙሪያውን ቃኝተህ ና"

"እሺ"

ሉቺያ ትእዛዝ የተቀበለችው ሴት መሆኗን ተገነዘበች። ዛፉን ተከልላ በጥንቃቄ ስትጓዝ አየቻት።

"ከእነሱ ጋር ምን እናደርጋለን?" ሲል ሪካርዶ ሜላዩ ጠየቀ።

"ትተናቸው እንሄዳለን" በማለት ጂሚ ሚሮ መለሰላት። ሌላው ሰው በተቃርኖ "ጂሚ ... እነዚህ የኢየሱስ አገልጋዮች ናቸው"

"እና ኢየሱስ ይጠብቃቸው" አለው ጂሚ ስሜት አልባ ሆኖ።

"የራሣችን ስራ አለብን"

መነኮሳቱ ባሉበት ቆመው ይጠብቃሉ። ሰዎቹ ጂሚን ከበውት እየተከራከሩ ነው።

"እንዲያዙ ትተናቸው አንሄድም። አኮካና ሰዎቹ እየፈለጋቸው ነው።"

"እኛንም እየፈለጉን ነው ወዳጄ"

"ሲስተሮቹ ከእኛ እርዳታ ውጭ ምንም ነገር ማሳካት አይችሉም"

ጂሚ ሚሮ በቁጣ "አይሆንም" ለእነሱ ብለን ህይወታችን አደጋ ላይ መጣል የለብንም። የራሣችን ችግር አለብን።"

ከአዛገሮቹ አንዱ የሆነው ፌለክስ ካርፒዬ "መንገድ ላይ ጥለናቸው እንሄዳለን ጂሚ ከዚህ እስኪወጡ ድረስ እንርዳቸው" አለና ወደ መነኮሳቱ ዞረ። "ወዴት ነው የምትሄዱት?"

የአምላክ ብርሃን አይኗ ላይ እየታየ ቴሬዛ ተናገረች። "መንፈሣዊ ተልእኮ

ተቀብያለሁ:: ሜንዳቪያ አንድ ገዳም አለ ወደእዛ ነው የምንሄደው::"

ተቀብያለሁ:: ሜንዳቪያ አንድ ገዳም አለ ወደእዛ ነው የምንሄደው::" ፌሊክስ ካርፒዬ ለጂሚ "እዛ ትተናቸው እንሄዳለን:: ሜንዳቪያን ወደ ሳንሲባስቲያን በምናደርገው ጉዞ ላይ እናገኘዋለን::"

ጂሚ ሜሮ በቀጣ ዞሮ እየተመለከተው:: "አንተ ደደብ ሞኝ!" የት እንደምንሄድ ለማንም ለሁሉም ሰው ሄደህ አትናገርም?"

"ማለት የፈለኩት ..."

"የማትረባ" አለው ድምፁ በንዴት ተሞልቶ:: "አሁን ምንም አማራጭ የለንም:: ከእኛ ጋር እንወስዳቸዋለን:: አኮካ ካገኛቸው እንዲናገሩ ያደርጋቸዋል:: ጉዞአችንን ቀርፋፋ በማድረግ አኮካ እና ኢራጆቹ እንዲይዙን እድል ይሰጧቸዋል::"

ሉቺያ በከፊል ነው የምታዳምጠው:: መስቀሉ አጠገብ ደርሳ ነበር:: ሰዎቹ እድሏን አበላሹባት::

"ጥሩ" አለ ጂሚ ሚሮ:: "የተባለውን ነገር እናደርጋለን:: ገዳሙ አጠገብ እናደርሳቸዋለን:: ነገር ግን ሁላችንም አብረን አንሄድም::" አለና ወደ መነኩሴዎቹ ዞረ:: ቁጣው አልበረደለትም:: "ከእናንተ መካከል ሜንዳቪያ የት እንደሆነ የሚያውቅ አለ?"

ሲስተሮቹ እርስ በእርሳቸው ተያዩ::

ግራሺላ "በትክክል አናውቀውም" አለች::

"ጌና እንዴት እዛ ለመድረስ አሰባችሁ?"

"እምላክ ይመራናል" አሉ ሲስተር ቴሬዛ በእርግጠኛነት::

ሩቢዮ አርዛም (የተባለው ታጣቂ "እድለኞች ናችሁ" አላቸው ወደ ጂሚ እየተመለከቱ:: "በሰዎች ተመስሎ እየመራችሁ ነው ሲስተር::"

ጂ ሚ መልስ አልሰጠም:: "በቡድን እንከፋፈላለን:: በሦስት አቅጣጫ እንጓዛለን::"

ካርታ አወጣና ከሰዎቹ ጋር መመልከት ያዘ::

"የሚንዳቪያ ገዳም የሚገኝበትን ቦታ አሳያቸው:: ከሎግራም ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል:: እኔ በሰሜን በኩል በባላዲልድ አቅጣጫ እጓዛለሁ:: ሩቢዮ





አንተ ደግሞ በኦልሜዶ በኩል ትሄዳለህ:: ሪካርዶ ሜላዶ አንተ ደግሞ በሴጐቪያ በኩል ትንቀሣቀሳለህ:: ሁላችንም ሎግራም ላይ እንገናኛለን:: ሎግራም ከዚህ 210 ኪሎ ሜትር ይርቃል:: ከሰባት ቀን በኋላ እዛው እንገናኛለን:: ከዋናው መንገድ ርቃችሁ ተጓዙ::

የሚገናኙበት ቦታ ተነጋግረው ሲለያዩ ሲሉ መነኮሳቱን ተከፋፈሏቸው::

በዚህ ጊዜ "ሉቺያ ወታደሮች የሚፈልጓችሁ ከሆነ ብቻችንን ብንጓዝ አደጋ አያገኘንም" አለች::

አሁን ብቻችሁን ልንተዋችሁ አንችልም:: ወይዘሪት አላት ጂሚ:: "ምክንያቱም ስለእቅዳችን ከሚገባው በላይ አውቃችኋለሁ::"

ሩቢዮ በበኩሉ "አገሩን አታውቁትም:: እኛ የባስክ ተወላጅ ነን:: ሰዎች ይረዱናል:: ይደብቁናል አላቸው::

እኔ ሜንዳቪያ መሄድ አልፈልግም:: አንተ ደደብ አለች ሉቺያ ለራሷ::

ሲስተር ሜጋን ትዕዛዝ የሚሰጠውን ሰው በጥሞና እየተመለከተችው ነው:: ደደብና መደዴ ነው ስትል አሰበች:: ነገር ግን ኃያል መሆኑ ያስታውቃል::

ወደ ቶማስ ሳንጅሮ እና ሩቢዮ አርዛኖ እየተመለከተ ሲስተር ቴሬዛ በእናንተ ኃላፊነት ስር ይሆናሉ" አለችው::

ሲስተር ቴሬዛ "የእኔ ኃላፊ አምላክ ነው" አሉት::

"ትክክል" አላቸው ጂሚ:: "በመጀመሪያ እዚህ የደረሳችሁት በእርሱ እርዳታ ነው::"

ሩቢዮ ወደ ሲስተር ቴሬዛ ተጠጋ:: "ሩቢዮ አርዛኖ የእርሶ አገልጋይ ነኝ:: እርስዎን ማን ልበል ሲስተር?"

"እኔ ሲስተር ቴሬዛ እባላለሁ"

ሉቺያ ፈጠ ን ብላ "እኔ ከሲስተር ቴሬዛ ጋር እሄዳለሁ" አለች:: እሷን በማንኛውም መንገድ ከወርቅ መስቀሉ ሊለያት አይችሉም::

ጂሚ ሚሮ በእሽታ አንገቱን ነቀነቀ:: "ጥሩ" አለ ወደ ግራሺላ እያመላከተ:: "ሪካርዶ እሷ ካንተ ጋር ትሄዳለች"

ሪካርዶ ሜላዶ አንገቱን እየነቀነቀ "እሺ" አለው።

ጂሚ አካባቢዋን እንድትቃኝ የላካት ሴት ተመለሰች። "ሁሉም ሰላማዊ ነው" አለች።

"በጣም ጥሩ" አለ ጂ ሚ ሚሮ ሜጋንን እየተመለከተ። "አንቺ ከእኛ ጋር ትመጫለሽ ሲስተር"

ሜጋን በእሽታ አንገቷን ከፍ ዝቅ አደረገች። ጂሚ ተመስጦባታል። ስለእሷ የሆነ የረበሸው ነገር አለ። ጥቁርና አስፈሪ ገፅታ አላት። ወሲብ የሚቀሰቅስ አመለካከት ይታይባታል።

ሴቷ ወደ ሜጋን ተጠጋች። "አምፓሮ ጂሮን እባላለሁ። ሲስተር አፍሽን ከዘጋሽ ችግር አይገጥምሽም።"

ጂሚ ሚሮ የመጨረሻውን ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ሁሉም ተበታትነው ጉዞቸውን ጀመሩ።





# ምዕራፍ አስር

ሚጉዌል ካሪሎ ተበሳጭቷል። በእርግጥም ቢበሳጭ አይፈረድበትም። ለእሱ ጥሩ ቀን አልነበረም። አራቱን መነኩሴዎች ሲያገኝ ቀኑ ጥሩ ሆኖለት ነበር። እሱም መነኩሴ መሆኑን ተናግሮ አሳምኗቸው ነበር። መጨረሻው ደግሞ ራሱን ስቶ ሱቁ ውስጥ እጁ ታስሮ አገኘ።

መጀመሪያ ያገኘችው የሱቁ ባለቤት ሚስት ነች። "ማን ነህ ስትል ጠየቀችው? እዚህ ምን ትሰራለህ? ስትል ጠየቀችው።

ካሪሎ በፈገግታ ተሞልቶ ዞሮ ተመለከታት። "እግዜር ይመስገን። እርሶ ደርሰውልኛል። "እለ በፍፁም እርግጠኛነት።። ከዚህ ለመውጣት እየተፍጨረጨርኩ ነበር። ፓሊስ ለመጥራት በስልክዎት መጠቀም እችላለሁ?"

"ጥያቄዬን አልመለስክልኝም እኮ።"

ተረጋግቶ ለመታገል ሞከረ። "ማብራሪያው ቀላላ ነው ወይዘሮ እባት ጉንዛሌዝ እባላለሁ። ማድሪድ አጠገብ ካለ ገዳም ነው የመጣሁት። በዚህ ሱቅ በኩል ሳልፍ ሁለት ወጣቶች ሰብረው ሲገቡ ተመለከትኩ። የእግዚአብሔር ሰው በመሆኔ እነሱን ማስቆም ግዴታዬ መሆኑ ተሰማኝ። ስህተት እየሰሩ መሆናቸውን ልነግራቸው ተከትያቸው ገባሁ። ነገር ግን ደብድበው አሰሩኝ። አሁን ቢፈቱኝ ጥሩ ነው . . ."

"የማትረባ!"

ትኩር ብሎ አያቸው። "ይቅርታዎትን እለምናለሁ?"

"ማነህ?"

"ነገርኩዎት እኮ እኔ . . ."

"እስከ ዛሬ ከማውቃቸው ሁሉ የበለጥክ ውሸታም ነህ" መነኩሴዎቹ የፈቱትን ገመድ ጠጋ ብላ ተመለከተችው።

"እነዚህ ምንድን ናቸው?"

"እ። እነዚህ አዎ። ሁለቱ ጉረምሶች ለማታለል የለበሷቸው ናቸው። አየሽ እና . . ."

ቆልፈውብኝ ጥለውኝ ሔዱ።

"የት እንደሚሔዱ ነግረውሀል ወይም ሲናገሩ ሰምተሀል?" በድንገት በካሪሎ ውስጥ ክብር የሚለው ሐሳብ ብልጭ አለ። ካሪሎ። "አልሰማሁም" አለ። "ሜንዳቪያ" የሚለውን ቃል ከአፉ አያወጣውም። ለመነኩሴዎቹ ደህንነት ሳይሆን ኮለኔሉ ፊቱን ስላበላሸበት ነው የማይነግረው። ከእስር ቤት ሲወጣ ኑሮ እንደሚከብደው ካሁኑ ገብቶታል።

ኮሎኔል አኮካ ወደ ጠባቂዎቹ ዞረ።

"በትንሹ ወዳጃዊ የማሳመን ስራው ምን እንዳስጋኝ እናየዋለን? ወደ ማድሪድ ላኩትና በግድያ ወንጀል ክሰሱት።"

ሉቺያ፣ ሲስተር ቴሬዛ፣ ሩቢዮ አርዛኖ እና ቶማስ ሳንጃሮ በሰሜን ምስራቅ በኩል እየተጓዙ ነው። የሚሔዱት ውሰጥ ለውስጥ ነው። ቀን ቁጥቋጦ ስር እየተደበቁ ሲጨልም ይጓዛሉ። ብዙ የገጠር መንደሮችን አቋርጠዋል።

ሩቢዮ አርዛኖ "ኦልሜዳ ቅርብ ነች። እስኪመሽ እዚህ እንቆያለን ሁላታችሁ ትንሽ መተኛት አለባችሁ።"

ሲስተር ቴሬዛ አካላቸው ደክሟል። የሆነ ነገር ውስጣቸውን እየረበሻቸው ነው። ከእውነቱ ጋር ከተራራቁ ቆይተዋል። ነገሩ የተጀመረው እጅግ የምትወደው መቁጠሪያ የፀሎት መፅሐፍ ከጠፋበት እለት አንስቶ ነው። ጥላው ነው ወይስ የሆነ ሰው ሰርቋት ነው? እርግጠኛ አይደለችም። ከምታስበው በላይ የአመታት መጠለያዋ ነው። ምን ያህል ጊዜ ፀሎት አድረሳበታለች። በሺዎች የህይወቷ እና የደ ህንነቷ ክፋይ ቢሆንም አሁን ጠፍቷል።

ገዳሙ ሲጠቃ ነው የጣለችው? ጥቃትስ ነበር? አሁን እውነት አልመስል ብሏታል። የትኛው እውነት እንደሆነ እርግጠኛ መሆን አልቻለችም። ህልሙስ የቱ ነው? በአካል ያየቻት ህፃን ነች። የሞኒካ ልጅ ነበረች? ወይስ አምላክ እየቀለደባት ነው? ነገሩ በጠቅላላ ግራ የሚያጋባ ነው። በወጣትነቱ ሁሉም ነገር ቀላል ነበር። ወጣት ስትሆን ግን . . .





# ምዕራፍ አስራ አንድ
# ኢዝ፣ ፈረንሣይ 1924

የስምንት ዓመት ልጅ በነበረችበት ወቅት የቴሬዛ ዲፏሴስ ደስታ የሚመነጨው ከቤተክርስቲያን ነበር። የዴስ ፔንቴንት ብላንክ ቤተ መቅደስን ጐብኝታለች። በሞናኮ በሚገኝ ካቴድራል ፀሎት አድርሳለች። ነገር ግን ዘወትር የምታገለግለው ኢዝ በሚገኝ ቤተክርስቲያን ነው።

ቴሬዛ የምትኖረው በሜዲትራንያንን ዳርቻ በምትገኘው ኢዝ ከተማ ነው። ከተማዋ ለሞንቴ ካርሎ ትቀርባለች። ከተማዋ ተራራ ላይ የከተመች በመሆኑ ቴሬዛ ከላይ ቆማ ቁልቁል ስትመለከት አለምን የመመልከት ያህል ስሜት ያድርባታል። በአቅራቢያዋ ገዳም ሲኖር የተራራውን ጥግ ይዘው መኖሪያ ቤቶች ተደርድረዋል።

የቴሬዛ የአንድ አመት ታናሽ እህቷ ሞኒካ ከቤቱ ውስጥ ቆንጆዋ እሷ ነች። በልጅነቷ የተመለከታት አንድ ሰው ስታድግ ውብ እንደምትሆን መስክሮላታል።

በአንፃሩ ቴሬዛ አስቀያሚ የምትባል አይነት ናት። ቤተሰቦቿ በጣም ያፍሩባት ነበር። ወደ ፕላስቲክ ቀዶ ህክምና በመላክ አፍንጫዋን ለማስቀነስ ሁሉ አስበው ነበር። ነገር ግን ሁለ ነገሯ የተበላሸ በመሆኑ ለማስተካከል አዳጋች ነው። ሰው ፊት ለመሳቅ አትደፍርም ነበር።

እግዚአብሔር መልከ ጥፉ አድርጐ ቢፈጥራትም በሌላ ስጦታ ክሷታል። ቴሬዛ የመላእክት ድምፅ አላት። ይህን ያወቀችው በቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትዘምር ነው። አድናቆት ጐረፈላት። እያደገች ስትመጣ ድምጿ የበለጠ እያማረ መጣ። የቤተክርስቲያን ዝማሬ በጠቅላላ ለእሷ ተሰጠ። የእሷ ቦታ ቤተክርስቲያን ብቻ ነበር። ከቤተክርስቲያን ውጭ ከሚገባው በላይ አይን አፋርና በራሷ የምታፍር ነች።

በትምህርት ቤት ሁሉም የሚቀርቡት ሞኒካን ነው። ወንዶችና ሴቶች በጠቅላላ ከእሷ ጋር መሆን ያስደስታቸዋል። ሞኒካን ፓርቲ ሲጋብዟት ቴሬዛንም አብረው ይጠሯታል። ነገር ግን ሁኔታውን መጋፈጥ አዳጋች ነው።

አሁን ግብዣ ስታደርጉ እህትማማቾቹን መለየት መጥፎ ፀባይ ነው።" ሞኒካ እህቷ አስቀያሚ በመሆኗ እጅጉን ታፍራለች።

የቴሬዛ ወላጆች እሷን በተመለከተ አያያዛቸው በጥንቃቄ የተሞላ ነው። ግጼታቸውን በአግባቡ ቢወጡም ውስጣቸው ለሞኒካ ያደላል። ቴሬዛ ካጣቻቸው ነገሮች አንዱ ፍቅር ነው።

እሷ የተገለለች፣ ምስጋና ለማግኘት የምትጓጓ፣ ሙዚቃ የምትወድ ጎበዝ ተማሪ ነች። አስተማሪዎቿና የአካባቢዋ ሰዎች ያገኑላታል።

ቴሬዛ ፍቅሯ ከቤተክርስቲያን ጋር ሲሆን ቄሱ እና እየሱስ ይወዷታል። ፀሎቷን ሳታቋርጥ ታደርሳለች። ስትዘምር በተስፋና ደስታ ትሞላለች። ድንቅ ነገር እንደሚገጥማትም ታምናለች። ህይወትን እንድትወድ የሚያደርጋት ብቸኛው ነገር ይህ ብቻ ነው።

ደስታ ማጣቷን ለቤተሰቦቿም ሆነ ለእህቷ አሳይታ አታውቅም። እንዲያዝኑ አትፈልግም። በልቧ አምላኳን ከመጠን በላይ ትወደዋለች። እሱም ይወዳታል።

ቴሬዛ ለእህቷ ፍቅር አላት። ሲጫወቱ ሆን ብላ ሞኑካ እንድታሸንፍ ታደርጋታለች። እያደጉ ሲመጡ እንደተገመተው የሞኑካ ውበት ሲጨምር ቴሬዛ ክፍሏ ተደብቃ ልብስ ትሰፋለች።

አንድ ቀን ከክፍሏ ወጥታ ወደ ጓዳ ስታልፍ አባትና እናቷ "ቴሬዛ አሮጊት የቤት እመቤት መሰለች። እኛ የራሳችንን ስራ መስራት አለብን" እያሉ ሲነጋገሩ አዳመጠች።

"ቴሬዛ አጣማሪዋን ታገኛለች። ለዚህ ብቁ ነች"

"የዛሬ ልጆች እሷን የሚከተሉ አይደሉም። እነሱ የሚፈልጉት ላይ የሚያስደስታቸውን ነው"

ቴሬዛ ወጥታ በረረች።

ቴሬዛ ዘወትር እሁድ ቤተክርስቲያን ሔዳ መዘመሯን አላቋረጠችም። በድንገት የፈጠረው ነገር የህይወቷን አቅጣጫ እስከመጨረሻው ቀየረው። በፀሎት ፕሮግራሙ ላይ ኑስ ያለው የሬዲዮ ጣቢያ ዳይሬክተር አክስት ተገኝታ ነበር።

ቴሬዛ አጠገብ ቆማ አነጋገረቻት።

"የእኔ ውድ እዚህ ሆነሽ ህይወትሽን እያባካንሽው ነው። ድምፅሽ እጅግ





ድንቅ ነው። እንደሰማሁሽ ነው ብቃትሽን የተረዳሁት። ለአክስቴ ልጅ እንድትሰሪ እፈልጋለሁ። በሬዲዮ እንድትዘፍኚ ያደርግሻል። ግን ፍላጎቱ አለሽ?"

"እኔ አላውቅም" ነገሩ ተሬዛን አስፈራት።

"ከቤተሰቦችሽ ጋር ተነጋገሪበት።"

"ሐሳቡ ድንቅ መሆኑን አስባለሁ" አለተ የቶሬዛ እናት "ለአንቺ ጥሩ ነገር ነው" አላት አባቷ።

ነገሩን የከላከለችው ሞኒካ ብቻናት። "አንቺ ብቁ ባለሙያ አይደለሽም። እራስሽን አታታይ "አለቻት ሞኒካ። እህቷን ተስፋ ለማስቆረጥ እየሞከረች ነው። ሞኒካ የምትፈራው የቴሬዛን ስኬት ነው። ዘወትር ማብረቅረቅ የምትፈልገው እሷ ብቻ ናት። አምላክ ይህን የመሰለ ድምዕ ለእሷ መስጠቱ ተገቢ አይደለም ስትል አሰበች። እሷ ዝነኛ ብትሆን እኔ ምን እሆናለሁ? እረሳለሁ።

በዚህ ምክንያት ሞኒካ እህቱን እንዳትመክረው ትገፋፋት ጀመር። በሚቀጥለው እሁድ ቀን ማዳም ኔፍ አስቆሟትና እንዲህ አሏት "የአጎቴን ልጅ አነጋግሬዋለሁ። ድምፃችን መስማት ፈልጓል። እሮብ ዘጠኝ ሰአት ላይ ይጠብቅሻል።

እሮብ እለት ግራ የተጋባችው ቴሬዛ ኒስ የማገኘው ስቱዲዩ በመምጣት ከዳይሬክተሩ ጋር ተገናኘች።

"ሉዊስ ቦኔት እባላለሁ" አላት በእርጋታ። "አምስት ደቂቃ ስጥቼሻለሁ።

የቴሬዛ አካላዋ አቋም ፍርሀት አጫረበት። አክስቱ ከዚህ በፊት ብቃት ያላቸው ሰዎች ልካለታለች።

ማዕድ ቤት እንድትቀመጥ እነግራታለሁ። ግን እንደማያደርገው ያውቀዋል። ችግሩ አክስቱ ሲበዛ ባለፀጋ ናት። ብቸኛ ወራሿም እሱ ብቻ መሆኑ ነው።

ቴሬዛ ወደ ጠባቧ የቀረፃ ክፍል ተከትላው ወረደች።

"ከዚህ በፊት በተለየ ሁኔታ ዘፍነሽ ታውቂያለሽ?"

"አላውቅም ጌታዬ" ግራ መጋባቷ አስጨንቋታል። ለመውጣት ቃጣት።

"ፒያኖ የሚጫወቱት ሰዎች ስላልመጡ በድምፅ ብቻ ትዘፍኛለሽ።

"እሺ"

"እኔ መቆጣጠሪያው ክፍል እገባለሁ። አንድ ዘፈን የምትጫወቺበት ጊዜ እሰጥሻለሁ"

"ጌታዬ እኔ ምን ማድረግ . . . ?"

ጥሏት ሔዷል። ምን እንደምትዘፍን አታውቅም።

ከዚህ መውጣት አለብኝ።

የሉዊስ ድምፅ ከሆነ ቦታ ተሰማት። "ሙሉ ቀን መዋል የለብኝም"

"አዝናለሁ እኔ . . .አልቻልኩም።"

ዳይሬክተሩ ጊዜውን ስላባከነችበት ሊቀጣት ፈለገ።

"ትንሽ ቃላት" በማለት አነሳሳት። ፍላጐቱ ለአክስቱ ሪፖርት የሚያደርገው ነገር ማግኘት ብቻ ነው። ከዚህ በኋላ ወደ እሱ መላኳን ታቆማለች።

ወንበሩ ላይ ደገፍ ብሎ ሲጋራ ለኮሰ። አራት ሰአት አለፈ። ሚስቱ እየጠበቀችው ነው። ለውሽማውም የሚደውልበት ጊዜ አያጣም።

ድምጿን ባለማመን ደጋግሞ ሰማው። ነፍስ የሚሰርቅ ድምፅ ነው ያላት። ብቸኝነትን፣ ቅስሙ የተሰበረ ሰው ስሜትን የቀን ህልምን የሚገልፅ ነው። አይኑ በእንባ ተሞላ። ውስጡ የሞተው ርህራሔ ነፍስ ዘርቶ ተነሣ። የተናገረው ነገር ቢኖር "እየሱስ ክርስቶስ! እስከ አሁን የት ነበረች?" የሚል ነው።

በቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች በጠቅላላ የድምፁን አቅጣጫ ተከትለው ወደ ስቱዲዮው መጡ። ልብ የሚሰርቀውን እና ለፍቅር የሚያነባውን ድምፅ እነሱም እያነቡ አዳመጡት።

ዘፈኑ እንዳለቀ ከዝምታ በኋላ ከሰዎቹ መሐል የነበረች አንዲት ሴት "ማንም ትሁን ማን እንዳትለቋት" አለች።

ሉዊስ ቦኔት ከስቱዲዮው እየተጣደፈ ወጣ።

ቴሬዛ ለመሔድ እየተዘጋጀች ነበር።

ረጅም ጊዜ ስለወሰድኩብህ አዝናለሁ። እየህ እኔ በፍፁም . . ."





"ቆጭ በይ ማሪያ"

"ቴሬዛ ነኝ"

"ይቅርታ" አለና በረጅሙ ተነፈሰ። "ዘወትር ቅዳሜ ምሽት የሙዚቃ ፕሮግራም እናስተላልፋለን"

"አውቃለሁ። አዳምጣለሁ"

"የዚህ አካል ብትሆኚ ምን ይሰማሻል?" የሰማችውን ነገር ባለማመን አተኩራ አየችው።

"ልትቀጥረኝ ትፈልጋለህ ማለት ነው?"

"በዚህ ሳምንት ጀምሪ። ከትንሹ እንድትጀምሪ እናደርግሻለን። ለአንቺ ትልቅ መተዋወቂያ ነው"

እውነት ከሆነ ጥሩ ነው። ለዘፈኔ ሊከፍሉኝ ነው።

"ሊከፍሉሽ ነው? ምን ያህል? ስትል ሞኒካ ጠየቀቻት።

"ላውቅም። ግድ የለኝም።" አስፈላጊው ነገር የሆነ ሰው ፈልጐኛል" ለማለት ፀፀትና መናገሩን ተወችው።

"ድንቅ ዜና ነው። እናም በሬዲዮ ልትቀርቢ ነው።" አላት አባቷ።

እናቷ ቀድማ እቅድ አዘጋጅታለች።

"ጓደኞቻችን በጠቀላላ እንዲሰሙ እንነግራቸዋለን። እንዴት ድንቅ እንደሆንሽ እንዲፅፋልሽም እና ደርጋለን።"

ቴሬዛ ሞኒካ የሆነ ነገር እስክትናገር ጠበቀቻት። አትችይም ልትላት ትችላለች። ቴሬዛ ግን ድንቅ ናት።

ነገር ግን ሞኑካ ቃል አልተነፈሰችም። ነገሩ ሁሉ በፍጥነት መፈፀሙን አሰበች።

ተሳስታለች።

ቴሬዛ ቅዳሜ ምሽት በሬዲዩ ጣቢያው ተገኝታለች። ግን ፍርሃት ወሯታል።

ሞኒካን በጥርጣሬ ተመለከታት።

"እሷ እህቴ ነች" አለች ሞኒካ" ቴሬዛ ትባላለች"

ፊቱ ሲለዋወጥ ተመለቱት። ከመገረም ወደ አለማመን ተቀየረ።

"ዘፋኟ አንቺ ነሽ?"

"አዎ"

ወደ ሞኑካ ዞሬ "አንቺስ . . ."

ሞኒካ ፈገግ ብላ "እህቷ ነኝ" አለችው

ቴሬዛን በድጋሚ እየተመለከታት አጠናት። ጭንቅላቱን በአግራሞት ነቀነቀ "አዝናለሁ" አላት ቴሬዛን። "አንቺ በጣም ..." ቃሉን ማውጣት አቃተው። "አንቺ በጣም ወጣት ነሽ። ይቅርታ ካደረግሽልኝ ወደ ፓሪስ መመለስ አለብኝ።" እያዩት ወጥቶ ሔደ። የሞኒካ ተንኮል ሰራላት።

ቴሬዛ ለመጨረሻ ጊዜ የዘፈነችው ያን ጊዜ ነው። ሉዊስ ቦኔት ሊያግባባት ቢሞክርም ልቧ ተሰብሮ ነበር።

እህቴን ካዩ በኋላ እኔን እንዴት ይፈልጉኛል? በጣም አስቀያሚ ነኝ ስትል አሰበች።

በህይወት እስካለች ድረስ የጃኩዊስ አስተያየት አትረሳውም። በዚህ ደረጃ ማለም አልነበረብኝም ስትል አሰበች። እግዚአብሔር ነው የቀጣኝ በማለት ተፅናናች። ከዚህ በኋላ ከቤተክርስቲያን ውጭ ዘፍና አታውቅም።

በሚቀጥሉት አስር አመታት ቆንጆዋ ሞኒካ በደርዘን የሚቆጠሩ የጋብቻ ጥያቄዎች ቢቀርቡላትም ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነችም። አባቷ ምን እንደምትፈልግ ሲጠይቃት እዚህ እንዳስጠላትና ፓሪስ መሔድ እንደምትፈልግ ነገረቻቸው። "የእኔ ህልም ያለው ፓሪስ ነው" አለች።

ቴሬዛ እና ሞኑካ አብረው ወደ ፓሪስ ተጉዘው በትንሽ ሆቴል አብረው መኖር ያዙ። ሁለቱ ፓሪስን የተመለከቱት በራሳቸው መንገድ ነው። ሞኒካ የምሽት መዝናኛ ቦታዎችን ስታዳርስ ቴሬዛ በበኩሏ ቤተክርስቲያን የመፅሐፍና አበባ መሸጫ ቦታዎችን ተመለከተች። ቴሬዛ ፓሪስን ወደደቻት። ነገር ግን ሞኑካ እንድታውቅባት አልፈለገችም። እሷ ካወቀች ሁሉም ነገር ያበቃለታል።





ወደ ቤት እንደተመለሱ "የሚሆነኝን ሰው አላገኘሁም" በማለት ተናገረች።

"አንቺን የሚፈልግ ሰው አላገኘሽም?" ሲል አባቷ ጠየቃት።

"አላገኘሁም" አለችው"

ከአመት በኋላ ሞኒካ ወደ ፓሪስ ለመመለስ ወሰነች።

"እቃዬን ላዘጋጅ" አለች ቴሬዛ

ሞኒካ አንገቷን ነቀነቀች።" አይሆንም! አሁን ብቻዬን ነው መሔድ ያለብኝ።"

እናም ሞኒካ ወደ ፓሪስ በረረች። ቴሬዛም ቤቷ ተቀምጣ ቤተክርስቲያን መመላለሷን ቀጠለች። ለእህቷ አብገዝታ ትፀልያለች። አንድ ቀን አስደናቂ ነገር ተከሰተ። ምክንያቱም ነገሩ የተከሰተው ቴሬዛ ላይ ነውና ከሙ ፊውል ጊዶት ይባላል።

ዘወትር እሁድ ቤተክርስቲያን በመገኘት ቴሬዛ ስትዘምር ያዳምጣል። ይህን የመሰለ ነገር ሰምቶ አያውቅም። "ልተዋወቃት ይገባል" አለ ለራሱ።

በሚቀጥለው ሰኞ ጠዋት ወደ ገበያ ስትወጣ ራውልን አገኘችው። ቴሬዛን ሲመለከት ፊቱ በራ። "ዘፋኟ"

ትኩር ብላ እያየችው "ምን አልክ?"

"ትላንት ቤተክርስቲያን ውስጥ ስትዘምሪ ሰምቼሻለሁ። ድንቅ ነሽ" መልከ መልካምና ረጅም ነው። ልብስ በመስፋት ያተዳደራል። የሚወደድ ገፅታ አለው። በሰላሣዎቹ መጀመሪያ ሲገኝ ከቴሬዛ ሁለት አመት ቢበልጥ ነው።

ቴሬዛ በሁኔታው ተገረመች። ትኩር ብላ ስታየው ልቧ እንደከበሮ ደለቀባት።

"አመሰግናለሁ" አለች ቴሬዛ። "ሶስት ሜትር ጨርቅ ፈልጌ" ነበር ፊውል ሳቀ። "ደስ ይለኛል፡ በዚህ በኩል"

ቴሬዛ ትኩረት ማድረግ አቃታት። በወጣቱ ውበት ተማርካለች።

ቴሬዛ የገዛችውን እቃ እየጠቀለለላት ሳለ በድንገት "አዲስ ነህ አይደል?" አለችው።

"ደስ ይለኛል" አለችው::

በሚቀጥለው ቀን ሲገናኙ ከሰአት በኂላ ስራ ማስፈቀዱን ነገራት እንደ ልጅ እየቦረቀ ነው:: ወደ ኒስ ተያይዘው በረሩ:: እያከነፉት ነው::

በሚቀጥለው ቀን ሞኒካ ከፓሪስ ትመለሳለች:: ራውልን ለሞኒካ ያዘጋጀችው ስጦታ ነበር:: ለእሷ እንደማይሆናት አውቃዋለች:: እውነት የሆነውንና የማይቻለውን ነገር ከህይወት ልምድ ለይታ አውቃዋለች:: መኪናውን የሚያከንፈውን ሰው እየተመለከተ የማይመስለውን ህልሟን ልትገድበው እየሞከረች ነው::

ኒስላይ ምሳቸውን ሲበሉ የባጥ የቆጡን እያወሩ ነው:: ለእፍታ ወሬያቸውን ማቆም አልቻሉም:: እሱ ይጠይቃታል:: እሷ ትመልሳለች:: ፍላጐቱን፣ አመለካከቷንና ስሜቷን ለማወቅ ፈልጓል:: ልባቸው የተገናኘ መስሎታል:: ቴሬዛ የሚፀፅታትን አገር ላለማድረግ እየተጠነቀቀች ነው::

"እህቴ ነገ ከፓሪስ ትመለሳለች:: አብረሽኝ እራት ትበያለሽ? ላስተዋውቅሽ እፈልጋለሁ"

"ደስ ይለኛል" አለችው ::

በሚቀጥለው ቀን ሞኑካ ወደ ቤት ስትመጣ ፈጥና ልትቀበላት ወጣች:: ቴሬዛ በችኰላ "ፓርስ ላይ የምትወጂው ሰው አገኘሽ?" ስትል ጠየቀቻት::

"ተመሳሳይ አሰልቺ ሰዎች" አለቻት::

አሁን እግዚአብሔር የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጥቷል::

"ነገ እራት ላይ አንድ ሰው አስተዋወቅሻለሁ" አለቻት ቴሬዛ "እንደምትወጂው ተስፋ አደርጋለሁ::" ለእሱ ምን ያህል እንደምጨነቅለት ማንም እንዲያውቅ አልፈልግም ስትል አሰበች::

በዛው ምሽት አንድ ሰአት አካባቢ ቴሬዛ ሞኒካ እና ቤተሰቦቻቸው ራውልን ለራት እየጠበቁት ነው::

"እነዚህ አባት እና እናቴ ናቸው ራውል"

"እንደምን ናችሁ?"

ቴሬዛ በረጅሙ ተነፈሰች:: "እሷ ደግሞ እህቴ ናት:: ሞኒካ ትባላለች::"





"እንደምን ነህ?" የሞኒካ አቀራረብ ትህትና የተሞላ ነው ሌላ ምንም ነገር አይታይበትም::

ቴሬዛ ራውል በሞኒካ ውበት ይማረካል ብላ እየጠበቀች ነው::

"ዝምታው" በዛ::

ቴሬዛ ያለችበት ሆና ትንፋሿን ውጣ በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን ነገር እየጠበቀች ነው:: ሞኒካም ራውልም ያውናቸው:: ራውል የሚያየው ቴሬዛን ብቻ ነው::

"ዛሬ አምሮብሻል ቴሬዛ"

በድንጋጤ "አመሰግናለሁ" አለችው::

ቴሬዛ ያሰበችው አልተሳካላትም:: የማይሆን ነገር እየሞከረች ነው:: የሚፈልገው እሷን ነው:: ማመን አቃታት:: በድጋሚ እንዳትጐዳ ፈርታለች:: መገለሷ የፈጠረባትን ስሜት ደብቃው ኖራለች:: አሁንም በደመ ነፍሷ ያንኑ ነገር ለመድገም ብትሞክርም ራውልን መቋቋም አቃታት:: እየተፈታተናት ነው::

"ልጃችሁ ስትዘፍን ሰምቻታለሁ "አለ ራውል" ልዩ ናት" ቴሬዛ ልቧ ደነበረ::

"ሁሉም ሰው የቴሬዛን ድምፅ ይወደዋል::" አለች ሞኒካ ረጋ ብላ:: ከባድ ምሽት ነው:: ዋናው ነገር መምጫው ደርሷል::

እራት በልተው እንዳበቁ ራውል "ቤታችሁ ያምራል" አለና ወደ ቴሬዛ ዞሮ "መናፈሻውን ልታሳይኝ ትችያለሽ?"

ቴሬዛ ሞኒካን አየቻት:: የእህቷን ትክክለኛ ስሜት ለማጥናት እየሞከረች ነው ሞኒካ ያው ነች::

"እውር ደንቆሮና ጋግርታም ሆናለች::" ስትል ቴሬዛ አሰበች:: ሞኒካ እየዞረች አጣማጆቿን ብትፈልግም ማግኘት አልቻለችም:: ይህ ማለት ስህተቱ የወንዶቹ ሳይሆን የእሷ ነው ማለት ነው:: የምትፈልገውን አታውቅም::

ቴሬዛ ወደ ራውል ዞራ "ወድጄዋለሁ" አለችው::

"እግዚአብሔር በዚህ አያምንም:: አነጋግሪው :: እሱ ይነግርሻል::

ቴሬዛ ግድግዳውን እያዩት ቆማ ቀረች:: ቄሱ ሲወጡ አላስተዋለችም::

በሚቀጥለው ቀን ያለፈው ስሜቷ ተመለሰላት:: ቤተክርስቲያን ሔዳ አምላኳን ይቅርታ ለመነች:: መንፈሷ ተመልሶ ታደሰ በእሷ ደካማነት ነው አምላኳን የሸነገለችው:: እሱ አልተዋትም::

ቄሱ ቤሬንዶ ውስጥ ነበሩ:: "ምን እንደማደርግ አላውቅም:: እምነቴ ሞቷል አለቻቸው:: ይዘዋት ገብተው ለአንድ ሰዓት ያህል አወሯት:: አባቷም ትተዋት ወደአገራቸው ተመለሱ:: ደህና እንደምሆንም ቃል ገባችላቸው::

ቴሬዛና ቄስ ቤሬንዶ በተደጋጋሚ መገናኘት ጀመሩ:: እጅግ አዘኑላት:: እየቆየች ተስፋዋ ተመለሰ:: ከረጅም ጊዜ በኋላ ውስጧ ነፃ መሆኑን ተረዳች::

ቄስ ቤሬንዶ አንድ ቀን "ከዚህ አለም እምነት ከሌለሽ በሚቀጥለው አለም ማመን አለብሽ" አሏት:: "እየሱስ ሊቀበልሽ ይጠብቅሻል:: መሄጃ እንደሌላት ስትነግራቸ ው ወደ ቤት መመለስ እንደምትችል ነገሯት::

"አልፈልግም"

"እዚህ መቆየት ትችያለሽ"

"እዚህ?" አለች ግራ በመጋባት::

"እዚህ አካባቢ የሴቶች ገዳም" አለ በማለት ዝርዝሩን አስረዷት:: አነጋገራቸው ልቧን አሞቀው:: ገዳም መግባት እንደምትፈልግ ነገረቻቸው::

"መመለስ የማይታሰብ ነው" አለች::

"እሷም መመለስ አልፈልግም" አለች::

በሚቀጥለው ቀን ቄስ ቤሬንዶ ወደ ገዳሙ ወስደው ከእማሆን ቤቲና ጋር አገናኟት:: ትተዋቸው ወጡ::

ቅጥር ግቢውን ስትረግጥ አወቀችው:: በመጨረሻ ስትል በውስጧ አሰበች:: በመጨረሻ::

ለአባቷና እናቷ ስልክ ደወለችላቸው::





"ሐሣብ ገብቶኝ ነበር" አሏት:: እናቷ "ወደቤት መቼ ትመለሻለሽ"

"እቤቴ ነው ያለሁት::

ቴሬዛ የምንኩስና ስነ ሥርዓቱን በማጠናቀቅ ገዳም ተቀላቀለች::

አሁን ከሰላሣ አመት በኋላ ትታው ወደነበረው አለም ተመለሰች:: ጫካ ውስጥ ተጋድማ ከአድማስ ባሻገር የምትወጣውን ፀሐይ እያየች ነው:: ሲስተር ቴሬዛ በሐሣቧ "ገዳም የገባሁት ለተሳሳተ አላማ ነበር:: ከአምላክ መሸሽ የለብኝም:: መራቅ የአለብኝ ከአለም ነው:: አምላክ የልቤን ያውቃል" አለች::

ስልሳ አመቷ ሲሆን ያለፉትን ሰላሣ አመታት በደስታ ኖራለች:: አሁን በድንገት አለም ተቀላቀለች::

እውነት የሆነውንና ያልሆነውን ማወቅ ተሳናት:: ያለፈውና የአሁኑ ነገር ተሳሰሩባት:: ይህ ነገር በእኔ ላይ ለምን ተፈጠረ? አምላክ በእኔ ላይ ያለው እቅድ ምንድን ነው?

# ምዕራፍ አስራ ሦስት

ለሲስተር ሜጋን ጉዞው ጀብዱ ሆኖባታል፡፡ አዲስ ነገርና ድምፅ ዙሪያዋን ከቧታል፡፡ እየተገረመች ነው፡፡

የቡድን አባሎቿ አስደንቀዋታል፡፡ አምፓሮ ጂሮን አስፈሪና ኃይለኛ ሴት ናት፡፡ ከሁለቱ ወንዶች እኩል ትራመዳለች፡፡ ደግሞም ሴትነቷ ያስታውቅባታል፡፡

ፌሊክስ ካርፒዮ ማራኪ ነው፡፡

ከቡድኑ አባላት ሜጋንን የሳባት ጀሚ ሚሮ ነው፡፡ ውስጡ ያለው ጥንካሬ ፊቱ ላይ ይነበባል፡፡ በአሳማው ፅኑ እምነት አለው ልክ በገዳም እንዳሉት መነኩሳት፡፡

በጉዞአቸው ወቅት ከሜጋን በስተቀር ሶስቱ የጉዞ እቃቸውን ተከፋፍለው ከመሣሪያቸው ጋር ተሸክመው ተንቀሳቀሱ፡፡

"አንዱን የመኝታ ከረጢት ልያዝ" በማለት ሜጋን ጠየቀች፡፡

ጀሚ ሚሮ በመገረም ካያት በኋላ "ጥሩ ነው ሲስተር" አላት

ከረጢቱን አቀበላት፡፡ ከጠበቀችው በላይ ከባድ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን አልተናገረችም፡፡ ቅሬታም አላቀረበችም፡፡

በጨለማ ቆንጥር እየሰበሩ ተጓዙ ትንኝ ይነክሳቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? ስትል ሜጋን ራሷን ጠየቀች፡፡ ተገረመችም፡፡ መነኩሳቱ ተበታትነዋል፡፡ እሷም ከማታውቃቸው ሰዎች ጋር መጓዟ ምቾት አልሰጣትም፡፡

ትንሽ ያወራሉ፡፡ ብዙ ያንሾካሹካሉ፡፡

"ቫላዶሊድ ላይ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል? በጉሽ ግጥሚያው ወቅት "አዎ ጀሚ፡፡ ሩቢዩ እና ቶማስን ባንኩ አጠገብ በጉሽ ግጥሚያው ወቅት እናገኛቸዋለን"

"ጥሩ" ለላርጐ ኮርቴዝ እንዳቀበለን መልእክት ስደድላት፡፡ ቀኑን ግን እንዳትነግረው፡፡

"እሺ"





ሜጋን ስማቸው የተጠራው ሰዎች እነማን ናቸው? ስትል አሰበች፡፡ በጉሽ ግጥሚያው ወቅት ባንኩ ጋር ምን ያደርጋሉ? መጠየቅ ፈልጋ ተወችው፡፡ ብዙ ጥያቄ እንደማይፈልጉ ገባት፡፡

ሊነጋጋ ሲል ከሸለቆው ስር ጭስ ታያቸው፡፡

"እዚህ ጠብቁኝ" አለ ጀመ በሹክሹክታ፡፡ "ዝም በሉ"

ጫካው ውስጥ ገብቶ ተሰወረ፡፡

ሜጋን "ምንድን ነው?" አለች፡፡

"አፍሽን ዝጊ!" አለቻት አምፓሮ ጂሮን"፡፡

ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ጀመ ተመለሰ፡፡

"በወታደሮች፡፡ ተከበናል፡፡"

ወደ ኋላ ግማሽ ማይል ያህል ተመልሰው ተጓዙና መንገዳቸውን ቀይረው ጉዞአቸውን ቀጠሉ፡፡

ሜጋን "ፖሊሶች ለምንድን ነው የሚፈልጓቸው?" ስትል ጠየቀች፡፡

ጀሚ ሚሮ "እንዳልተያየን" መናገር አለብን አለ፡፡

መልሱ አረካት፡፡ ለጊዜው ስትል አሰበች፡፡ ስለዚህ ሰው ብዙ ማወቅ ፈልጋለች፡፡

ከግማሽ ሰአት ጉዞ በኋላ መጠለያ መርጠው አረፉ፡፡ "ፀሐይ እየወጣች ነው፡፡ አስኪመሽ እዚህ እናሳልፋለን፡፡ "አለ ጀሚ ሜጋንን እያየ፡፡ "ዛሬ ምሽት ፈጠን ብለን መጓዝ አለብን፡፡"

አንገቷን በመነቅነቅ "በጣም ጥሩ" አለች

ጀሚ የመኝታ ከረጢቱን አወጥቶ ዘረጋው፡፡ አምፓሮ ጂሮን አጠገቡ ተኛች፡፡

ፊላክስ ካርፒዮ ሜጋንን "የእኔን ወስደሽ ተኚ ሲስተር እኔ መሬት ላይ እተኛለሁ"

"እሱ የአንተ ነው አልፈልግም" አለች ሜጋን፡፡

ሰላም ካንቺ ጋር ይሁን አሏት በመጨረሻ፡፡

አስራ አምስት አመት ሲሞላት የሜጋን ውበት ልብ የሚሰርቅ ሆነ፡፡ አንድ ቀን ማርቸዲስ ኤንጂልስ በድንገት ቢሮአቸው አስጠሯት፡፡ ቄስ ቤርንዶ አብረዋቸው ነበሩ፡፡

"ሰላም አባቴ"

"ሰላም ነሽ የእኔ ውድ ሜጋን"

ማርቸዲስ ኤንጅልስ "ችግር እንደገጠመን ስነግርሽ እየፈራሁ ነው ሜጋን"

"እ?" አለች የሰራችውን ጥፋት እያሰበች፡፡

ኃላፊዎ "እዚህ ለመኖር የእድሜ ገደብ ተቀምጧል፡፡ ገደቡ አስራ አምስት አመት ሲሆን አንቺም አስራ አምስት አመት ሞልቶሻል፡፡

ሜጋን ደንቡን በደንብ ታውቀዋለች፡፡ ማሰብ አትፈልግም እንጂ፡፡ ማንም እንደ ማይፈልጋት ታውቀዋለች፡፡

"መልቀቅ አለብኝ?"

ኃላፊዎ ቢያዝኑም ምንም አማራጭ የላቸውም፡፡ በወጣው ደንብ ነው የምንገዛው፡፡ የቤት ሰራተኛ ሆነሽ የምታገለግይበት ቦታ አግኝተንልሻል፡፡

ሜጎን ቃል አልተነፈሰችም፡፡

ቄስ ቤርንዶ "የት መሔድ ነው የምትፈልጊው?"

የሆነ የምትሔድበት ቦታ መኖሩ ታወሳት፡፡

በአስራ ሁለት አመቷ ለተቋሙ እቃ ለመግዛት ወደ ውጭ ስትመላለስ በአቅራቢያቸው ያለውን የሴቶች ገዳም ታውቀዋለች፡፡ ለእማሆይ ቤቲና እቃ ታደርስ ነበር፡፡ ዘወትር ወደ ግቢው ስትገባ ንፅህና ይሰማታል፡፡ ለሜጋን ደግሞ ፍቅር የተሞላ ቤት ነው፡፡

እማሆይ ብሩህ ከሆነችው ወጣት ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን በአመታት ቁርኝታቸው ስለ ብዙ ነገር አውግተዋል፡፡

"ሰዎች ገዳም የሚገቡት ለምንድን ነው? "ስትል ሜጋን ጠየቀቻቸው "በብዙ ምክንያቶች፡፡ ራሳቸውን ለአምላክ ለመስጠት፣ ተስፋ ሲቆርጡ፣ መኖር ሲያስጠላቸው፣ ጠፍተው ይመጣሉ፡፡ አምላክ ደግሞ ለሁሉም ነገር መልስ





ይሰጣቸዋል፡፡

በሜጋን ልብ ተስፋ ብልጭ አለ፡፡ "እኔ የማንም ሆኜ አላውቅም" ስትል ሜጋን አሰበች፡፡ የእኔ እድል ይሄ ነው፡፡"

"ገዳሙን መቀላቀሉ ጥሩ ይመስለኛል፡፡"

ከስድስት ሳምንት በኋላ ሜጋን እቃዋን ጠቅልላ ወጣች፡፡

በመጨረሻ ሜጋን ስትፈልገው የነበረውን ነገር አገኘች፡፡ የእሷ የሆነውንና እሷን የሚመጥናትን፡፡ እነዝህ የእሷ እህቶች ናቸው፡፡ እስካሁን ያላገኘችውን ቤተሰብ አግኝታለች፡፡ ሁሉም በአባታቸው ጥላ ስር አንድ ናቸው፡፡

ሜጋን በገዳሙ የሒሳብ ሰራተኛ ሆና ተቀጠረች፡፡ ሲስተሮቹ የሚጠቀሙበት ጥንታዊ የምልክት ቋንቋ በጣም መሰጣት፡፡ 472 ምልክቶችን ይጠቀማሉ፡፡

ሁሉም ትዕዛዝ በምልክት ይከናወናል፡፡ አንድ መነኩሴ ህይወታቸው ማለፉን ተከትሎ ሜጋን የቀብር ስነስርዓቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ታደማች፡፡ ከ1030 እ.ኤ.አ. አንስቶ ባህሉ አልተለወጠም፡፡ ሻማ ይበራል፣ አበባ ይቀመጣል፣ የምንኩስና ልብሳቸውን እንዳጠለቁ አምረው ይገነዛሉ፡፡ የፀሎት ስነ ስርዓቱ እንደተጠናቀቀ ቀብሩ ይፈፀማል፡፡

ሜጋን በሐሳብ የምትዋጥባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው፡፡ ገዳሙ ፍፁም የሆነ ሰላም ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን ገና ሰላሟ አልተሟላም፡፡ ውስጧ የጐደለው ነገር አለ፡፡ የረሳቻው ነገር እየተመለሰ ይረብሻታል፡፡ በህፃናት ማሳደጊያው ትታቸው ስለመጣቸው ጓደኞቿ ታስባለች፡፡ የውጩ አለም ሁኔታ ያሳስባታል፡፡ ሙዚቃ፣ ዳንሱ እና ሳቁ ይታወሳታል፡፡

ሜጋን ወደ እማሆይ ቤቲና ሄደች፡፡

"ሁላችንም ላይ የሚከሰት ነገር ነው" አሏት፡፡ "ለእሷ ማረጋገጫ ሲሰጧት" ነገሩን ቤተክርስቲያን "የሰይጣን ስራ" ብላ እንደምትጠራው ነገሯት፡፡ አትጨነቂ ልጄ ሁሉም ያልፋል፡፡

እንዳሉት ሆነ፡፡

ልትረሳው ያልቻለችው ነገር የበተሰቦቿን ማንነት የማወቅ ጉጉቷ አለመሞቱ ብቻ ነው፡፡ "መቼም አላውቃቸውም" ስትል ተስፋ በመቁረጥ አሰበች፡፡ በህይወት እስካለሁ ድረስ አይሳካልኝም፡፡

# ምዕራፍ አስራ አምስት
# ኒውዮርክ ሲቲ 1976

ኒውዮርክ በሚገኘው ዋልዶርፍ አስቶሪያ ሆቴል ዙሪያ ሪፖርተሮች አሰፍስፈው ታዋቂ የኪነጥበብ ባለሙያዎችን ይመለከታሉ። ያማረ የእራት ልብስ የለበሱት ኮከቦች ከሊሞዚናቸው እየወረዱ ሶስተኛ ፎቅ ወደ ሚገኘው ቦልሩም እየገቡ ነው።

ሪፖርተሮቹ "ምክትል ፕሬዝዳንት አባክዎ ወደዚህ ይመልከቱ?" ሲሏቸው የፎቶ ካሜራዎች ብልጭታ ፊታቸው ላይ አንፀባረቀ።

"አገረ ገዥ አዳምስ ተጨማሪ ፎቶ ልውሰድ እባክዎ?"

የብዙ አገራት ተወካዩችና ሴናተሮች ተዋቂ ሰዎችና ነጋዴዎች ተገኝተዋል። ሁሉም የተሰበሰቡት የኤለን ስኮትን ስላሳኛ የልደት በአል ለማክበር ነው። እነሱ የሚያከብሩት የስኮት ኢንዱስትሪ ብቸኛ ወራሽ የሆነችውን ኤለን ስኮትን እና የምትመራቸውን የተለያዩ ግዙፍ ተቋማት ነው። በዚህ ምሽት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለበጎ አድራጎት ድርጅት የሚሰጥ ነው።

የስኮት ኢንዱስትሪ በመላው አለም ተስፋፍቷል። ከሀያ አምስት አመት በፊት የድርጅቱ ፕሬዝዳንት የነበረው ሚሎ ስኮት በድንገተኛ የልብ ድካም ህይወቱ ሲያልፍ ሚስቱ ኤለን ስኮት የማስተዳደር ስልጣኑን ጠቅላላ ያዘችው። በአመታት ሒደት የኩባንያውን ትርፍ በሶስት እጥፍ በማሳደግ ታዋቂነቷን አሳይታለች።

የዋልዶርፍ አስቶሪያ ግራንድ ቦልሩም በደንብ አሸብርቋል። በግብዣው ላይ ስድስት መቶ የሚጠጉ እንግዶች ታድመዋል።

የእራት ግብዣው እንደተጠናቀቀ የኒውዮርክ ከተማ አገረ ገዥ ወደ መድረክ ወጡ።

"ክቡር ምክትል ፕሬዝዳንት ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች..." በማለት ኤለንን የሚያሞግስ ንግግር አደረጉ።

ፈገግታና ጭብጨባ አጀባቸው።





የኤለንን ለጋስነት አግዝፈው ተናገሩ። ንግግሩ አስር ደቂቃ ወሰደ። ነገር ግን ኤለን ስኮት እየሰማች አልነበረም። "እንዴ ለምንድን ነው የተሳሳተው" ስትል አሰበች።

ስኮት ኢንዱስትሪ የእኔ ኩባንያ አይደለም። እኔ እና ሚሎ በስርቆት ያገኘነው ነው። እኔ ከእሱ የበለጠ ወንጀለኛ ነኝ። ከአሁን በኋላ ችግር አያመጣም። ምክንያቱም በቅርቡ ሟች ነኝና።

ዶክተሩ የነገራትን ቃል በቃል አስታወሰችው ከላብራቶሪ የወጣውን የሞት ደብዳቤውን አንብቦት ነበር።

"እጅግ ከልቤ አዝናለሁ ወይዘሮ ስኮት። ከዚህ የበለጠ በጨዋነት ልነግርዎት የምችልበት መንገድ የለኝም። ካንሰሩ በመላ አካልዎ ተስፋፍቷል። መከላከል የማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።"

ሆዷ ሲገለባበጥ ተሰማት።

"ምን ያህል ጊዜ እቆያለሁ?"

እያመነታ "ምናልባት አንድ አመት"

በቂ ጊዜ አይደለም። ብዙ የምሰራው ስራ አለኝ። "ስለዚህ ነገር ለማንም እንዳታውራ" አለችው አስረግጣ።

"በፍፁም አላደርገውም።"

"አመሰግናለሁ ዶክተር"

ሐኪም ቤቱን የመልቀቅ ፍላጐት አላሳየችም። የምታስበው ብቸኛው ነገር" ከመሞቴ በፊት ላገኛት ይገባል" የሚለው ሐሳብ ነው።

የአገር ገዥው ንግግር አበቃ።

በመቀጠል ኤለን ስኮትን ከእንግዶቹ ጋር አስተዋወቃት።

ኤለን ስኮት ተነስታ ወደ መድረኩ ወጣች።

"እኔን መመልከት ልክ በመሞት ላይ ያለችን ኮከብ እንደመመልከት ነው። ከአሁን በኋላ እዚህ አልገኝም" ስትል አሰበች።

"ኑ፡፡ ቀላል ነው፡፡ የማስብበት ጊዜ ቢኖረኝ ኖሮ እሮጬ አመልጥ ነበር፡፡" ኖርተን አተኩሮ እያት፡፡ "ወይዘሪት ዱዳሽ አንቺን ብሆን ኖሮ ያንን አልናገርም፡፡

"ለምን? እውነት ነው እኮ፡፡"

ይህንን አልጠበቀም ነበር፡፡ ልጅቷ ያለችበትን ሁኔታ አላወቀችውም፣ ኤለንን የማያስጨንቃት ነገር አውጥታ መናገር ፈለገች፡፡" ሚስተር ስኮትን ታገኘዋለህ?

"አዎ"

"ውለታ ልትውልልኝ ትችላለህ?"

"ከቻልኩ አደርገዋለሁ"

አደጋው በእሱ ጥፋት የተከሰተ አይደለም፡፡ እኔንም እንዳድነው አልጠየቀኝም፡፡ ግን . . ." የሆነ ነገር ተሰማት፡፡

"በቃ ተወው"

ነገሩ ተጀመረ ሲል ኖርተን አሰበ፡፡ ምን ያህል ሽልማት ፈልጋ ይሆን? ገንዘብ ነው? ጥሩ ስራ? ምንድን ነው?" እባክሽ ቀጥይ ወይዘሪት ዱዳሽ"

አመነታች፡፡ "እውነታው በቂ ገንዘብ የለኝም፡፡ ለህክምና ወጪ ሳነሳለት ደግሞ ሁሉም ያበቃል፡፡ የሆስፒታሉን እዳ መክፈል የምችል አይመስለኝም፡፡ ሚስተር ስኮትን ማስቸገር ባልፈልግም የሆነ ብድር እንዲያመቻችልኝ እፈልጋለሁ፡፡ እዳዬን መልሼ እከፍላለሁ፡፡" የኖርተን ፊት በአድናቆት ተሞላ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ አነጋገሬ ያልተገራ ይሆናል፡፡ ለሽርሽር የቆጠብኩት ገንዘብ ነበር አደጋው ሁሉንም ነገር አበላሸው፡፡

ንፅህናዋ አስደነቀው፡፡ የዚች አይነት ንፁህ ልጅ ካየ ብዙ ዘመን ሆኖታል፡፡

ሙያዊ ግዴታውን ዘንግቶ አጠገቧ ተቀመጠ፡፡ እጇን ይዞ "የመልካም ወዳድነት ስሜት እንደተሰማውና ስለገንዘብ እንዳታስብ ቃሉን ሰጣት፡፡ መግለጫውን እንዴት ማጠናቀቅ እንዳለባቸው ከነገራት በኋላ ይዟት ወጣ፡፡ እውነቱን ሳይሆን መናገር ያለባትን አስረዳት፡፡

ጋዜጣዊ መግለጫውን በሚፈለገው መንገድ ካጠናቀቀች በኋላ ስለደከማት ገብታ ተኛች፡፡





በዛው እለት ረፋድ ላይ ሚሎ ስኮት ሊጎበኛት መጣ፡፡ በጣም ተገረመች፡ ፡ ቤቱ ኒውዮርክ መሆኑን ስምታለች፡፡

"ጋዜጣዊ መግለጫው በጥሩ ሁኔታ መጠናቀቁን ሰምቻለሁ፡፡ ጀግና ነበርሽ፡፡"

"ሚስተር ስኮት የምነግርህ ነገር አለኝ፡፡ እኔ ጀግና አይደለሁም፡፡ አንተን ማትረፍ ማስታወስ አላቆምኩም፡፡ ግን . . . ያደረኩት"

"አውቄዋለሁ ሳም ኖርተን ነግሮኛል"

"ደህና በመቀጠል . . ."

ኤለን የተለያዩ የጀግንነት መገለጫዎች አሉ፡፡ እኔን ስለማትረፍሽ አታስቢ ግን በደመነፍስ አድርገሽዋል፡፡ ራስሽን ከማዳን ይልቅ እኔን ማዳኑን አስቀድመሻል፡፡"

"ያንቺ እዳ አለብኝ"

"ምንም እዳ የለብህም"

"አንድ ነገር እንድታውቅ እፈልጋለሁ"

"ስለሆስፒታል ክፍያው መጨነቅሽንም ሳም ጨምሮ ነግሮኛል፡፡ ነገ ትወጫለሽ፡፡ እራት ልጋብዝሽ?"

አልገባውም ስትል አሰበች፡፡ የእሱን ልግስና አልፈልግም፡፡ ሀዘኔታውንም አልመኘም፡፡ እዳ የለብህም ስልህ እኔም እዳ የለብኝም፡፡ ስለሆስፒታሉ ክፍያ አመሰግናለሁ፡፡

"ጥሩ፡፡ አሁን እራት ልጋብዝሽ እችላለሁ?"

ነገሩ የተጀመረው እንዲህ ነው፡፡ ሚሎ ስኮት ጋሪ ላይ ለሳምንት ቆየ ኤለንንም በየቀኑ ያገኛት ነበር፡፡

የኤለን አባት እና እናት አስጠነቀቋት፡፡ "የቀረበሽ የሆነ ነገር ፈልጎ ነው" አሏት፡፡

ሚሎ ስኮት ሐሳቧን አስቀየራት፡፡ ድንቅ ሰው ነው፡፡ ከእሷ ጋር በመሆኑ እጅግ ተደስቷል፡፡ እሱ አይን አፋር ሲሆን እሷ በበኩሏ ግልፅ ነች፡፡ ሚሎ ቀደም

"የእኛ መትረፍ ተአምር ነው" አለ ሚሎ::

ተአምር ነው:: ነገር ግን ለሌሎቹ አይደለም::

ኤለን ስኮት የሚነዳውን አውሮፕላን እያየች የሆነ ነገር አሰበች::

"ሚሎ?"

"አቤት? እየሰማት አይደለም::

"እድል ነው"

"ምን"

"ስኮት ኢንዱስትሪ አሁን የአንተ ሆኗል::"

"እኔ አልፈልግም . . ."

"ሚሎ እግዚአብሔር ሰጥቶሀል" አለችው:: "እድሜህን ሙሉ ወን ድምህን አገልግለሀል:: ሀያ አመት ለፍተሀል አሁን ጊዜው ያንተ ነው::"

ኤለን "በድናቸው እዛ ወድቆ እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ታስቢያለሽ?

"አውቃለሁ:: ግን እኛ አልገደልናቸውም:: አሁን የእኛ ተራ ነው:: ሚሎ:: ኩባንያውን የሚጠይቅ ማንም የለም::"

ልክ ይህን ስትናገር የህፃን ለቅሶ ሰማች:: እርስ በእርሳቸው ተያዩ::

"ፓትሪሺያ ነች:: በህይወት አለች:: አምላኬ::"

ተአምር በሚመስል መልኩ ምንም ነገር አልነካትም::

ሚሎ አንስቶ አቀፋት:: "አይዞሽ የእኔ ውድ" አላት::

ኤለን አጠገቡ ቆማ "ሞታለች አላልከኝም ነበር::

"ራሷን ስታ ነበር"

ኤለን ስኮት እያየቻት "ከሌሎቹ ጋር አብራ መሞት ነበረባት::" አለችው::

በድንጋጤ ተመለከታት:: "ምንድን ነው ያልሽው?"





"ባይሮን ሁሉንም ነገር የተወው ለፖትሪሺያ ነው:: ለሚቀጥሉት ሀያ አመታት የእሷ አሳዳጊ ትሆናለህ:: ስታድግ ደግሞ ልክ እንደ አባቷ አሽከሯ ታደርግሀለች:: ያንን ነው የም ትፈልገው?"

"ዝም" አለ::

"የዚህ አይነት እድል መቼም አይገጥመንም::" አለችው ልጅቷን እያየች::

አይቶባት የማያውቀውን አተያይ ከአይኗ ላይ አነበበ::

ራሷን አላወቀችም ሲል አሰበ:: "ስለ አምላክ ብለሽ:: ኤለን ምንድን ነው የምታስቢው?"

"አላውቅም" አለችው "የሆነ ነገር ማድረግ አለብን:: ሚሎ የሆነ ቦታ ልንተዋት ይገባል:: ፖይሰቱ አቪላ አቅራቢያ ነን ብሎ ነበር:: እዛ ደግሞ ብዙ ቱሪስቶች ይመጣሉ:: ልጅቷን ከአደጋው ጋር አያይዞ የሚያስባት አይኖርም::

"ኤለን"

"ይህን ያደረገው አምላክ ለእኛ ሲል ነው"

"ደህና ነች" አለች ኤለን:: "አንዱ ገበሬ ቤት አጠገብ እናስቀምጣታለን:: እነሱ ያሳድጓታል::

"ይህን ማድረግ አልችልም" አላት::

"ከወደድከኝ ለእኔ ስትል ታደርገዋለህ:: መምረጥ አለብህ ሚሎ:: ከእኔ ጋር ትኖራለህ ወይም እድሜ ልክህን የወንድምህን ልጅ ታገለግላለህ"

"እባክሽ እኔ . . ."

"ትወደኛለህ?"

"ከህይወቴ አብልጬ" አላት በቀላሉ::

"ከሆነ አረጋግጥልኝ"

አውሮፕላን ከወደቀበት ተራራ ግርጌ ወዳለው አቅጣጫ ወረዱ:: ከሶስት ሰአት በኋላ አቪላ አቅራቢያ የሚገኝ የገበሬ ቤት አጠገብ ሚሎና ኤለን ደረሱ:: ገና አልነጋም::

ይላቸዋል፡፡ ይህ የእሳቸው ሐሳብ ነው፡፡

ሩቢዩን እየተመለከቱት "ደህና ነኝ" አሉ ሲስተር ቴሬዛ፡፡ ሸለቆውን አቋርጠው አንዲት አነስተኛ መንደር ደረሱ፡፡ ገበሬዎች ኩልል ያለ ንፁህ ወራጅ ወንዝ ስር የሚታጠቡ ሰዎችን ተመለከቱ፡፡

ሰላም የሚሰጥ እይታ ነው ሱል ሩቢዩአሰበ፡፡ ትቶት የመጣው እርሻው ትዝ አለው፡፡ ስፔን እንዲህ ነበረች፡፡ በምብና ሞት የሌለባት፡፡ ይህ ሰላም ተመልሶ ይመጣ ይሆን?

"ጉዞ አድካሚ ነው፤ ውኃ መጠጣት እንችላለን?"

"በትክክል፡፡ ራሳችሁን እርዱ"

"እሺ"

ውኃው ንፁህና ልብ የሚያረካ ነው፡፡

"እንሒድ"

ሩቢዮ ከዚህ ቦታ መሔድ አልፈለገም፡፡

ሁለቱ ሴቶችና አጃቢዎቻቸው አሁንም እየተጓዙ ነው፡፡ አትክልቱና ፍራፍሬው በሸለቆው ውስጥ አፍርተው ይታያሉ፡፡ የዶሮዎች፣ ፍየሎችና አሳማዎች ድምፅ ይሰማል፡፡

ሩቢዮ እና ቶማስ ቀደም ብለው እየተጓዙ ነው፡፡ በፀጥታ እየተነጋገሩ ነው፡፡

ሲስተር ቴሬዛ ስለእሳቸው የሚያወሩ መሰላት፡፡ ፈጠን ብላ ተጠግታ የሚነጋገሩትን ለማዳመጥ ሞከረች፡፡

"እኛን ለያዘ 500 ሺ ፔስታስ መንግስት ይሰጣል፡፡ ኮሎኔል አኮካ ደግሞ ጀሚን ለያዘለት ከዚህ በላይ ይከፍላል፡፡ ጭንቅላቱን ሳይሆን . . .ነው የሚፈልገው" ካሉ በኋላ ሁለቱም ተያይዘው ሳቁ፡፡

ሲስተር ቴሬዛ ንግግራቸውን ካዳመጠች በኋላ ጥርጣሬዋ ጨመረ፡፡ እነዚህ ሰዎች ነፍሰ ገዳይ ናቸው፡፡ ስራቸው የሰይጣን ነው፡፡ አምላክ ወደ ቤቴ ይመልሰኛል በማለት አሰቡ፡፡

የራውል ጊራዶት ሁሉ ነገር መልሶ ትዝ አላት፡፡ ፈገግታውን መቼም





ቢሆን አትረሳውም፡፡

"ድምፅሽ ያምራል፡፡"

ይቅርታ አድርግልኝ?

ንግግሩን ልቅም አድርጋ አስታወሰችው፡፡

ሉቺያ በደንብ እየተከተለቻት ነው፡፡ ሲስተር ቴሬዛ ከራሷ ጋር እያወራች ነው፡፡ ነገር ግን ምን እንደምትል ማዳመጥ አልቻለችም፡፡

ሉቺያ መስቀሉን የምታገኝበትን መንገድ እያሰበች ነው፡፡

ሩቢዮ ቆም አለ፡፡ "እዛ አካባቢ ወታደሮች አሉ፡፡ ወደ ተራራው አናት ላይ እንውጣና እንደበቅ" አለ፡፡

ፈጠን ብለው ወደጋራው አናት ወጡ፡፡

"ትንሽ መንገድ ነው የሚቀረን" አለ ሩቢዩ አርዛኖ በእርግጠኛነት፡፡ "ከዛ በኋላ እናርፋለን"

ተራራው አናት ላይ እንደቀረቡ ቶማስ ሳንጃሮ በድንገት እጃቸውን ያዘው፡፡

"ቁሙ" አለ በሹክሹክታ፡፡

ሩቢዮ አዘቅዝቆ ሲመለከት ብዛት ያላቸው ወታደሮችን ተመለከተ፡፡

"ሩቢዮ በቁጣ ነደደ፡፡ "ሙሉ ጦር ነው፡፡ ምሽቱን እዚህ ማሳለፍ አለብን፡፡

"ነገ ሲሔዱ ይችላሉ፡፡ ያን ጊዜ መንገዳችንን እንቀጥላለን" አላቸው ለመነኰሳቱ፡፡ መሸበሩን እንዲያውቁበት አልፈለገም፡፡ "ምሽቱን እዚህ እናሳልፋለን ሲስተር፡፡ ድምፃችን መሰማት የለበትም፡፡ እዛ ታች ወታደሮች ስላሉ እንዲያገኙን ማድረግ የለብንም፡፡"

ሉቺያ እስካሁን ከሰማችው ጥሩ የተባለውን ነገር አዳመጠች፡፡ ድንቅ ነው ስትል አሰበች፡፡ ዛሬ ምሽት መስቀሉን ይገኘ እሰወራለሁ፡ ወታደሮቹ በመኖራቸው እኔን ፍለጋ አይወጡም፡፡

ለሲስተር ቴሬዛ ደግሞ ዜናው ሌላ መልእክት አዝሏል፡፡ ኮሎኔል አኮካ ይፈልገናል ሲሉ አዳምጠዋል፡፡ ኮለኔሉን ጠላት ሲሉት ሰምተዋል፡፡ ጠላት ግን እነሱ ናቸው፡፡

ሩቢዮ "ሲስተር በጣም ዝም ማለት አለብን" አላቸው"

ሁለቱ ሰዎች የመኝታ ክረጢቱን ሲስትሮቹ እንዲተኙበት አዘጋጁላቸው::

"አሁን ትንሽ ማሸለብ አለባችሁ" አሏቸው::

ሴቶቹ ያልለመድት ከረጢት ውስጥ ገብተው ተጋደሙ:: ምሽቱ ብሩህ ከመሆኑ በላይ ኮከቦቹ ጥርት ብለው ይታያሉ:: ሉቺያ ኮከቦቹን እየቆጠረች ትንሽ ነው የቀረኝ ስትል አሰበች::

ምን ያህል እንዳደከማት አልተሰማትም ነበር:: ወዲያው እንቅልፍ ወሰዳት::

ሲስተር ቴሬዛ አጠገቧ ተጋድመዋል:: ከራሳቸው ጋር እየታገሉ ነው:: ከሌሊቱ አስር ሰአት ላይ ሲስተር ቴሬዛ የያዙትን መስቀል ሉቺያ የተኛችበት ከረጢት ውስጥ ከተው ከጠባቂዎቻቸው ተሰውረው ቁልቁል ተንደረደሩ::

እታች ሲደርሱ አንድ ድምፅ "እዛ ያለው ማነው?" ሲል ተጣራ "ሲስተር ቴሬዛ"

የወታደር መለያ ያጠለቀ ወታደር ተጠጋቸው:: መሣሪያ ታጥቋል::

"ከየት ነው የመጡት እሮጊቷ እመቤት?" በማለት ጠየቃቸው::

"እግዚአብሔር ልኮኝ" አሉት አተኩረው እየተመለከቱት::

ጠባቂው እየተመለከታቸው "አሁን ነው ያደረገው?"

"አዎ:: ኮለኔል አኮካን እንዳገኘው ልኮኛል::"

ጠባቂው አንገቱን ነቀነቀ:: "አንቺ ኮለኔሉ የሚፈልጋት አይነት አለመሆንሽን ልትነግሪው ይገባል:: ከዚህ ሒጂ"

"አልገባህም:: እኔ ከሴቶቹ ገዳም የወጣው መነኩሴ ነኝ:: የጅሚሚሮ እስረኛ ነበርኩ:: የእሱ ሰዎች አግተውኝ ነበር"::

ጠባቂው በአግራሞት ተመለከታት::

"አንቺ ከገዳሙ ነው የመጣሽው?"

"አዎ"





"አቪላ ካለው ገዳም?"

"አዎ" አለች ትዕግስቷ ተሟጦ "ለጊዜው ኮለኔሉ እዚህ የለም ሲስተር::" ያልጠበቀችው ነገር ነበር::

"ግን የተወከለው ኮለኔል ኮስቴሎ አለ:: ወደ እሱ እወስድሻለሁ::"

"እሱ ሊረዳን ይችላል?"

"በደንብ ይረዳናል"

ጠባቂው እድሉን እያመሰገነ ወደ ኮሎኔል ኮስቴሎ ውሰዳት:: በደስታ ተቀበላት:: ወደ ጊዚያዊ ድንኳኑ አስገብቶ ጥያቄውን አጐረፈው:: ካርታ ዘርግቶ የነገረቻቸውን አቅጣጫ መመልከት ጀመሩ::

ኮሎኔሉ አምላክ የሰጠው እድል አድርጐ ቆጠረው:: ሲስተር እነዚህ ሰዎች የት እንዳሉ ያውቃሉ? ሲስተር ቴሬዛ "በትክክል እዛ አናት ላይ ከእናንተ ተደብቀው ተቀምጠዋል" አሉ::

# ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

አልጋዋ ላይ እርቃኗን ተጋድማለች ቤኒቶ ፓታስ ውስጥ ሲገባ እየተሰማት ነው፡፡ ስሜቷ ጣራ ነክቷል፡፡ ነገሩ ቢያስደስታትም፡፡ ፓታስን ገድየዋለሁ ስትል አሰበች፡፡ እሱ ሞቷል፡፡

ሉቺያ አይኗን ከፍታ ተቀምጣ ዙሪያዋን አማተረች፡፡ የሆነ ነገር ጐኗን ወጋት፡፡ እቃውን ስታወጣው መስቀሉን አገኘችው፡፡ ባለማመን ተመለከተችው፡፡ አምላክ ድንቅ ነገር እያደረገልኝ ነው ስትል አሰበች፡፡

መስቀሉ እሷ ጋር እንዴት እንደመጣ አታውቅም፡፡ ግድም አልነበራትም፡፡ በመጨረሻ በእጇ አስገብታዋለች፡፡ አሁን ማድረግ ያለባት መጥፋት ነው፡፡

ሲስተር ቴሬዛ የት እንደተኛች ፍለጋ ያዘች፡፡ የለችም ሉቺያ በጨለማው ውስጥ ዙሪያዋን አማተረች፡፡ ቶማስ አለ ሩቢዮ ግን አይታያትም፡፡ ግድ አልነበራትም፡፡ አሁን የማምለጫው ጊዜ ነው ስትል አሰበች፡፡

መንቀሳቀስ ስትጀምር የሚታያት ነገር አልነበረም፡፡

በድንገት ነገሩ ተበላሸ፡፡

ኮሎኔል ሩል ሶስቴሎ ትዕዛዝ እየሰጠ ነው፡፡ የኮሎኔል አኮካ ረዳት ሆኖ እንዲሰራ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕዛዝ ነው የተሾመው፡፡ ጂሚ ሚሮን እና መነኩሳቱን እንዲይዝ፡፡ እድል አንዷን መነኩሴ በሩ ድረስ አምጥቶለታል፡፡ ዝናውን ለምን ከኮሎኔል አኮካ ጋር ይ ካፈላል? ኮሎኔል አኮካ ገደል ይግባ ሲል ፉል ሶስቴሎ አሰበ፡፡ ይህ የእኔ ነው፡፡ ምናልባት አፖስ ሞንዶ ከአኮካ ይልቅ በእኔ መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል ሲል አሰበ፡፡

ኮሎኔል ሶስቴሎ ለሰዎቹ ግልፅ ትዕዛዝ እየሰጠ ነው፡፡ "ማንንም እስረኛ እንዳታደርጉ፡፡ ይህ ከአሸባሪዎች ጋር መደራደር ነው፡፡ ግደሏቸው፡፡"

"ኮሎኔል ከሚሮ ሰዎች ጋር መነኩሳቱ አሉ፡፡ እነሱን ምን ማድረግ . . ?" አለብን በማለት መቶ አለቃ ፓንቴ እያመነታ ጠየቀው፡፡

"አሸባሪዎቹ ከመነኩሳቱ ጀርባ እንዲሸሸጉ እንተዋቸው? አይደረግም፡፡ ምንም እድል የለንም"





ደርዘን የሚቆጠሩ ወታደሮቹን ለግዳጅ አሰማራቸው፡፡ ከፍ ባለ ደረጃ ታጥቀዋል፡፡ በጨለማው ተከልለው ወደ ተራራው ወጡ፡፡

አካባቢው ጋር ሲደርሱ ኮሎኔል ሶስቴል ለወጉ ያህል "ተከባችኋል መሣሪያችሁን ጣሉ" ባለበት ትንፋሽ "ተኩሱ" ሲል አዘዘ መሣሪያዎቹ ተንጣጡ"

ቶማስ እድል ሳያገኝ አንዷ ጥይት ባረቀችው፡፡ መሮት ከመድረሱ በፊት ህይወቱ አለፈች፡፡ ተኩሱ ሲከፈት ሩቢዩ አርዛኖ ራቅ ብሎ በመቆሙ ተርፏል፡ ፡ ጓደኛው ሲዘረጋ ተመልክቷል፡፡

ሉቺያ ከእሱ ሁለት እርምጃ ርቃ ፊቱ ቆማለች፡፡

"ሲስተር ቴሬዛ የት ናቸው?" በማለት ጠየቃት

"ሔዳለች"

"ዝቅ በይ" አላት ሩቢዮ

የሉቺያን እጅ ይዞ ከጠላት ወረዳ ራቀ፡፡ ጥይቱ በአናታቸው ላይ እያፏጨ ነው፡፡ ኩሒያና ሩቢዮ በዛፎቹ ተከልለው እየሮጡ ነው፡፡

"ያዥኝ" አላት ሉቺያን፡፡

የአጥቂዎቻቸው ድምፅ እየራቀ ሲመጣ ትንፋሽ ለመሰብሰብ ቆሙ፡፡ ሁለቱም በረጅሙ እየተነፈሱ ነው፡፡

"ለጊዜው ተሰውረናል" አላት ሩቢዮ፡፡ "ነገር ግን ጉዞአችንን መቀጠል አለብን፡፡

ሉቺያ በኃይል እየተነፈሰች ነው፡፡

"ማረፍ ከፈለግሽ?

"አልፈልግም" አለችው፡፡ ተዳክማለች፡፡ ግን ደግሞ መያዝ አትፈልግም፡፡ መስቀሉ እጇ ከገባ በኋላ መሆን የለበትም፡፡

"ደህና ነኝ" አለችው፡፡ "ከዚህ እንውጣ"፡፡

የኮሎኔል ኮስቴሎ ፊት ገርጥቷል፡፡ አንድ አሸባሪ ተገድሏል፡፡ ምን ያህሉ እንዳመለጡ የሚያውቀው አምላክ ብቻ ነው፡፡ የያዘው ጂሚ ሚሮን ሳይሆን

አንድ መነኩሴ ነው፡፡ ምን እንደተፈጠረ ለኮሎኔል አኮካ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከዚህ የበለጠ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡

ከአለን ተኮር የደረሳት ሁለተኛው የስልክ ጥሪ ለኤለን ስኮት ውርጅብኝ ነው የሆነባት፡፡

"የሆነ ጥሩ መረጃ አግኝቼልሻለሁ፡፡" አላት በእርጋታ፡፡

"የቆዩ ጋዜጦችን ሳገላብጥ ስለልጅቷ ጠቃሚ መረጃ ሳላገኝ አልቀረሁም፡፡

"እና?" የምታውቀው ነገር ሲመጣባት ተረበሸች፡፡

ተኮር ድምፁን የጨዋ ለማስመሰል እየሞከረ ነው፡፡ "ልጅቷ ወድቃ የተገኘችው በእናንተ ላይ የአውሮፕላን አደጋው በደረሰበት ተመሳሳይ ወቅት ነው፡፡"

ዝምታ፡፡

ቀጠለ "የባለቤትሽን ወንድም ሚስቱንና ልጁን ፓትርሺያን የገደለው አደጋ" ድርድር እያቀረበላት ነው፡፡ ተጨማሪ ማብራሪያ አላስፈለጋትም ጉዳዩን ደርሶበታል፡፡

"ልክ ነህ" አለችው ኤለን፡፡ "ያንን ልነግርህ ይገባ ነበር፡፡ ስትመለስ ሁሉንም ነገር አስረዳሀለው፡፡ ስለልጅቷ ያገኘኸው ተጨማሪ ነገር አለ?

"የለም ግን ከዚህ በኋላ ለብዙ ጊዜ መደበቅ አትችልም፡፡ አገሩ በጠቅላላ እየፈለጋት ነው፡፡

"እንዳገኘኸት በፍጥነት አሳውቀኝ፡፡

ስልኩ ተቋረጠ፡፡

አለን ተኮር በዝምታ ተቀምጧል፡፡ በጣም ረጋ ያለች ሴት ነች ሲል በአድናቆት አሰበ፡፡ ከእሷ ጋር በሽርክና መስራትን ስታስብ ምን ይሰማት ይሆን?

እሱን መላኬ ስህተት ነበር ስትል ኤለን ስኮት አሰበች፡፡ ላቆመው ይገባል፡፡ ስለልጅቷስ ምን ማድረግ አለባት? መነኩሴ ስላገኛት መወሰን አልችልም፡፡ አልችልም፡፡

ፀሐፊዋ በውስጥ ስልክ ደወለችላት፡፡





"የቦርድ ክፍል ውስጥ እየጠበቁሽ ነው ወይዘሮ ስኮት፡፡

"መጣሁ"

ሉቺያ እና ሩቢዮ አርዛኖ በጫካው እየተሹለከለኩ መንዛቸውን ቀጥለዋል፡፡

ሩቢዩ በመጨረሻ "እዚህ መቆም አለብን፡፡ አሁን አያገኙንም፡፡ በጫካው መሐል ገብተዋል፡፡

ሉቺያ መሬቱ ላይ ተጋድማ ትንፋሿን ለመሰብሰብ እየሞረች ነው፡፡ በሐሳቧ የቀደመውን ትዕይንት ማሰብ ይዛለች፡፡ ቆማስ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ተገድሏል፡፡ እነሱንም ሲገሏቸው መሞከራቸውን አስታወሰች፡፡ እስካሁን የኖረችው አጠገቧ ባለው ሰውዬ እርዳታ ነው፡፡

ሩቢዮ አካባቢውን ሲቃኝ ተመለከተችው፡፡

"ምሽቱን እዚሁ እናሳልፋለን ሲስተር"

"ጥሩ" መሔዱን ብትፈልግም ማረፍ እንዳለባት አልጠፋትም፡፡ ሩቢዩ ምግብ ፍለጋ ወደ ከተማ ሲወጣ እዛው እንደምትጠብቀው ጠየቃት?"

"አዎ እጠብቅሀለው" አለችው

አለምን በድጋሚ መቀላቀሏ ያስፈራት መሰለው፡፡

ሉቺያ አያየችው "እለምደዋለሁ" አለች፡፡

"ጠንካራ ነሽ ሲስተር" አላት ሩቢዩ በአድናቆት፡፡"ቶሎ እመለሳለሁ"፡፡

ከአጠገቧ ሲርቅ ተመለከተችው፡፡ ሁለት አማራጭ አላት፡፡

ወደ ከተማ ሔዳ የወርቅ መስቀሉን በመሸጥ ፓስፖርት አውጥታ ወደ ስዊዘርላንድ መንዝ ወይም ከወታደሮቹ እስኪሰወሩ ድረስ ከሰውየው ጋር መቆየት፡፡ አስተማማኙ ይኸኛው ነው ስትል ወሰነች፡፡

ሩቢዮ አርዛኖ ተመልሶ መጣ፡፡ በፈገግታ ቀረባት፡፡ የሚበላ ነገር በእጁ ይዟል፡፡

አጠገቧ ተቀመጠ፡፡ "ጥሩ እራት ነው፡፡ ልክ ከሰማይ እንደወረደ መና ይቆጠራል" አላት፡፡

ሉቺያ እያየችው "እርቦኛል እውነትም ከሰማይ የወረደ መና ነው" አለች::

በልተው ከጨረሱ በኋላ አንድ ዛፍ አጠገብ ተቀመጡ:: ሩቢዩ ያወራል ሉቺያ ታዳምጣለች:: ነገር ግን ከልቧ አልነበረችም::

"አስር አመት ገዳም ነበርኩ:: ነው ያለሽው ሲስተር?"

"ለምን?" ጠየቀኝ ስትል እያሰበች::

"አዎ"

አንገቱን ነቀነቀ:: "በአለም ላይ ምን እንደተፈጠረ አታወቂም ማለት ነው::"

"አዎ"

"ባለፉት አስር አመታት አለም በእጅጉ ተለውጣለች ሲስተር::"

"ነው እንዴ?"

"ፍራንኮ ሞቷል"

"አይደረግም!"

"አዎ ባለፈው አመት ነው የሞተው::"

እያለ የምታውቀውን ነገር ያስረዳት ጀመር:: ሁለት ሰዎች ጨረቃ ላይ አረፉ:: በአሜሪካና በፖርቹጋል አብዮት ተካሔደ::

ሲጋራ ሲለኩስ ማጨስ እንደምትፈልግ ነገረችው::

"ባጨስ ቅር ይልሀል?"

"መሞከር ትፈልጊያለሽ?

"ምን እንደሚመስል ለማወቅ ብቻ" አለች ሉቺያ በጥድፊያ::

አቀበላት:: አንድ ጊዜ በሀይል ማገችው:: እፎይታ ተሰማት ሩቢዩ በመገረም እያያት ነው::

አሁን ምን ምን እንደሚል አወኩት::

"ወደድሽው"





"በፍፁም" ካለች በኋላ በድጋሚ አንዴ ሳበችለት:: መጠንቀቅ አለባት:: እንዲጠረጥራት እድል መስጠት የለባትም:: ገዳሙ ውስጥ የቆየችው ለጥቂት ወር ነው:: ወደ አለም በድጋሚ መቀላቀል ሩቢዩ እንዳለው አስቸጋሪ ነው:: ስለሚጋንና ግራሺያ አሰበች:: ሲስተር ቴሬዛስ ምን ገጥሟት ይሆን? ወታደሮቹ ይዘዋት ይሆን?"

ሌሊቱ ረጅም በመሆኑ ለመተኛት ወሰነች::

ትንሽ መተኛት ያለብኝ ይመስለኛል::" አለችው

"አታስቢ:: እኔ እጠብቅሻለሁ ሲስተር::"

"አመሰግናለሁ" አለችው በፈገግታ:: በጥቂት ጊዜ ውስጥ እንቅልፍ ጣላት::"

ሩቢዩ አርዛኖ እየተመለከታት በሐሳብ ተዋጠ:: እንደዚች አይነት ሴት አይቼ አላውቅም:: እራሷን ለአምላኳ አሳልፋ የሰጠች ናት:: በተመሳሳይ አለማዊነት ይታይባታል:: ዛሬ ምሽት ደግሞ ከወንድ የበለጠ ጀግንነት አሳይታለች:: ድንቅ እና የተለየች ሴት ነሽ አላት በእንቅልፍ የወደቀችውን ሉቺያን እያያት:: ትንሿ የእየሱስ ሲስተር::

# ምዕራፍ ሀያ

ኮሎኔል ፉል ሶስቴሎ አስረኛ ሲጋራውን ለኮሰ። ከዚህ በላይ መቆየት አልችልም። መጥፎ ዜና እግር ያለው ይመስል ቶሎ ይደርሣል።

ራሱን ለማረጋጋት ከሞከረ በኋላ ስልኩን መደወል ጀመረ። መስመር ላይ ኮሎኔል ራሞን አኮካን እንዳገኘው ‹‹ትላንት ማታ የአሸባሪዎቹን ካምፕ ወረን ነበር። ጀሚ ሚሮ እዛ መኖሩ መረጃ ደርሶን ነበር። ማወቅ ያለብህ ስለመሰለኝ ነው የደወልኩት።››

አስፈሪ ዝምታ ሰፈነ።

‹‹ያዝከው?››

‹‹አልያዝኩትም››

‹‹እኔን ሳታማክር ነው ተልእኮውን የፈጸምከው?››

‹‹ጊዜ አልነበረኝም››

‹‹ግን ሚሮ እንዲያመልጥ ጊዜ ነበረው።›› ራሞን አኮካ በብስጭት ተውጧል። ‹‹ይህን መጥፎ ውሣኔ እንድትወስድ አይዞህ ያለህ ማን ነው?››

ኮሎኔል ሶስቴሎ በረጅሙ ተነፈሰ። ‹‹ከገዳሙ ካመለጡት መነኮሳት መካከል አንዷን ይዘናታል። ወደ ሚሮ እና ሰዎቹ የመራችን እሷ ናት። ከሰዎቹ አንዱን ገድለነዋል››

‹‹ሌሎቹ ግን አመልጠዋል?››

‹‹አዎ ኮለኔል››

‹‹መነኩሴዋ የት ነው ያለችው? ወይስ እሷንም ለቀሀታል? ድምፁ ተቆጥቷል።

‹‹አይደለም ኮሎኔል›› አለ ሶሽቴላ በችኮላ። ‹‹እዚህ ካምፕ ውስጥ ነው ያለችው። እየመረመርናት ነበር።››

‹‹ተው እኔ ራሴ እጠይቃታለሁ። በአንድ ሰዓት ውስጥ እደርሳለሁ። እኔ





እስክመጣ በደንብ ጠብቃት›› አለና መነጋገሪያውን ዘጋው።

ልክ ከአንድ ሰዓት በኋላ ኮሎኔል ራምን አኮካ ገምቹ ደረሰ። አብረውት የመጡ በደርዘን የሚቆጠሩ ረዳቶቹ ይታያሉ።

‹‹መነኩሴዋን ወደ እኔ አምጧት›› ሲል አኮካ አዘዘ። ሲስተር ቴሬዛ ኮለኔል አኮካ ወደሚጠብቃት ድንኳን ተይዛ መጣች። ስትመጣ ትህትና የተሞላ ፈገግታ ሰጣት።

‹‹ኮሎኔል አኮካ ነኝ››

በመጨረሻ ‹‹እንደምትመጣ አውቅ ነበር። አምላኬ ነግሮኛል›› በትህትና አንገቱን ነቀነቀ። ‹‹ነግሮሻል? ጥሩ። እባክሽ ተቀመጪ ሲስተር››

ሲስተር ቴሬዛ ለመቀመጥ አመነታች። ‹‹ልትረዳኝ ይገባል››

‹‹እርስ በርሣችን መረዳዳት አለብን›› በማለት ኮሎኔሉ ማረጋገጫ ሰጣት።

‹‹ስሺላ ካለው የሴቶች ገዳም ነው ያመለጡት ልክ ነኝ?››

‹‹አዎ። አስደንጋጭ ነበር። ሰዎቹ በጠቅላላ እግዚአብሔር የማይወደውን ነገር ነው ያደረጉት። እና ...››

‹‹የማይረባ ነገር እንድታመልጡ ያደረግናችሁ እኛ ነን። ‹‹እዚህ እንዴት መጡ ሲስተር?››

‹‹አምላክ አመጣኝ። ሊፈትነኝ ፈልጎ ነው ከዚህ በፊት ...››

ኮሎኔል አኮካ በትእግስት ተሞልቶ ‹‹ከእግዚአብሔር በተጨማሪ እዚህ የመጣዎት ሌላ ሰው አለ ሲስተር?››

‹‹አዎ›› አፈኑኝ። ከእነሱ አመለጥኩ››

‹‹ለኮሎኔል ሶስቴሎ ሰዎቹ ያሉበትን ቦታ ነግረውት ነበር?››

‹‹አዎ። ሰይጣኖች ናቸው። ከዚህ ነገር ጀርባ ያለው ራውል ነው። ገባህ። ደብዳቤ ልኮልኛል እና ...››

‹‹ሲስተር እኛ በተለየ ሁኔታ የምንፈልገው ጀሚ ሚሮን ነው። እሱን አይተውታል?›› ተረበሸች። ‹‹አዎ። እሱ ...››

ኮሎኔሉ ወደፊት ተጠጋ። «እጅግ በጣም ጥሩ። አሁን የት እንደሚገኘው ይነግሩኛል።»

«እሱና ጓደኞቹ ወደ ኢዝ እየተጓዙ ነው።»

ግራ ተጋባ። «ወደ ኢዝ? ወደ ፈረንሣይ?»

ድምጿ በቁጣ የተሞላ ነው። «አዎ። ሞኒካ ራውልን ከድታዋለች። እና ሰዎቹን እኔን እንዲያግቱኝ ላካቸው። ለልጁ ሲል ነው...»

ትእግሥቱን ለመቆጣጠር እየሞከረ ነው። «ሚሮ እና ጓደኞቹ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ነው የተጓዙት። ኢዝ ደግሞ በምስራቅ በኩል ነው።»

«ወደራውል እንዲወስዱኝ ልትፈቅድላቸው አይገባም። እሱን በድጋሚ ማየት አልፈልግም። ገባህ አይደል። ላየው አልችልም።»

ኮሎኔል አኮካ በቁጣ «ራውል ስለምትይው ሰው አያገባምኝም። ማወቅ የምፈልገው ጀሚ የት እንዳለ ነው?»

«ነገርኩህ። ኢዝ ላይ እኔን እየጠበቀኝ ነው። እሱ የሚፈልገው ...»

«እየዋሸሽ ነው። ሚሮን ለመደበቅ እየሞከርሽ ነው። ልጉዳሽ አልፈልግም። በድጋሚ አንድ ጊዜ እጠይቅሻለሁ። ጀሚ ሚሮ የት ነው ያለው?»

ሲስተር ቴሬዛ ረዳት አልባ ሆና ተመለከተችው። «አላውቅም» በማለት አንሾካሾከች። ዙሪያዋን በፍርሀት እያቃኘች «አላውቅም» አለች።

«ቅድም ኢዝ ነው ብለሽኝ ነበር።» ድምፁ ያስፈራል።

«አዎ። አምላክ ነግሮኛል»

ኮሎኔል አኮካ በቂ ነው ሲል አሰበ። ሴትየዋ የተዋጣላት ተዋናይ ወይም እብድ ነች። በሁለቱም መንገድ ነገሯን ሁሉ ከአምላክ ጋር አያያዘችው።

ረዳቱ ወደሆነው ፓትሪክ አሪታ በመዞር «የሲስተሯ አስተሳሰብ መታደስ አለበት። ወደዋናው ድንኳን ውሰዳት። ምናልባት አንተ እና ሰዎችህ ጀሚ ሚሮ የት እንዳለ እንድታስታውስ ትረዷት ይሆናል።»

«አዎ ኮሎኔል።»





ፓትሪክ አሪታ እና ረዳቶቹ በገዳሙ ጥቃት ላይ ተሳትፈዋል። በአራቱ መነኮሳት ማምለጥ እነሱም ተጠያቂ ናቸው። ደህና ነገሩን አሁን እናስተካክለዋለን በማለት አሰበ።

አሪታ ወደ ሲስተር ቴሬዛ ዞረ። «ከእኔ ጋር ይምጡ ሲስተር»

«እሺ» እግዚአብሔር ይመስገን በማለት አሰበች። «አሁን ቦታውን ለቀን እንሄዳለን? ወደ ኢዝ እንዲወስዱኝ አትፈቅድላቸውም?»

«አልፈቅድላቸውም» በማለት አሪታ አረጋገጠላቸው። «ወደ ኢዝ አይሄዱም። »

ኮሎኔሉ ልክ ነበር ሲል አሰበ። እየተጫወተችብን ነው። ደህና እኛ ደግሞ አዲስ ጨዋታ እናሳያታለን። ዝም ብላ ትጋደማለች ወይስ ትጮኸለች?

«ዋናው ድንኳን በር ላይ ሲደርሱ አሪታ «ሲስተር አንድ የመጨረሻ እድል እንሰጥዎታለን። ጀሚ ሚሮ የት ነው ያለው?»

ቅድም ጠይቀውኝ አልነበረም እንዴ? ወይስ ሌላ ሰው ነው?

«ወደ ራውል ሊወስደኝ አግኝቶኝ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ሞኒካ ስለከዳቸው እና ...»

«በቃ። የምትፈልጊው ይሄ ከሆነ» አለ አሪታ «አእምሮሽን እናድስልሻለን»

«አዎ» እባክህ ሁሉም ነገር ግራ የሚያጋባ ነው።»

ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ የአኮካ ሰዎች ወደ ድንኳኑ ገቡ። የሶስቱም ወታደሮች ከነመለዮ ልብሳቸው ተቀላቀሏቸው።

ሲስተር ቴሬዛ አየቻቸው። ፈዝዛ ተመለከተቻቸው። «እነዚህ ሰዎች ናቸው ወደ ገዳሙ የሚወስዱኝ?»

«ከዛ የተሻለ ነገር ሊያደርጉ ነው» አላት ፓትሪኮ አሪታ «ወደ ገነት ሊወስዱሽ ነው ሲስተር»

ሰዎቹ ተጠግተው ከበቧቸው።

«ያደረጉት ቀሚስ በጣም የሚያምር ነው» አለ አንዱ ወታደር በትክክል መነኩሴ ነሽ የእኔ ውድ? በማለት የሚጠራት። ይህ ሰው ራውል ነው እንዴ?

እየሀ ከወታደሮቹ ለማምለጥ ስንል ልብሳችንን ቀይረን ነበር። ግን እነዚህ ደግሞ ወታደሮች ናቸው። ግራ የሚያጋባ ነገር።

አንዱ ወታደር ቴሬዛን መሬት ላይ ጣላት። ‹‹ቆንጆ አይደለሽም ግን ከልብሱ ስር ምን እንዳለ አብረን እንይ››

‹‹ምን እያደረክ ነው?››

ቀሚሷን ተረተረው። ሌላው ደግሞ ከላይ የለበሰችውን ልብስ አወለቀባት።

‹‹ለአሮጊት መጥፎ የሚባል ገላ አይደለም?››

ቴሬዛ ጮኸች።

የከበቧትን ሰዎች እያየች። እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል። ጫፌን እንዲነኩኝ አይፈቅድላቸውም። የአምላክን ንፅህና የተላበስኩ ነኝ።

አንዱ ወታደር ቀበቶውን ፈታ። ጠንካራ እጅ ጭኗን ሲፈለቅቅ ታወቃት፡ ፡ ውስጧ ሲገባ ጮኸች።

‹‹አሁን አምላኬ ቅጣቸው››

መብረቅ ይወርዳል በማለት ጠበቀች። ምንም አልተፈጠረም።

ሌላው ወታደር እላይዋ ላይ ተከመረባት። ቴሬዛ አሁንም የአምላክን በትር እየጠበቀች ነው። አሁን ህመሙ ትቷታል።

መቶ አለቃ አሪታ ቆሞ እያየ ነው። ሰዎቹ አምሮታቸውን ከተወጡ በኋላ ‹‹ይበቃሻል ሲስተር? ጄሚ ሚሮ የት እንዳለ ከነገርሽን ነገሩ ይቆማል።››

ሲስተር ቴሬዛ አልሰማቻቸውም። አምላክ ይቀጣቸዋል ብላ ተስፋ አድርጋለች።

በሚገርም ሁኔታ አምላክ መልስ አልሰጣትም። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም። አሁን ገባት። ስድስተኛው ሰው እየተገናኛት ነው። ጥምቀቱ ተገለፀላት።

እግዚአብሔር ስለሌለ ነው የማይሰማት። ቢኖር ኖሮ ያድነኝ ነበር ስትል አሰበች። ጊዜዋን በከንቱ ያሳለፈች ያህል ተሰማት።





አይኗን በትክክል ገልጣ ዙሪያዋን በሚገባ መመልከት ቻለች። ሌሎች በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች ሊደፍሯት ተራቸውን እየጠበቁ ነው። መቶ አለቃ አሁንም ጥግ ይዞ ትእይንቱን እየተመለከተ ነው።

አንዱ ሲጨርስ አንዱ ይተካል። ሁሉም ከነሙሉ ትጥቃቸው ነው የሚደፍሩባት።

አምላክ ሳይሆን ሰይጣን ነው ያለው። እነዚህ ደግሞ የእሱ ረዳቶች ናቸው፡ ፡ በማለት ሲስተር ቴሬዛ አሰበች። እናም ሁሉም መሞት አለባቸው። ሁሉም።

አንዱ ወታደር እቃውን አንጠልጥሎ ውስጧ ሲገባ እሷም ሽጉጡን ከመታጠቂያው ላይ በፍጥነት በማውጣት ማንም ሳያስተውል ወደ አሪታ አነጣጥራ ተኮሰችበት። ጥይቷ ጉሮሮውን በጠሰችው።

እላይዋ ላይ በተጋደመው ወታደር ተከልላ አራቱን አጋደመቻቸው። እነሱም ወደ እሷ መተኮስ ጀመሩ። ቢያስቸግራቸውም መጨረሻ ላይ እሷን እና እላይዋ ላይ የተጋደመውን ወታደር እኩል ጨረሷቸው።

ወደኋላ አልተመለሰም፡፡ ለራሱ እና ለቤተሰቦቹ ሲል ከልቡ ተዋጋ፡፡ ጆሚ ባንኮችን ፋብሪካዎችን በጥንቃቄ እያቀደ አጋያቸው፡፡ ሰዎቹ ከተያዙበት በማንኛውም መንገድ ያስለቅቃቸዋል፡፡

የስፔን መንግሥት የደህንነት ቢሮ ባስክን እንዲያጠቃ መታዘዙን ሲሰማ ፈገግ ብሎ «ጥሩ፡፡ ዋጋቸውን ያገኛሉ›› አላት፡፡ በፅናት ማንነቱን ማሳየት ችሏል፡፡ ለሚያምንበት ነገር ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሏል፡፡

አሁን አንድ የእሱ ሰው በነፃነት ማውራቱን ተከትሎ እነዚህ መነኩሴዎች ከእነሱ ጋር ተጣብቀዋል፡፡

ቤተክርስቲያን ከእኛ ጐን ትቆማለች ማለት ምፀት ነው፡፡ አሁን ዘግይቷል፡፡ ሌላ ነገር በማዘጋጀት እናቴን አባቴንና እህቶቼን ከመለሱልኝ እንስማማለን ሲል በምሬት አሰበ፡፡

ሌሊቱን በጫካ እየተጓዙ ነው፡፡ ጆሚ እና ሚጋን በዘግታ ከፌላክስ ጋር ስለአለፈው ጀብዱአቸው ማውጋት ያዙ፡፡ ጆሚ ሚሮን የመሰለ ሰው አታውቅም፡፡ ፍፁም በሆነ ሁኔታ በራሱ ይተማመናል፡፡

ሜንዶቪያ ሊያደርሰኝ የሚችል ሰው ቢኖር ይህ ሰው ብቻ ነው ስትል ሜጋን አሰበች፡፡

ጆሚ ለሲስተሯ ለማዘን ትንሽ ጊዜ ወሰደበት፡፡ በዚህም ላይ ላሳየችው ፅናት ምንም አላላትም፡፡ የእሱ ሰዎች እንዴት እየሆኑ እንደሆነ አሰበ፡፡

እሱ ለመፅናኛ አምፓሮ ጂሮን አላቸው፡፡ ሌሊት ላይ ትልቅ ምቾት ትሰጠዋለች፡፡

እሷ ከእኔ በላይ ለአላማዋ ሟች ነች ሲል ጆሚ አሰበ፡፡ ከእሱ የበለጠ መንግሥትን የምትጠላበት ምክንያት አላት፡፡ የአምፓሮ ጠቅላላ ቤተሰብ በብሔርተኞቹ ተጠራርገው አልቀዋል፡፡ ነፃና በጥልቅ ስሜት የተሞላች ናት፡፡

ንጋት ላይ ሳልማንካ አጠገብ የሚገኘው የሪዬ ቶርሜስ ባንክ ደረሱ፡፡ «ከመላው ስፔን የሚገኙ ተማሪዎች እዚህ ይመጣሉ›› በማለት ፊሊክስ ለሜጋን አብራራላት፡፡ «በስፔን ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ተመራጩ እዚህ ያለው ነው፡፡

ጆሚ እየሰማው አይደለም፡፡ የእሱ ትኩረት በሚቀጥለው እንቅስቃሴው ላይ ነው፡፡ አዳኝ ብሆን ወጥመዴን የት ነው የምዘረጋው?





ወደ ፌሊክስ ዞረ፡፡ «ሳል ማንካን መዝለል አለብን፡፡ ከከተማው ውጭ የሚገኝ ቦታ ላይ እንቆማለን፡፡›› ቦታው ፓራዶር ትባላለች፡፡ የቱሪስት መናኸሪያ ከተማ ነች፡፡ የድንጋዩ መንገድ በደንብ በታጠቁ ወታደሮች ይጠበቃል፡፡

በቡድን የመጡ ሰዎች ወደበሩ ሲጠጉ ጆሚ ለሁለት ሴቶች «እዚህ ጠብቁኝ›› አላቸው፡፡

ፌሊክስ ካርፒዮን ሲጠቅሰው ሁለቱ ሰዎች በፍጥነት ተሰወሩ፡፡

«የት ነው የሚሄዱት?›› ስትል ሜጋን ጠየቀች፡፡

አምፓሮ ጂሮን በግድየለሽነት ተመለከተቻት፡፡ «ምን አልባት የአንቺን አምላክ ፍለጋ ይሆናል››

«እንደሚያገኙት ተስፋ አደርጋለሁ›› አለች ሜጋን በእርግጠኛነት ከአስር ደቂቃ በኋላ ወንዶቹ ተመለሱ፡፡

«ሁሉም ነፃ ነው›› አላት ጆሚ ለአምፓሮ፡፡ «አንቺ እና ሲስተር አንድ ላይ ትተኛላችሁ፡፡ ፌሊክስ ከእኔ ጋር ይቆያል›› እያለ ቁልፍ አቀበላት፡፡

አምፓሮ በቅሬታ «ከአንተ ጋር መሆን ነው የምፈልገው ጆሚ በትዕዛዝ ተናግሬያለሁ፡፡ በደንብ ጠብቂያት››

አምፓሮ ወደ ሜጋን ዞረች «ነይ ወደ እኔ ሲስተር››

ሜጋን አምፓሮን ተከትላ ወደ ፎቁ ወጣች፡፡

ክፍሏ ጠባብ ብትሆንም ለሁለቱ ሴቶች በቂ ናት፡፡

ሜጋን ክፍሉን እየቃኘች «ቆንጆ ነው›› አለች፡፡

አምፓሮ ተበሳጭታለች፡፡ ሜጋንን መስናክል አድርጋ ቆጥራታለች፡፡ «አንቺ ማነሽ እና ነው ቅሬታ የምታቀርቢው?››

«ሥራ ነው›› ስትል ሜጋን ቀጠለች፡፡

አምፓሮ ካየቻት በኋላ ሳቀች፡፡ ከገዳሙ ክፍል ጋር ሲነፃፀር በእውነትም ስፊ ነው፡፡

አምፓሮ ልብሷን ማውለቅ ጀመረች፡፡

# ምዕራፍ ሀያ ሁለት

በምስራቅ በኩል ብዙ ማይል ርቆ ሉቺያ ጫካ ውስጥ ተጋድማለች።

ሩቢዮ አርዛኖ ቁጭ ብሎ ይመለከታታል። ልቀስቅሳት እያለ እያንገራገረ ነው። እንደ መልአክ ተኝታለች ሲል አሰበ።

ሊነጋ በመሆኑ መንቀሣቀስ አለባቸው።

ሩቢዮ በዝግታ ተጠግቷት በቀስታ ‹‹ሲስተር ሉቺያ ...››

ሉቺያ አይኗን ገለጠች።

‹‹አሁን መሄድ አለብን››

ካዛጋች በኋላ በእርጋታ ተነሣች። ‹‹የለበሰችው ልብስ ጡቷን በግልጽ የሚያሳይ ነው። ሩቢዮ ሳይወድ በግድ ተመለከተው።

ቃሌን ማክበር አለብኝ። እሷ የእግዚአብሔር ሙሽራ ናት።››

‹‹ሲስተር››

‹‹አቤት?››

‹‹ውለታ እንድትውይልኝ ብጠይቅሽስ›› አለ እያንገራገረ።

‹‹እሺ?››

‹‹ከፀለይኩ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል። ነገር ግን ካቶሊክ ነኝ። ብትውይልኝ ቅር ይልሻል?››

ሉቺያ የምትጠብቀው ይህንኑ ነበር።

ከፀለይኩ ምን ያህል ጊዜ ሆኖኛል? በማለት ተገረመች። በገዳሙ ያደረገችው አይቆጠርም። ሌሎች ሲፀልዩ እሷ እንዴት እንደምታመልጥ ታስብ ነበር።

‹‹አልችልም››

‹‹ሁለታችንንም እፎይታና ደህንነት ይሰጠናል››





‹‹ማንኛውንም አይነት ፀሎት ማድረግ እንደማትችል እንዴት ትንገረው?›› እኑ ... እሺ። የምታስታውሰው አንድ ፀሎት አለ። ልጅ ሳለች አባቷ አጠገቧ ሆና የምትፀልየው ‹‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝ የለም...››

ሐሣቧ ወደኋላ ወሰዳት።

‹‹እሷ እና አባቷ አለምን በቁጥጥራቸው ስር አድርገው ነበር። በእሷም ይኮራ ነበር።

‹‹የተወለድሽው በእድለኛ ኮከብ ስር ነው "ፋሺያ መላእክ" ሉቺያ እድለኛ መሆኗ ይታወቃት ነበር። ቆንጆ መሆኗን ዘወትር ይነግራታል። ማንም ምንም ነገር ጉድቷት አያውቅም። የአንጄሎ ካፒማይን ቆንጆ ልጅ አይደለች?

ሰይጣኖቹ የአባቴ እና ወንድሞቼ ጠላቶች ናቸው ስትል አሰበች። ዋጋቸውን ሰጥታቸዋለች።

ገዳም እያለች ስለአምላኳ አስባ አታውቅም። እዚህ ግን ከተራ ገበሬ ጋር ሆና እየፀለየች ነው።

‹‹ልትፀልይልኝ ትችያለሽ?››

ሉቺያ ቀጠለች። ‹‹በትክክል በህይወቴ ዘመን ሁሉ መልካም ነገር ይከተለኛል። ለዘለአለሙ በእግዚአብሔር ቤት እኖራለሁ››

ሩቢዮ እያያት ወደእሷ ተንቀሣቀሰ።

‹‹አመሰግናለሁ ሲስተር››

ሉቺያ በአንገቷ መልስ ሰጠችው። ምንድን ነው የሆንኩት? ስትል ራሷን ጠየቀችው።

‹‹ተዘጋጅተሻል ሲስተር?››

ሩቢ አርዛኖን እያየች ‹‹አዎ ተዘጋጅቻለሁ›› አለችው።

ከአምስት ደቂቃ በኋላ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ድንገተኛ ዝናብ ሲይዛቸው ቁጥቋጦ ስር ተጠለሉ። ዝናቡ ሲጨምር ድምፁ አስፈሪ ሆነ።

# ምዕራፍ ሀያ ሦስት

ሳልማንካ በሚገኘው የፖሊስ ጣቢያ መቶ አለቃ ፍሎረን ሳንቲያጐ የስልኩን መነጋገሪያ ሲያስቀምጥ እጁ እየተንቀጠቀጠ ነበር።

‹‹ጀሚ ሚሮና ሦስቱ ጓደኞቹ እኔ ጋር ነው ያሉት። እነሱን መያዝ የሚያስገኘው ክብር ምን ያህል ነው?

መንግሥት ጀሚ ሚሮን ለያዘ ከፍተኛ ገንዘብ በውለታ ለመክፈል ደንግጓል። ገንዘቡ ህይወቱን በጠቅላላ ይለወጥለታል። ለአጐቱም ጥቂት ገንዘብ ይሰጠዋል። 20 በመቶውን እሰጠዋለሁ ሲል ሳንቲያጐ አሰበ።

የጀሚ ሚሮን ዝና በሚገባ ያውቀዋል። እሱን ለመያዝ በማለት ህይወቱን አደጋ ላይ መጣል አይፈልግም። የገንዘብ ስጦታውን እኔ እወስዳለሁ። አደጋውን ሌሎቹ ይጋፈጡት።

ወንበሩ ላይ ተቀምጦ የተሻለ የሚለውን ዘዴ እያውጠነጠነ ነው። ኮሎኔል አኮካ ትዝ አለው። በኮሎኔሉና በህግ መካከል ከፍተኛ የበቀል ስሜት እንዳለ ሁሉም ያውቀዋል። ከዚህ ጐን ለጐን ኮሎኔሉ የደህንነቱን ቢሮ የማዘዝ ሙሉ ስልጣን አለው። መንገዱ ይህ ብቻ ነው።

ስልኩን አንስቶ ከኮሎኔሉ ጋር ተነጋገረ።

‹‹ሳልማንካ ከሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ መቶ አለቃ ፍሎሪና ሳንቲያጐ ነኝ። ጀሚ ሚሮ ያለበትን ቦታ ደርሼበታለሁ››

ኮሎኔል አኮካ ድምፁን ለመቆጣጠር ሞከረ። ‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹አዎ ኮሎኔል። ሁለት ክፍል ይዘው ነው ያረፉት።››

ኮሎኔል አኮካ ‹‹በጥንቃቄ አዳምጠኝ መቶ አለቃ። ወደቦታው በፍጥነት ሔደህ አካባቢውን በጥንቃቄ ተከታተል። ማናቸውም እንዳይወጡ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ካለህበት ቦታ እደርሣለሁ። ወደ ውስጥ እንዳትገባ። ከአይን እንዳትርቅ። ግልጽ ነው?››

‹‹አዎ አለቃዬ። አሁኑኑ እሄዳለሁ።›› እያመነታ ‹‹ኮሎኔል ስለሽልማት ገንዘቡ ...››

‹‹ሚሮን እንደያዝነው ገንዘቡ ይሰጥሀል››





‹‹አመሰግናለሁ ኮሎኔል። እኔ በጣም...››

‹‹ሂድ››

‹‹እሺ አለቃዬ››

ፍሎሪና ሳንቲያጐ መነጋገሪያውን አስቀመጠ። ለውሽማው ወሬውን ሊነግራት ፈለገ። ቀስ ብሎ ያስደንቃታል። አሁን የሚሰራው ሥራ አለ።

ጥበቃውን ለሌላ ፖሊስ ሰጥቶ ወጣ። ከጥቂት ሰዓት በኋላ እመለሳለሁ አለው። ስመለስ ሐብታም ሆኜ ነው ሲል አሰበ። የሚገዛውን ነገር እያለመ ነው።

ኮሎኔል አኮኮ የስልኩን መነጋገሪያ ካስቀመጠ በኋላ ማሰብ ያዘ። አሁን መሳሳት የለበትም። የመጨረሻ እርምጃው መሆን አለበት። ልክ እንደቼዝ ጨዋታ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

አኮካ ለረዳቶቹ ደወለ።

‹‹አቤት ኮሎኔል››

‹‹ምርጥ የሆኑ ሁለት ደርዘን ሰዎችህን አዘጋጅ። በደንብ መታጠቃቸውን አረጋግጥ። ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ወደሳልግንካ እንንቀሣቀሣለን።››

‹‹እሺ ጌታዬ››

አሁን ሜሮ ማምለጫ የለውም። ኮሎኔሉ ወረራውን በአእምሮው ስሎታል፡ አካባቢው በፍጥነትና በፀጥታ ይወረራል። ጥቃት ከማድረሱ በፊት ይያዛል። በተኙበት እንጨርሳቸዋለን።

ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ጉዞአቸውን ጀመሩ።

መቶ አለቃ ሳንቲያጐ ጊዜ ሳያጠፋ ቦታው ደረሰ። አሸባሪዎቹን የመያዝ ምንም ፍላጐት የለውም። የአኮካን ትእዛዝ ተከትሎ ጨለማ ውስጥ ተደብቆ ሁሉንም ነገር እየተከታተለ ነው። የሚያስበው በሽልማት የሚያገኘውን ገንዘብ ብቻ ነው። ሁሉም ከሰአታት በኋላ እንደሚገደሉ እርግጠኛ ሆኗል።

ወታደሮቹን የያዘው መኪና በዝግታ ወደከተማው ገባ። ኮሎኔል አኮካ መብራቱን አብርቶ ካርታውን መመልከት ያዘ። ‹‹እዚህ ጋ አቁም። የቀረውን መንገድ በእግራችን እንጓዛለን። ድምፅ እንዳታሰሙ።››

ፍሎሪና ሳንቲያጎ አጠገቡ መድረሳቸውን አላወቀም። «ማነው?» ሲዞር ከኮሎኔል አኮ ጋር ፊት ለፊት ተገጣጠመ። አምላኬ ያስፈራል ሲል አሰበ።

«መቶ አለቃ ሳንቲያጎ ነኝ ጌታዬ»

«ከክፍሉ የወጣ ሰው አለ?»

«የለም ጌታዬ። ሁሉም ውስጥ ናቸው። ምናልባት ተኝተው ይሆናል፡ ኮሎኔሉ ወደ ረዳቶቹ ዞረ። «ግማሾቹ ሆቴሉን እንዲከቡ እፈልጋለሁ። ለማምለጥ ከሞከሩ ግደሏቸው። የቀራችሁት ከእኔ ጋር ትመጣላችሁ። ወንበዴዎቹ ላይኛው ፎቅ ሁለት ክፍል ውስጥ ነው ያሉት።»

ሳንቲያጎ ኮሎኔሉና ረዳቶቹ ወደ ውስጥ በዝግታ ሲገቡ ተመለከታቸው። በተኩስ ልውውጡ አኮካ እንዳይገደልበት ሰጋ።

ፎቁ ላይ ሲደርሱ ኮሎኔሉ «እድል እንዳትሰጧቸው ተኩሱባቸው አላቸው።

ረዳቱ «ኮሎኔል ከአንተ ፊት እንዲሆን ትፈልጋለህ ሲል» ጠየቀው።

«አይሆንም» አለው ጂሚ ሜሮን መግደል የሚሰጠውን ደስታ እያሰበ።

ወደበሩ በዝግታ ተጠጉ። ሁሉም አድፍጠዋል።

«አሁን» ሲል ኮሎኔሉ ጮኸ።

በዛው ቅጽበት በሩን በርግደው ወደ ውስጥ ገቡ።

ክፍሉ ባዶ ነበር።

«ሔሎ» ሲል ተጣራ። ምንም ምላሽ የለም። ተደብቀዋል ማለት ነው ሲል ገመተ።

አንዱ ወታደር ከመቀመጫው ኋላ ያለውን ነገር ተመለከተ።

«ኮሎኔል ...»

አኮካ ፊቱን አዙሮ ነገሩን ተመለከተ።

ግዙፉ የማናጀሩ አካል ታስሮ ወለሉ ላይ ተዘርግቷል።

እባካችሁ አትረብሹን የሚል ቃል ተፅፎበታል።





# ምዕራፍ ሀያ አራት

ሩቢዮ አርዛና ሉቺያ በፍጥነት ውሃው ውስጥ ስትሰምጥ በድንጋጤ እየተመለከታት ነው። በቅጽበት እየሮጠ ወደ ወንዙ ገሰገሰ። የሉቺያን አካል እንደምንም ታግሎ ከውሃው ውስጥ አወጣው።

ካወጣት በኋላ ሣሩ ላይ ዘረራት። ሉቺያ ራሷን ስታለች። መተንፈስም አቁማለች። ሩቢዮ በጀርባዋ ካስተኛት በኋላ አየር እንድታገኝ መታገል ጀመረ። ጥረቱ ተሳክቶ ሆዷ የገባው ውኃ ሲወጣ በጣም አሳለች። ሩቢዮ የምስጋና ፀሎት አደረሰ።

እተነፋፈሷ እስኪስተካከል ድረስ ጠበቃት። የገረጣው ፊቷ መለስ አለ። ገላዋን በቅጠል ሊያደርቅላት ሞከረ። እራሱ እየተንቀጠቀጠ ነው። ብርዱ ውስጡ ዘልቋል። ሲስተር ሉቺያ የምትሞት መስሎት ነበር። ሲያስበው ዘገነነው። ገላዋን በዝግታ አደረቀላት። የማይሆን ሐሣብ አእምሮውን ሞላው።

የሚያስደንቅ ገላ አላት። ይቅር በለኝ አምላኬ። እሷ የአንተ ነች። ይህን መጥፎ ሐሣብ ከእኔ አርቀው።

ሉቺያ ቀስ በቀስ ነቃች። በምላሱ አካሏን እያሞቀው ነበር፡ አዎ ስትል አሰበች። ስሜቱ አስደስቷታል። አዎ አታቁም ካሮ አለች ለራሷ። አይኗን ከመክፈቷ በፊት በደስታ ተሞልታ ነበር።

ሉቺያ ወደወንዙ ስትወድቅ የመጣላት የመጨረሻ ሐሣብ ሞት ብቻ ነበር። ነገሩ ግን በህይወት አለች። ከሞት ያዳናትን ሰው እየተመለከተችው ነው። ሉቺያ በድንገት ወደታች ጐትታ ሳበችው። ፊቱ ላይ መገረም ይነበብበት ነበር። ደንግጧል።

«ሲስተር» ሲል ተቃወማት። «ይህንን ማድረግ ...»

«ዝም በል»

ከንፈሯ ከንፈሩን ፍለጋ ተጓዘ። ለሩቢዮ ከብዙ ነገር በላይ ነበር።

«ፍጠን» አለች ሉቺያ እየተጣደፈች።

ለሥራው ዋጋው ሊከፈለው ይገባል ስትል አሰበች። የማደርገውም ይህንኑ ነው።

# ምዕራፍ ሀያ ስምንት

ሪካርዶ ሜላዶ ዋሻው በር ላይ ሲደርስ ቀበሮው ወደ መግቢያው እየተጣጋ ነበር። በህይወቱ አድርጎት የማያውቀውን ነገር በፍጥነት አደረገ። ወደ ዋሻው በር ተንደርድሮ መግቢያውን ዘጋው።

"ሲስተር!"

በጨለማው ጭላንጭል ቀበሮው ወደ ግራሼላ እያቀና ነበር። ሽጉጡን አውጥቶ ተኮሰ በት። ቀበሮው ህመሙ ሲፀናበት ወደ ሪካርዶ ዞሮ ተከመረበት። ቀበሮው ቢቆስልም ጥንካሬው አስገራሚ ነበር። ሪካርዶ ራሱን ነፃ ሊያወጣ ቢሞክርም አልቻለም።

ራሱን ለመሳት መቃረቡን ተገነዘበ። ግራሼላ ወደ እሱ ስትመጣ በጭላንጭል እና በግማሽ ነፍስ ተመለከታት። በጩኸት "ከዚህ ውጪ" አላት።

የግራሼላ እጅ ከጭንቅላቱ በላይ ሲነሣ ተመለከተ። ትልቅ ድንጋይ ይዛለች። ልትገለኝ ነው ሲል አሰበ።

ድንጋዩ እሱን አልፎ የቀበሮውን ጭንቅላት አፈረሰው። ሪካርዶ እንደምንም ተነስቶ ተቀመጠ። ትንፋሹን ለመሰብሰብ እየሞከረ ነው። ግራሼላ አጠገቡ ተንበርክካለች።

"ደህና ነህ" በማለት መጨነቋ እየታወቀባት ጠየቀችው አንገቱን ነቀነቀ። ድምፅ ሲሰማ እንደምንም ተነስቶ ቆመ። አጠገባቸው ደርሶ የተመለሰው ሞት ሁለቱንም አስደንግጧቸዋል።

"ከዚህ አካባቢ እንጥፋ። ተመልሰው ሊፈልጉን ይመጡ ይሆናል" ግራሼላ የተደቀነባቸው አደጋ ገባት።

አንድ ሰአት ያህል ከተጓዙ በኋላ ትንሽ ወራጅ ውሃ አጠገብ ደረሱ። ሪካርዶ" እዚህ እንቁም" አላት።

ቁስሉን ያለምንም የህክምና መሣሪያ ጠራረጉት። ቀዝቃዛው ውሃ እፎይታ ሰጠው። የእጁ ቁስል እጁን ለማንቀሳቀስ አስቸገረው። እስኪገርመው ድረስ ግራሼላ "እኔ ልጥረግልህ" አለችው።





ትህትናዋ አስገርሞታል። ግራሼላ ድንጋጤው ባይለቃትም ጥሩ አድርጋ ጠረገችለት።

"አሁን ሁሉም አብቅቷል" አላት ሪካርዶ

መንቀጥቀጧን አሁንም አላቆመችም።

ሪካርዶ እጇን ያዝ አድርጎ "ሽሽ። ሞቷል እኮ። ከአሁን በኋላ የሚያስፈራሽ ነገር የለም"

ጥብቅ አድርጎ ያዛት። ትንፋሿ ተሰማው። በድንገት ከንፈሯን ከንፈሩ ላይ አሳረፈችው። ወደራሷ አስጠግታ አቀፈችው። የማይገባውን ነገር እያንሾካሾከችለት ነው።

ግራሼላን ሁልጊዜ ማወቅ አዳጋች ነው። አሁንም ስለእሷ የሚያውቀው ነገር የለም። ከዚህ ውጭ የአምላክ ድንቅ ስራ ነች። ሲል አሰበ።

ግራሼላም በበኩሏ አምላኳን እያሰበች ነው። አመሰግናለሁ። አምላኬ ለእዚህ ደስታ ስላበቃኸኝ አመሰግንሀለው። በመጨረሻ ፍቅር ምን እንደሆነና ስሜቱን እንድረዳ ስላደረከኝ አመሰግንሀለሁ።

ለእሷ ቃላት የማይገልፀው አዲስ ልምድ ነበር። ሪካርዶ አሁንም ውበቷን እያደነቀ ነው። አሁን የእኔ ነች ሲል አሰበ። ወደ ገዳም አትመለስም። እንግባና ቆንጆ ልጆች እንወልዳለን።

"አፈቅርሻለሁ" አላት። "ግራሼላ ከእኔ ተለይተሽ እንድትሔጂ አልፈልግም"

"ሪካርዶ. . ."

"የእኔ ውድ ላገባሽ እፈልጋለሁ። ታገቢኛለሽ?"

ግራሼላ ሳታቅማማ "አዎ። አዎ" አለችው።

በድጋሚ ክንዱ ላይ ዘፍ አለች። ሊያስበው የነበረው ይህንኑ ነበር። ፈረንሣይ ትንሽ ቆይተው ውጊያው ሲያበቃ ወደ ስፔን እንደሚመለሱ ነገራት። ከዚህ ሰው ጋር የትም ትሄዳለች። አደጋውንም ትጋራለች።

ስለብዙ ነገር አወሩ። ከጄሚ ሚሮ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት እንደተገናኙ

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]





[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

እናም አሰበች፡፡ ገዳሙን መተው እንዲህ ቀላል ውሣኔ ነውን? በግራሼላ ተገርሜያለሁ? ወይስ በራሴ ነው መገረም ያለብኝ?

ኮሎኔል አኮካ በረዳቶቹ ሪፖርት ደረሰው፡፡

"ከአንድ ሰዓት በፊት ሰርከሱ አካባቢ ታይተዋል፡፡ እኛ ስንደርስ እነሱ ሔደዋል፡፡ በሰማያዊ እና ነጭ ሽፋን መኪና ነው የሔዱት፡፡ ልክነህ ኮለኔል፡፡ ወደ ማንጀቪያ ነው የሚጓዙት፡፡

በመጨረሻ ሁሉም ነገር ሊያበቃ ነው ሲል ኮሎኔል አኮካ አሰበ፡፡ መሳደዱ ቢያስደስተውም ጂሚ ሚሮ እውነተኛ ተቀናቃኝ መሆኑን ተቀብሏል፡፡ ኢፕስ ሙንዶ አሁን ለእኔ ትልቅ እቅድ ይኖረዋል፡፡

በግዙፍ አጉሊ መነጽር ኮሎኔል አኮካ ሰማያዊና ነጭ ሽፋን መኪና እየፈለገ ነው፡፡ ከጋሪው አናት ላይ ሆኖ ወደገዳሙ የሚጓዙ መኪኖችን ይቃኛል፡፡ በመንገዱ ግራና ቀኝና በገዳሙ አቅራቢያ ብዛት ያላቸው የታጠቁ ወታደሮች አድፍጠዋል፡፡ ማንም ሰው የሚያመልጥበት ምንም እድል የለውም፡፡

ሽፍን መኪናው ወደ ገዳሙ ተጠግቶ ሲቆም ኮሎኔል አኮካ በያዘው የመገናኛ ሬዲዮ ተጠጉ! አሁን!

ከበባው በትክክል ሰርቷል፡፡ የታጠቁት ሁለት ደርዘን ወታደሮች ቦታቸውን ያዙ፡፡ መንገዱን ዘግተው ሽፍኑን መኪና ከበቡት፡፡ ኮሎኔል አኮካ በደስታ ትእይንቱን እየተመለከተ ነው፡፡ በእጁ ሽጉጥ ይዞ በዝግታ ወደ መኪናው ተጠጋ፡፡

"ተከባችኋል" በማለት ተጣራ፡፡ ምንም እድል የላችሁም፡፡ እጃችሁን ወደላይ አድርጋችሁ ውጡ፡፡ ለየብቻ ውጡ፡፡ እምቢ ካላችሁ ሁላችሁም ትሞታላችሁ፡፡

ከብዙ ዝምታ በኋላ የመኪናው በር ተከፈተና ሦስት ወንዶችና ሦስት ሴቶች እየተንቀጠቀጡ እጃቸውን ወደላይ አድርገው ወጡ፡፡

ሁሉም እንግዶች ናቸው፡፡





# ምዕራፍ ሠላሣ ስድስት

ከገዳሙ በላይ ያለው ጋሪ ላይ ሆነው ጂሚና ጓደኞቹ ኮሎኔል አኮካ ወደ ሽፋን መኪናው ሲንቀሳቀስ እየተመለከቱት ነው፡፡ በድንጋጤ የተዋጡት ተሳፋሪዎች እጃቸውን ወደ ላይ አንስተው ነገሩን እየታዘቡ ነው፡፡

"ጂሚ ሚሮ የሚነጋገሩትን ቢሰማ ደስ ባለው ማን ናችሁ?"

"ሎጋርኖ አቅራቢያ የሚገኝ ሆቴል ሠራተኞች ነን፡፡"

"እዚህ ምን ታደርጋላችሁ?"

"አንድ ሰው አምስት ሺ ፔስታስ ሰጥቶን ይህን መኪና እዚህ ገዳም እንድናደርስ ነገረን፡፡"

"ምን ዓይነት ነው?"

"አላውቅም፡፡ ከዚህ በፊት አይቼው አላውቅም"

"ይህን ፎቶ ይመስላል?"

"አዎ እሱ ነው"

"ከዚህ ወጥተን እንሒድ" አለ ጂሚ፡፡

በነጭ ስቱሽን ዋገን ተጭነው ወደ ሎጋርኖ ተመለሱ፡፡ ሜጋን ጂሚን በመገረም እያየችው ነው፡፡

"እንዴት አወክ?"

"ኮሎኔል አኮካ እኛን ገዳሙ ጋር እንደሚጠብቀን ? እራሱ ነገረኝ፡፡

"ምን?"

"ቀበሮዋ ማሰብ ያለባት በአዳኙ ቦታ ሆና ነው ሜጋን ፡፡ እራሴን በአኮካ ቦታ አስቀመጥኩት ወጥመዱን የት ጋር ነው የሚዘረጋው? ያሰብኩትን ነው ያደረገው››

"ባይመጣስ ኖሮ?"

# ምዕራፍ ሠላሣ ሰባት

የእስራኤል አምላክ ከእናንተ ጋር ይሁን። ይባርካችሁ እያሉ ቄሱ ፀሎታቸውን ቀጥለዋል።

ሪካርዶ አይኑን ከቄሱ ላይ አንስቶ አ ጠገቡ የቆመችውን ግራሺላን እየተመለከተ ነው። ልክ ነበርኩ። እሷ በአለም ላይ ላሉ ሙሽሮች ቆንጆዋ ናት።

ግራሺላ የቄሱን ቃላት በፅሞና እያዳመጠች ነው። በቤተ ክርስቲያኑ የሰላም ስሜት ሰፍኗል። ግራሺላ ካለፉት አስፈሪ ጭንቀቶቿ ተላቃለች። የሰው ልጆች ሰላም ፍለጋ ወደዚህ ቦታ መምጣት ከጀመሩ ብዙ ዘመናት አስቆጥረዋል። ልክ ገዳም ያለች ያህል ተሰምቷታል። ወደ ቤቴ በድጋሚ የገባሁ ያህል ተሰምቶኛል ስትል አሰበች።

አምላኬ ከሚገባው በላይ ባርኮኛል። የእሱን ዋጋ መክፈል አለብኝ፡ የቄሱ ፀሎት ቀጥሏል።

የእኔ ዘመን ባንተ እጅ ነው። ቀሪ የህይወት ዘመኔን ባንተ ላይ ጥያለሁ። ግራሺላ ፍፁም ተደስታለች።

ሐጢያት ሰርቼ እንዴት ይቅር ሊለኝ ይችላል?

ግራሺላ በድንገት መተንፈስ አቃታት። በሩ የተዘጋባት መስሎ ተሰማት። እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ።

በዛ ቅፅበት ከግራሺላ ህይወት ውስጥ ተነቅሎ ወጣ። በደስታ ተሞላች።

ቄሱ እየተናገሩ ነው። "መንግሥተ ሰማያትን ያዋርሳችሁ። ይህንን ጋብቻ እንድትባርክ እንጠይቅሀለን። እና …"

"እኔ ቀደም ብሎ አግብቻለሁ" አለች ግራሺላ ጮክ ብላ። በድንገት አስፈሪ ዝምታ ሰፈነ። ሪካርዶና ቄሱ እየተመለከቷት ነው። የሪካርዶ ፊት ገርጥቷል።

"ግራሺላ ምን እያደረግሽ …? "

እጁን ይዛ ለስለስ ባለ አንደበት "አዝናለሁ ሪካርዶ"





"አልገባኝም። እኔን ማፍቀርሽን አቆምሽ?"

አንገቷን ነቀነቀች። "ከህይወቴ አስበልጬ አፈቅርሀለሁ። ነገር ግን ከእንግዲህ በኋላ የእኔ ህይወት የእኔ አይደለም። ከረጅም ጊዜ በፊት ለአምላኬ ሰጥቼዋለሁ።"

"አይሆንም! ህይወትሽን መስዋእት እንዳታደርጊ .."

"የምወድህ ሪካርዶ … መስዋትነት አይደለም። መባረክ ነው። የመጀመሪያ ሰላሜን ያገኘሁት ገዳም ውስጥ ነው። አንተ የአለም ሰው ነህ። ስለዚህ ይህን አለም ትቼ ወደራሴ አለም መመለስ አለብኝ።"

ቄሱ ባሉበት ቆመው እያዳመጧት ነው።

"ላደረስኩብህ ህመም ይቅር በለኝ። ነገር ግን ቃሌን ማጠፍ አልችልም፡ ፡ የማምነውን ነገር በጠቅላላ ክጄዋለሁ። ነገሩ የገባኝ አሁን ነው። በፍፁም ደስተኛ መሆን አልችልም። እባክህ ተረዳኝ።

ሪካርዶ እየተንቀጠቀጠ ይመለከታታል። ከአፉ ቃል አልወጣም። በውስጡ የሆነ ነገር ሲሞት ተሰማው።

ግራሺላ የገረጣ ፊቱን እየተመለከተች ልቧን ከልቡ አራቀቻቸው። ጉንጩ ላይ ሳመችው። "አፈርቅሀለሁ" አለችው በዝግታ አይኗ በእምባ ተሞልቷል። "እፀልይልሀለሁ። ለሁለታችንም እፀልያለሁ።"

# ምዕራፍ ሠላሣ ስምንት

አርብ ረፋዱ ላይ የጦር ሠራዊት አምቡላንስ ወደ አራንዳ ዱሬ የድንገተኛ ህመም መግቢያ በር ተጠጋ:: ሁለት የፖሊስ ልብስ ያጠለቁ ግለሰቦች ከአንቡላንሱ ሹፌር ጋር አብረው መጥተዋል:: ከወንበሩ ጀርባ ወደተቀመጠው ተቆጣጣሪ ተጠጉ::

"ሩቢዮ አርዛኖን እንድንወስድ ትእዛዝ ተሰጥቶናል" አለ አንዱ ፖሊስ:: የሆነ ወረቀት አቀበለው::

ተቆጣጣሪው ከተመለከተው በኋላ ፊቱን አጨፈገገ:: "እሱን የመልቀቅ ስልጣን ያለኝ አይመስለኝም:: ጉዳዩ የተያዘው በአገር ገኘሮው እጅ ነው::

"ደህና:: አገናኘኝ::"

ተቆጣጣሪው አመነታ:: "አንድ ችግር አለ:: ለእረፍት ወጣ ብሏል"

"ይህ የእኛ ችግር አይደለም:: የማስፈቻ ትእዛዙን ሰጥተንሀል:: የተፈረመው በኮሎኔል አኮካ ነው:: ደውለን በክብር እንዳልሰጠኸን እንንገረው?"

"አይሆንም" አለ በጥድፊያ:: "አስፈላጊ አይደለም:: እንዲፈቱት እንነግራቸዋለን::"

ግማሽ ማይል ርቆ ከሚገኘው የከተማዋ እስር ቤት ሁለት መርማሪዎች ከፖሊስ መኪና ውስጥ ወርደው ወደህንፃው እየተጠጉ ነው:: መረጃ ተቀባይ ወታደሩ አጠገብ ደረሱ::

አንዱ ግለሰብ መታወቂያውን አሳየው:: "ሉቺያ ካርማይን ለመውሰድ ነው የመጣነው::"

ወታደሩ ሁለቱን ግለሰቦች እየተመለከተ "ስለዚህ ጉዳይ የነገረኝ ሰው የለም::"

አንዱ መርማሪ በኃይል ተነፈሰ:: "የማይረባ ቢሮክራሲ ግራ እጁ የሚያደርገውን ነገር ለቀኝ እጁ ነግሮት አያውቅም"

"የማስፈቻ ትእዛዙን ልመልከተው::"





መርማሪው አቀበለው::

"ኮሎኔል አኮካ ፈርሞበታል?"

"ልክ ነህ"

"የት ነው የምትወስዷት?"

"ማድሪድ" ኮሎኔሉ ራሱ ሊመረምራት ይፈልጋል"

"እሱ ራሱ? ደህና ከእሱ ጋር መነጋገር አለብኝ ይመስለኛል::

"ያንን ነገር ማድረግ አስፈላጊ አይደለም" በማለት መርማሪው ተቃወመው::

"እቺን ሴት በተመለከተ ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቶናል:: የጣሊያን መንግሥት እሷን ለመቀበል ቸኩሏል:: ኮሎኔል አኮካ ከፈለጋት በቀጥታ ለእኔ ሊነግረኝ ይገባል::"

"ጊዜያችንን እያባከንክ ነው:: እና ..."

"እኔ ብዙ ጊዜ አለኝ ወዳጄ:: የራሴን ችግር ሳልፈታ የሰው ችግር መሸከም አልፈልግም" በማለት ስልኩን አንስቶ "ኮሎኔል አኮካን ከማድሪድ አገናኙኝ::"

"እየሱስ ክርስቶስ" አለ መርማሪው:: "በድጋሚ ለአራት ከዘገየሁ ሚስቴ ትገለኛለች:: ኮሎኔሉም ቢሆን ዝም..."

ጠረጴዛው ላይ ያለው ስልክ ጮኸ:: ወታደሩ አነሣው::

"ከኮሎኔሉ ቢሮ ጋር አገናኙኝ"

መርማሪው ወታደሩን በተከፋ ገጽታ ተመለከተው:: "ሔሎ ይህ አራንዳ ዱሮ የሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ መረጃ ተቀባይ ወታደር ድምፅ ነው:: ከኮሎኔል አኮካ ጋር ለብርቱ ጉዳይ መነጋገር እፈልጋለሁ::"

አንዱ መርማሪ ትእግስት በማጣት ስሜት ሰአቱን እየተመለከተ ነው:: "እዚህ ከመቆም የበለጠ የምሰራቸው ጠቃሚ ጉዳዮች ነበሩኝ እና ..."

"ሔሎ ኮሎኔል አኮካ?"

በስልኩ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ ጮክ ብሎ "አቤት:: ምንድን ነው?

እኔና ሩቢዮ ሁለት የተለያየ ህይወት ያለን ነን። በተለያየ አለም የኖርን ነን። እኔ አንጀሎ ካርታማይን ሴት ልጅ ነኝ"

"እባክዎት ቁጥሩን?"

እሱ ገበሬ ነው የሚወደው እሱን ነው። ከእዚህ እንዴት ልነጥለው እችላለሁ? በእሱ ላይ ያንን ማድረግ አልችልም።

ኦፕሬተሯ ትእግስቷ አለቀ። "ምን ልርዳሽ?"

ሉቺያ በዝግታ አመሰግናለሁ። የምትረጂኝ ነገር የለም በማለት ስልኩን ዘጋችው። በሚቀጥለው ቀን ወደሪዮ ስትሄድ ብቻዋን ነበረች።





# ምዕራፍ ሠላሣ ዘጠኝ

ውይይቱ የተከናወነው በኤለን ስኮት የከተማ ቪላ ውስጥ ነው። አለን ተከር ልጅቷን ይዟት እስኪመጣ ድረስ መታገስ አቅቷታል። ልጃገረድ አይደለችም። ሴት ትሆናለች። መነኩሴም ነች። ምን ትመስል ይሆን? ህይወቷን እንዴት ነው የገፋችው? ለእሷ ምን ማድረግ አለብኝ?

ጋሽ ጃግሬው ወደ ክፍሉ ገባ። "እንግዶችሽ ደርሰዋል ማዳም"

በሐይል ተነፈሰችና "አስገባቸው" አለች።

ከአፍታ በኋላ ሚጋንና አለን ተከር ወደ ክፍሉ ገቡ።

ቆንጆ ናት ስትል ኤለን ስኮት አሰበች።

ተከር ፈገግ አለ። "ወይዘሮ ስኮት እሷ ሚጋን ነች"

ኤለን ስኮት ቃል ሳትተነፍስ ተመለከተችው። "ከዚህ በኋላ አታስፈልገኝም" አለችው። ንግግሯ ለሁለቱ የመጨረሻቸው ነበር።

ፈገግታው ደበዘዘ።

"ደህና ሁን ተከር"

ባለበት ደርቆ ቀረ። አላመነም ነበር። ነገር ግን አንገቱን እየነቀነቀ ወጣ። የሆነ ነገር እንዳጣ ስለገባው ስሜቱን መቆጣጠር አቃተው። ዘግይቻለሁ ሲል አሰበ።

ኤለን ስኮት ሚጋንን እያጠናቻት ነው። "እባክሽ ተቀመጪ" ሚጋን ወንበር ስባ አረፍ አለች። ሁለቱ ሴቶች እርስ በርስ እየተጠናኑ ነው።

እናቷን ትመስላለች ስትል ኤለን ስኮት አሰበች። ቆንጆ ሴት ሆና አድጋለች። አደጋው የደረሰበት ምሽት ትዝ አላት። ነጎድጓዳማው አርና የአውሮፕላኑ መንደድ።

ሞታለች ብለሽኝ አልነበረም ... ሌላ መንገድ አለ ... ፓይለቱ አቪላ አቅራቢያ ነን ብሏል። እዚህ ብዙ ቱሪስቶች አሉ። ልጅቷን ከአውሮፕላኑ

# ምዕራፍ አርባ

አዲስ የሆነ ሰው ከመኪናው መግቢያ በር ላይ ቆሟል፡፡ ይህ ደግሞ ጀሚ ሚሮን አበሳጨው፡፡

"በእሱ እርግጠኛ አይደለሁም" በማለት ፌሊክስ ካርፒዮ ነገረው፡፡ "እየነዳ ትቶን ቢሄድ ምን ታደርጋለህ?"

"ዘና በል፡፡ እሱ የአጐቴ ልጅ ባል ነው፡፡ ጥሩ ሰው ነው፡፡ ከእኛ ጋር ለመውጣት እድል እንዲሰጠው ይለምን ነበር፡፡"

"መጥፎ ስሜት እየተሰማኝ ነው" አለ ጀሚ፡፡

በዛው እለት ረፋድ ላይ ሲቪላ ደረሱ፡፡ እቅዳቸውን ከማሳካታቸው በፊት ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ ባንኮችን አጣሪ፡፡ ከመንገዱ ባሻገር ያገኙት ባንክ ትንሽና የትራፊክ ግርግር ያልበዛበት ነበር፡፡ አጠገቡ ፋብሪካ አለ፡፡ ሁሉም ነገር ጥሩ ይመስላል፡፡ መኪናው አጠገብ ከቆመው ሰው በስተቀር፡፡

"ይህ ነው እንዲህ ያስጨነቀህ?" ሲል ፌሊክስ ጠየቀው፡፡

"አይደለም"

"እና ምንድን ነው?"

ለመመለስ አስቸጋሪ ሆነበት፡፡ "የማይሆን ብለህ ጥራው" በማለት በዝግታና በቅሬታ ተናገረ፡፡

ፌሊክስ ነገሩን በቁም ነገር ወሰደው፡፡ "ልታባርረው ትፈልጋለህ?"

"ምክንያቱም ጥሩ ያልሆነ ስሜት ያደረብኝ መሰለኝ? አይደለም ወዳጄ፡፡ ነገሩ በቀላሉ ይጠናቀቃል፡፡

በመጀመሪያ ነበር፡፡

በባንኩ ብዙ ደንበኞች ነበሩ፡፡ ፌሊክስ በመሣሪያ አስገድዶ ሲያስተኛቸው ጀሚ ከመሳቢያዎች ውስጥ ገንዘብ እየሰበሰበ ነበር፡፡ እንዳለው ነገሩ ቀላል ነበር፡፡

ሁለቱ ሰዎች ወደ መውጫው በር ተጠግተው ወደ መኪናው ሲቃረቡ





ጀሚ "ወዳጄ ገንዘቡን ለጥሩ ጉዳይ እንደምንፈልገው እንዳትረሳ" በማለት ጮሆ ተናገረ፡፡

ወደ ውጭ እንደወጡ ነበር ነገሩ መበላሸት የጀመረው፡፡ በየቦታው ፖሊሶች ነበሩ፡፡ የመኪናው ሹፌር የመንገዱ ጠርዝ ላይ ተንበርክኳል፡፡ ፖሊስ ግንባሩ ላይ ሽጉጥ ደቅኖበታል፡፡

ጀሚ እና ፌሊክስ በግልጽ ሲታዩ አንዱ መርማሪ ከፍ ባለድምፅ "መሣሪያችሁን ጣሉ" አላቸው፡፡

ጀሚ ለሰከንድ ካመነታ በኋላ መሣሪያውን አነሣ፡፡

"ሜጋን እኔና አንቺ ጥሩ ወዳጆች በመሆናችን እውነቱን ልንግርሽ ይገባኛል። እየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሊያድነው አይችልም። ተአምር ነው የምትጠብቂው ..."

"በተአምራት አምናለሁ። ትረዳኛለህ?"

ለቅፅበት አጠናት። "ምን አይነት ፈተና ነው። ጉደኛ ለመቼ ነው? ምግባቸውን ሞክረሽው ታውቂያለሽ? በጣም ጣፋጭ ነው።"

ከማድሪድ የመጣው ፋክስ እንዲህ ይነበባል። "በአውሮፓ ያሉ በደርዘን የሚቆጠሩ ጠበቆችን አነጋግሬያለሁ። ሚሮን ለመወከል ፈቃደኛ አይደሉም። እኔ ራሴ ችሎት ፊት ለመቆም እሞክራለሁ። ፍርድ ቤቱ አይሆንም ብሎኛል። ለአንቺ ለጓደኛዬ ስል ተአምሩን ለመሳብ እሞክራለሁ። ነገር ግን እየሱስ ክርስቶስ ገና አልተነሣም። ወደ ቤት እየተመለስኩ ነው። ምሳ የመጋበዝ እዳ አለብሽ። ማይክ?"

ችሎቱ የሚከፈተው ሴፕቴምበር 17 ነው።

"ቀጠሮዬን ሰርዝ" አለች ሜጋን ለረዳቷ። "ማድሪድ ላይ የማከናውነው ሥራ አለኝ"

"ምን ያህል ጊዜ ትቆያለሽ?"

"አላውቀውም።"

አትላንቲክን ስታቋርጥ እቅዷን እያዘጋጀች ነበር።" የሆነ መንገድ ይኖራል ስትል ሜጋን አሰበች። ገንዘብና ኃይል አለኝ። ቁልፉ ያለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ላይ ነው። ክሱ መታየት ከመጀመሩ በፊት ላገኘው ይገባል። ከዛ በኋላ ከሆነ ግን ይዘገያል።

ሜጋን ማድሪድ ከደረሰች በሀያ አራት ሰአት በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ሊኦፓልዶ ማርቲኔዝ ጋር ቀጠሮ ያዘች። በቤተመንግሥቱ ውስጥ ምሣ ተጋበዘች።

"በፍጥነት ሊያገኙኝ በመፈለግዎ አመሰግናለሁ" አለች ሜጋን። "ምን ያህል ሥራ እንደሚበዛብዎት አውቃለሁ።"

እጁን በአድናቆት እየዘረጋ "የእኔ ውድ ስኮት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የስኮት ኢንዱስትሪ መሪ እኔን ለማግኘት ወደ አገሬ ስትመጣ የሚሰማኝ ክብር





ብቻ ነው። በምን አይነት መንገድ እንደምረዳሽ ንገሪኝ።"

"እኔ ነኝ ልረዳዎት የመጣሁት" አለች ሜጋን። "ውስጥ ጥቂት ፋብሪካዎች ቢኖሩንም አገርዎት የሰጠችኝን ያህል እየተጠቀምንባቸው አይደለም።"

አይኑ በርቶ እያዳመጣት ነው። "አዎ"

"የስኮት ኢንዱስትሪ ግዙፍ የኤሌክትሮኒክስ ማምረቻ መክፈት ይፈልጋል። ከአንድ ሺህ እስከ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሠራተኛ ይይዛል። ፋብሪካው አዋጪ ከሆነ ሌሎች ቅርንጫፎችን እናስፋፋለን።"

"ይህን ፋብሪካ የት አገር መክፈት እንዳለብሽ አልወሰንሽም ማለት ነው?"

"ትክክል። እኔ በግሌ ስፔንን እመርጣለሁ። ግን እውነቱን ለመናገር ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች በእዚህ ደስተኛ አለመሆናቸውን ለክቡርነትዎ መናገር እፈልጋለሁ። በሰብአዊ መብት አያያዛችሁ ቅሬታ አላቸው።"

"እውነትሽን ነው?"

"አዎ። የመንግስትን ፖሊሲ የሚቃወሙትን ሐሣቦች በአስከፊ ሁኔታ ነው የምትይዙት በማለት ይናገራሉ።"

"በአእምሮሽ በተለየ መንገድ የያዝሽው ሰው አለ?"

"እንደ እውነቱ ከሆነ አዎ አለኝ። ጄሚ ሚሮ።"

በተቀመጡበት እየተመለከቷት ነው። "ገባኝ። በጄሚ ሚሮ ጉዳይ መደራደር ከቻልን የኤሌክትሮኒክስ ኩባንያውን እናገኛለን እና ..."

"እናም ከሱ የበለጠ ነገሮችን" በማለት ሜጋን አረጋገጠችላቸው። "የእኛ ኩባንያዎች ማህበረሰቦቹ ባሉበት ቦታ ሁሉ ኑሮአቸውን ለማሻሻል ይሠራል።"

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመጠራጠር ተመለከቷት። "አንድ ችግር መኖሩን ስነግርሽ ቅር እያለኝ ነው።"

"ምንድን ነው? ገፍተን መደራደር እንችላለን።"

"ለስምምነት የማይመች ጉዳይ ነው። ወይዘሪት ስኮት። የስፔን ክብር ለሽያጭ አይቀርብም። እኛን መደለል ወይም መግዛት ወይም ማስፈራራት

በዚህ ወቅት ዲላፎንቴን ዶክተር አናቺዩን እየተመለከቱ ነበር በክፍሉ ቀዳዳ ከውጭ የሚመጣው ጩኸት ይሰማቸዋል::

ዲሊፎንቴ ጂሚን ተመልክቶ ሰቀጠጠው:: "ለውጥ የለውም:: እግዚአብሔር ምን ሊል እንደፈለገ ይገባዋል::"

አንገት መስቀያውን የያዘው ግዙፍ ሰው በጂሚ ጀርባ በኩል ሔዶ ቆመ:: ጉሜዝ ዲላፎንቴ "ፊትህ እንዲሸፈን ትፈልጋለህ?" ሲል ጠየቀው::

"አልፈልግም"

ኃላፊው ግዙፉን ሰው እየተመለከተ አንገቱን ነቀነቀ:: ሰውየው አንገት መስቀያውን ከፍ አድርጐ በመያዝ ወደ ፊት ተጠጋ::

ከውጭ አሁንም ጩኸት ይሰማል::

"አንድ ነገር ታውቃለህ? አለ ከጠባቂዎቹ አንዱ::" ከእነሱ ጋር ውጭ አብሬያቸው ብሆን ደስይለኝ ነበር::

ከአምስት ደቂቃ በኋላ አረንጓዴው በር ተከፈተ::

ዶክተር አናቺዩን "በድኑ የሚጠቀለልበትን ቦርሣ አምጣ አሉ::

በትዕዛዙ መሰረት የጂሚ ሚሮ በድን ከእስር ቤቱ የጓሮ በር በድብቅ ወጣ:: በድኑ ምልክት በሌለው ሸፍን መኪና ላይ ተጫነ:: መኪናው ከእስር ቤቱ በወጣበት ቅፅበት ውጭ ያለው ህዝብ ወደፊት መጠጋት ጀመረ:: የሆነ ማግኔት የሚስባቸው ይመስላል::

"ጂሚ . . . ጂሚ . . . ."

አሁን ጩኸቱ እየቀነሰ ነው:: ወንዶችና ሴቶች እያነቡ ነው ልጆቻቸው በመገረም ይመለከቷቸዋል:: ነገሩ ፈፅሞ አልገባቸውም:: መኪናው በግርግሩ መሐል አቋርጦ ወደ ዋናው ጐዳና ገባ::

"እየሱስ አለ ሹፌሩ::" እርኩስ መንፈስ ይመስላል:: ሰውዬው የሆነ ነገር ሳይኖረው አይቀርም::"

"አዎ ብዙ ሺ ሰዎች ነገሩን ያውቁታል::"

በዛው እለት ስምንት ሰአት ላይ የእስር ቤቱ ኃላፊ ዋርደን ጐሜዝ ዲላፎንቴና





ሁለቱ ረዳቶቹ ጁአኒቶ ሞሊናስና ፔድሮስ አራናጐ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርቲኔዝ ቢሮ ተገኙ::

እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ" አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ:: "ቅጣቱ ድንቅ በሆነ መንገድ ነው የተፈፀመው::"

ኃላፊው "ቅጣቱ ድንቅ በሆነ መንገድ ነው የተፈፀመው"

ኃላፊው "ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እዚህ የመጣነው የእርስዎን ሙገሣ ለመቀበል አይደለም:: ስራችንን በፈቃዳችን ለመልቀቅ ነው::"

ማርቲኔዝ አተኩረው ተመለከቷቸው:: ግራ ገብቷቸዋል::" ነገሩ አልገባኝም . . .ምን . . .?

"ሰብአዊነትን የተመለከተ ጉዳይ ነው:: ክቡርነትዎ:: ሰውየው ሲሞት ቆመን ተመልክተናል:: ምናልባት ሞት ይገባው ይሆናል:: ግን በዛ መልክ መሆን አልነበረበትም:: ጥንታዊና አረመኔያዊ አገዳደል ነው:: ከዚህ በኋላ የዚህ አካል መሆን አልፈልግም:: ጓደኞቼም የሚሰማቸው ይኸው ነው::"

"ብታስቡበት የሚሻል ይመስለኛል:: ጡረታችሁን . . ."

"ህሊናችን ሳይሸነቁጠን መኖርን መርጠናል" በማለት ዋርደን ዲላፎንቴ ሶስት ወረቀቶችን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቀበላቸው:: የመልቀቂያ ደብዳቤያችን ነው::"

በዛው ምሽት ሸፍኑ መኪና የፈረንሣይን ድንበር አቋርጦ ቢዳቼ ወደተባለችው አነስተኛ መንደር ተጠጋ:: መንደሯ ባዮኔ አጠገብ ትገኛለች:: ወደ አንድ የገበሬ ቤት ተጠጉ::

"ቦታው እዚህ ነው:: ሰውነቱ ከመሸተቱ በፊት እናስወግደው::

የገበሬው መኖሪያ ቤት በር እድሜዋ ወደ ሀምሣዎቹ በተጠጋ ሴት ተከፈተ:: "አመጣችሁት?"

"አዎ እማማ:: የት ቦታ . . . ይፈልጋሉ?

"የእንግዳ ማረፊያው ውስጥ አድርጉት እባካችሁ::"

"እሺ እማማ:: እሱን ለመቅበር ብዙ ጊዜ ማጥፋት አልፈልግም:: ምን

ለማለት እንደፈለኩ ይገባዎታል?"

ሁለቱ ሰዎች በድኑን ተሸክመው ወለሉ ላይ ሲያስቀምጡት እየተመለከቱ ነው።

"አመሰግናለሁ"

"ምንም አይደል"

መኪናቸውን ይዘው ከአይን እስኪርቁ ቆማ ተመለከተቻቸው። አጠገቡ ካለው ክፍል የወጣችው ሌላ ሴት በሩጫ በድኑ ወደ ተጠቀለለበት ቦርሣ ከነፈች። በጥንቃቄ ዚፑን ከፈተችው።

ጀሚ ሚሮ በሰዎቹ ላይ እየሣቀ ውስጡ ተጋድሞ ነበር። "የሆነ ነገር ታውቂያለሽ? አንገት መቅያው ማጅራቴ ላይ እውነተኛ ህመም ጥሎብኛል።"

"ነጭ ወይስ ቀይ ወይን?" ስትል ሜጋን ጠየቀችው።





# ምዕራፍ አርባ ሶስት

ማድሪድ በሚገኘው የባራዳስ አየር ማረፊያ የቀድሞው የእስር ቤት ኃላፊ ቀርደን ጐሜዝ ዲ ላፎንቴ እና የቀድሞ ረዳቶቹ ሞሊናስና ኢራንጐ እንዲሁም ዶክተር አናቺዬና ግዙፉ ሰው የእንግዳ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ ተቀምጠዋል።

"ከእኔ ጋር ወደ ፓርቶርኮ አልሔድም ማለትህ አሁንም ስህተት መስሎ እየተሰማኝ ነው" አለ ዲላፎንቴ።" በአምስት ሚሊዮን ዶላርህ አጠቃላይ ደሴቱን መግዛት ትችላለህ።"

ሞሊናስ ጭንቅላቱን ነቀነቀ። "እኔና አራንጐ ወደ ስዊዘርላንድ እንሔዳለን። ፀሐይ ሰልችቶኛል። ጥቂት የበረዶ ጥንቸሎች በመግዛት እንዝናናለን።

"እኔም እንደዛው ነኝ" አለ ግዙፉ ሰው። ወደ ሚጉዌል አናቺዬ ዞሩ።

"አንተስ ዶክተር?"

"ወደ ባንግላዴሽ እሔዳለሁ"

"ለምን?"

"ልክ ነህ። ገንዘቡን እዛ አገር ሆስፒታል እከፍትበታለሁ። ታውቃለህ ይህን ጉዳይ የሜጋንን መደራደሪያ ከመቀበሌ በፊት ለረጅም ጊዜ ሳስብበት የኖርኩበት ነው። ግን የአንድ አሸባሪን ህይወት በማዳን የብዙ ንፁሃንን ህይወት ማትረፍ ትልቅ የንግድ ድርድር ነው። ከዚህ ጐን ለጐን መናገር ያለብኝ ጀሚ ሚሮን እወደዋለሁ።"

# ምዕራፍ አርባ አራት

በፈረንሣይ ገጠራማ ክፍል ያለው ብሩህ ወር ነው። ገበሬዎች ዘር እየዘሩ ነው። ሁሉም ወቅት እንዲህ ቢሆን እንዴት ደስ ይል ነበር ሲል ሩቢዮ አርዛኖ አሰበ። በብዙ መልኩ ካለፈው አመት የተሻለ ነው።

መጀመሪያ ጋብቻው ከአመት በኋላ የመንታ ልጆቹ መወለድ። ከዚህ የበለጠ ደስታ የሚያስብ ሰው አለ?

መዝነብ ጀምሯል። ሩቢዮ ትራክተሩን አዙሮ ወደ ቤቱ ሲመለስ ስለመንታ ልጆቹ እያሰበ ነበር። ወንዱ ግዙፍ ነው ግን እህቱ! ጥንቃቄ ያስፈልጋታል። ባሏን ስራ ታበዛበታለች። በማለት ሩቢዮ  ደግሞ አሰበ። ከእናቷ የወረሰችው ነው።

ወደ ቤቱ ሲጠጋ ጥሩ ስሜት ተሰማው። በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ።

"በሰአትህ ከች አልክ" አለችው ሉቺያ እየሳቀች። "እራት ተዘጋጅቷል።"

የገዳሙ እማሆይ ፕሪኦርስ ቤቲና ከእንቅልፋቸው የነቁት ድንቅ ነገር እንደሚከሰት እያሰሙ ነው።

ልክ ነው። እስከ አሁን ብዙ ድንቅ ተአምራቶች ተፈፅመዋል።1


የሴቶቹ ገዳም ከተከፈተ ጊዜ አንስቶ በንጉስ ዶንጁዋን ካርሎስ ጥበቃ ስር ሆኗል። ሲስተር ግራሼላና ሌሎቹ መነኩሳት ከተወለዱበት የማድሪድ ከተማ በደህና ሁኔታ ተመልሰዋል። በድጋሚ እራሳቸውን ለአምላካቸው በገዘምታ አሳልፈው ሰጥተዋል።

ቁርስ ከተበላ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እማሆይ ፕሪኦሬስ ወደ ቢሮአቸው ሲገቡ አንድ ነገር ላይ አተኩረው ቆሙ። ጠረጴዛቸው ላይ የሚያብረቀርቀው የወርቅ መስቀል ተቀምጧል።

በተአምር የተገኘ ያህል ቆጥረው ተቀበሉት።

ተፈፀመ

አራቱ መነኮሳት ባልጠበቁት ፍጥነት ከብዙ ዓመታት በፊት "ዓለም በቃኝ" ብለው ጥለውት ወደነበረው ጨለማው ዓለም ተመልሰው ቃልኪዳናቸውን ሊፈታተናቸው ተጋፈጡት፡፡ የዓይን እማኝ በሌለበትና ስለምንና ምንም ባላወቁበት ትዕይንት ውስጥ ገብተው ሁለት ጽንፍ በወጡ ባላንጣዎች ከባለግርማ ሞገሱ የባስኮዎች መሪ ጄም ማሪዮና ከስፔኑ ወታደራዊ አዛዥ አይምሬው ኮሎኔል ራሞን አኮካ መዳፍ ስር ዋሉ፡፡




ዘ ሳንድስ ኦፍ ታይም (The Sands of Time) ጊዜ ከማይሽራቸው ትዕንግርት ከሚመስሉ የስፔን ኮረብታዎች ተከታታይና ውስብስብ ታሪኮች ቅንብር፣ ልብን በሚያቆመሙ ታሪኮችን የሰደረ መፅሐፍ ነው፡፡

የሽፋን ገጽ ዲዛይን 0913450005

ዋጋ 150.00 ብር